pdf by @shuktuss ሹክቱስ



# ዴል ካርኔጊ

t.me/BooksandYou

# ጠብታ ማር

ትርጉም በባሴ ሐብቴና በደምሴ ጽጌ

Scanned by CamScanner

# ዴል ካርኔጊ

«በውስጤ ያሉትን ጥሩ ነገሮች» ሁሉ ያገኘሁት ከመጻሕፍት ነው…»

«በሳይንስ ወይም በቀለም ሰዎች የተጻፉ መጻሕፍን ካላነበብን የሰውን ምንነት ለማወቅ በማንችልበት ዓለም ውስጥ ነው የምንኖረው» ይላል ማክሲም ጐርኪ የመጻሕፍትን ምንነት ሲገልጽ።

«ሰዎች ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን ችሎታ ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል ነው የጻፍኳቸው» ይላሉ ካርኔጊ ስለ መጻሕፍቶቻቸው ሲያወሱ።

እንደ «ጭንቀትን አስወግዶ ስለመኖር» (How to Stop Worrying and Living) የመሳሰሉ መጻሕፍትን ያቀረቡልን ዴል ካርኔጊ በተጨማሪም ስለ መጻሕፍቶቻችው ናቸው» ይላሉ።

በረጅሙ የህይወት ጎዳና ውስጥ የዴል ካርኔጊን ቋሚ ምክሮች በመከተል በሕይወት ውስጥ ተሳክቶላቸው በደስታ የሚኖሩ በመላው አለም ቁጥራቸው በሚሊዮን የሚቆጠር ለመሆኑ የመጻሕፍቶቻቸው በብዙ የአለም ቋንቋዎች መተርጐምና በሚሊዮን ኮፒ መሸጥ በቂ ምስክር ነው። እኛስ ከዴል ካርኔጊ ሥራዎች ምን እናገኝ ይሆን?

ዋ.ን 30.30 ብር

Scanned by CamScanner

20/03/2011

0925036620

# ጠብታ ማር

## በዴል ካርኔጊ

«ከአንድ እንስራ ሀሞት ይልቅ ጠብታ ማር ብዙ ንቦችን ትስባለች::»

t.me/BooksandYou

ትርጉም

በባሴ ሀብቴና በደምሴ ፅጌ

አዲስ አበባ

Scanned by CamScanner

# ማውጫ

1. ምዕራፍ 1

ራስህን ፈልግ፤ ራስህን ሁን፤ አስታውስ በዚች ዓለም አንተን የመሰለ ሌላ ሰው የለም። ........................................11

2. ምዕራፍ 2

ድካምና ጭንቀትን ለማስወገድ የሚረዱ አራት ጥሩ የአሠራር ልምዶች ........................................20

3. ምዕራፍ 3

የድካም ስሜት ለምን እንደሚሰማና እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ........................................26

4. ምዕራፍ 4

ድካምን፣ ጭንቀትንና ቁጭትን የሚያስከትለውን ስልቾታ ስለማስወገድ ........................................32

5. ምዕራፍ 5

ተፈጥሮ ከለገሰችህ ፀጋዎች አንዱን እንኳን በሚሊዮን ብር ትሸጣለህ? ........................................36

6. ምዕራፍ 6

የሞተን ውሻ የሚደበድብ እንደሌለ አስታውስ። ...............41

7. ምዕራፍ 7

ይህንን ብታደርግ ነቀፋ አያሸብርህም ........................44

8. ምዕራፍ 8

ከሰዎች ጋር ለመግባባት የሚረዱ ዋና ዋና መንገዶች ......48

9. ምዕራፍ 9

ይህን ማድረግ የሚችል ሁሉም ይደግፈዋል፤ የማይችል ግን

Scanned by CamScanner

ብቻውን ይቆማል፡፡ ........................................................... 54
10. ምዕራፍ 10
ይህንን ካደረግህ የትም ተቀባይነት ታገኛለህ፡፡ ................ 58
11. ምዕራፍ 11
ከሰዎች ጋር እንዴት በቀላሉ መግባባት እንደሚቻል ........ 63
12. ምዕራፍ 12
ጠላት ለማፍራት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን እንዴት
ማስወገድ እንደሚቻል ................................................ 74
13. ምዕራፍ 13
ወደ ሰዎች የአስተሳሰብ አድማስ የሚመራ ጥርጊያ
መንገድ ..................................................................... 80
14. ምዕራፍ 14
የሶቅራጥስ ሚስጥር፡፡ ................................................ 84
15. ምዕራፍ 15
ሰዎች እንዲተባበሩን ስለማድረግ ................................. 88
16. ምዕራፍ 16
ጥላቻን የሚያስከትል ትችት ስለመሰንዘር ...................... 92
17. ምዕራፍ 17
ስህተትህን እመን ........................................................ 94
18. ምዕራፍ 18
የማስታወስ ችሎታችንን ስለማሻሻል ............................... 97

Scanned by CamScanner

t.me/BooksandYou.

## እንደ መግቢያ

*«በውስጤ ያሉትን ጥሩ ነገሮች ሁሉ ያገኘሁት ከመጻሕፍት ነው... በሳይንስ ወይም በቀለም ሰዎች የተጻፉ መጻሕፍትን ካላነበብን የሰውን ምንነት ለማወቅ በማንችልበት አለም ውስጥ ነው የምንኖረው»* ይላል ማክሲም ጐርኪ የመጻሕፍትን ምንነት ሲገልጽ።

መጻሕፍት ለተለያየ አላማ ይጻፋሉ። ለማስተማር፣ ለማዝናናት፣ ለማስተማርና ለማዝናናት። እውቀትን፣ ታሪክን፣ ባህልን ወግን ሌላውን ቅርጽ ሁሉ ለትውልድ ለማስተላለፍ ይጻፋሉ።

የልብ ወለድ ጽሁፍ አለ፤ ልቦለድ ያልሆነም አለ። ሌላው አገር ስለብዙ ነገር ይጻፋል። እንደአገራችን ሳይሆን ሳይንሱ፣ ታሪኩ፣ ጆግራፊው፣ ስነአእምሮው፣ አንትሮፖሎጂው፣ ምግብ አቀቃቀሉ፣ ልብስ አለባበሱ፣ አተኛኙቱ... ሁሉም በየዘርፉ የተጻፉትን ለመዘርዘር ወረቀትም ጊዜም አይበቃ። ብቻ ስለ ሰው ብዙ ተጽፏል። እየተጻፈም ነው።

በአውሮፓና በአሜሪካ ኑሮህን እንዲህ ኑረው የሚሉ መጻሕፍት በየቀኑ ገበያ ላይ እንደሚውሉ ይወሳል። ስለሥራ፣ ስለጋብቻ፣ ስለወሲብ፣ ከራስና ከሰዎች ጋር ተስማምቶ ስለመኖር የሚጻፉት አያሌ ናቸው።

ባገራችን አልፎ አልፎ ከላይ በተጠቀሱት ርዕሶች አንዳንድ መጻሕፍት እንደመስቀል ወፍ ብቅ ቢሉም ስለኛ በቂ ተጽፏል ለማለት የሚያስደፍር ደረጃ ላይ አልደረስንም። እርግጥ በቅርቡ በዛ ያሉ የልቦለድ ድርሰቶችና እንደ «እሷና እሱን» የመሳሰሉ «መካሪ» መጻሕፍት ታትመው አንባቢ እጅ ደርሰዋል።



Scanned by CamScanner

t.me/BooksandYou

ዝናቸው በመላው አለም የተናኘውና በተለያየ ቋንቋዎች በሚሊዮን ኮፒ ተራብተው የሚሸጡት የዴል ካርኔጊ መጽሐፍት በጥቅሉ በኑሮ ትግል ውስጥ እንዲሳካላችሁ ይህን አድርጉ ያን አታድርጉ እያሉ ከሚያስተምሩና ከሚመክሩ መጻሕፍት ጐራ ነው እሚመደቡ።

«ሰዎች ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን ችሎታ ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል ነው የጻፍኩት» ይላሉ ካርኔጊ ስለመጻሕፎቻቸው ሲያወሱ።

«እውቀት ለኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን አሟልቶ መገኘት ነው» ይላሉ ዶክተር ጆን ሂበን። ለተሳካና ደስተኛ ኑሮ የሚያስፈለጉ ዋና ዋና ነገሮችን ያሳዩና በሚል ነው ይህን ከዴል ካርኔጊ ሥራዎች የተውጣጣ መጽሐፍ ተርጉመን ለማቅረብ የተነሳሳነው።

«የትምህርት አላማ ማወቅ ሳይሆን ማድረግ ነው» ይላል የታወቀው ፈላስፋ ኸርበርት ስፔንሰር። ዴል ካርኔጊም «መጽሐፎቼ ሁሉ የድርጊት መጽሐፎች ናቸው» ይላሉ። እናም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ፍርሃትን ጭንቀትንና አይን አፋራምነትን አስወግደን፣ በራሳችን ተማምነን፣ ከሰዎች ጋር ተግባብተን የምንኖርበትን ጐዳና ነው አብርተው ሊያሳዩን የሚሞክሩት። ሰው የማወቂያ መሳሪያውን እንጂ እውቀትን ይዞ አይደለም ከናቱ ማህፀን የሚወጣው። ሁሉንም ነገር የሚማረው በኋላ ነው። እየኖረ ይማራል፤ እየተማረ ይኖራል። የዴል ካርኔጊ መጽሐፍት ኑሮን እየኖርን እንዴት እንደምንማረው ነው የሚያሳዩን።

ለመሆኑ ዴል ካርኔጊ ራሳቸው ምን አይነት ሰው ነበሩ?

* * *

ዴል ካርኔጊ ከደሀ ቤተሰብ ነበው የተወለደው። የገበሬ ልጅ ነው። በጠዋት ተነስቶ ላሞች ያልባል፤ እንጨት ይቆርጣል፤ አሳማዎችን



Scanned by CamScanner

ይቀልባል። ይህንን ካከናወነ በኋላ ነበር ት/ቤት ለመሄድ የሚዘጋጀው። ይህ አድካሚ ሥራ ዴል ካርኔጊን ከአንዴም ሁለት ሶስት ጊዜ ትምህርቱን እንዲያቋርጥ ምክንያት ሆኖ ነበር።

እንደምንም ኮሌጅ ገባ። ሆኖም አባትየው የኮሌጁን ክፍያ ሊከፍሉለት ባለመቻላቸው በቀን 62 ማይልስ በፈረስ ጀርባ መጓዝ ነበረበት።

ዘወትር ከሚለብሰው ሌላ ቅያሬ ልብስና ጫማ ስላልነበረው ከክፍል ጓደኞቹ ጐን ደፍሮ ለመቆም ጉልበቶቹ ይንቀጠቀጡ ጀመር። ቀስ በቀስ የበታችነት ስሜት እያደረበት መጣ። ወጣቱ ካርኔጊ ፈሪና አይና አፋር፣ በራሱ የማይተማመን ሆነ። ችሎታውን በተግባር ለመተርጐም እስከሚያቅተው ድረስ ወረደ።

ይህንን የተገነዘቡት እናቱ በክርክር ክበቦች ውስጥ እንዲሳተፍ አበክረው ይገፉፉት ነበር። የሳቸውን ምክር ተቀብሎ ሞከረ። አልተሳካለትም። የጓደኞቹ መሳቂያ መሳለቂያ ከመሆን አልፎ በሁለት እግሩ ሊቆም አልቻለም።

በየክበቡ እየገባ ብዙ ከሞከረ፣ ብዙ ከወደቀ በኋላ በመጨረሻው ተሳካለት። ይህ ድል ለተሳካ ኑሮ የሚያስፈልገውን በራስ መተማመንና በሚያደርጋቸው ነገሮች እርግጠኛ መሆንን አስገኘለት። በአንድ አመት ውስጥ የተለያዩ ክርክሮችን አሸንፎ ስም ያለው ተናጋሪም ወጣው።

ይህን ያዩ ተማሪዎችም ከሱ ምክር ለመጠየቅ ይጐርፉ ጀመር። በትግል ያገኘውን እውቀት አካፈላቸው። ብዙዎቹ እንደሱ ተሳካላቸው።

ዴል ካርኔጊ የደረሰበትን የበታችነት ስሜት ለማስወገድ ባደረገው ትግል ሀሳቡን ለአንድ ወይም ለብዙ አድማጮች ለማስተላለፍ የሚያስፈልገው በራስ መተማመን መሆኑን ተረዳ። በዚያም አላቆመ።



Scanned by CamScanner

t.me/BooksandYou

በራስ መተማመን ሰውን በየትም ቦታ ከሌሎች እኩል በሁለት እግሩ የሚያቆመው መሆኑንም ተገንዝቧል::

ሰዎች እርስ በርሳቸው· የሚያደርጉትን ግንኙነት ለመረዳት መምከር ብቻ ሳይሆን መመሪያ የሚሆኑ መጽሐፍትን ማዘጋጀት ጠ ቃሚ መሆኑን በመገንዘቡ How to Win Friends and Influence People, How to Stop Worrying and Start Living, How to Develop Self-confidence and Influence People by Public Speaking የተሰኙ መጻሕፍትን ያቀረበ ሲሆን እነዚህ መጽሐፍት ዛሬ በመላው አለም በተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉመው በሚሊዮን ኮፒዎች ተሰራጭተዋል::



Scanned by CamScanner

## እንደመደምደሚያ፡-

በትርጉም ሥራ ውስጥ የተለያዩ መጻሕፍት በተለያዩ መንገድ ነው የሚተረጐሙት:: ተመሳሳይ መጽሐፍትንም በተለያየ መንገድ መተርጐም እንደሚቻል በሙያው የተሰማሩ ጠበብት አንድ ሁለት ብለው ይናገራሉ::

ይሄ ከላይ እንዳልነው መካሪ፣ አስተማሪ፣ መሪ መጽሐፍ ነው:: ህሳብን ግልጽ በሆነ መንገድ ለሌላው ማቀበል ነው አላማው:: ይህን ትርጉም ስንሰራ በሀሳቡ ላይ ነው ያተኮርነው:: ይህ ሀሳብ በኛ ቋንቋ ለኛ ሰዎች እንዴት ይደርሳል ነበር ጭንቀታችን:: ስለዚህ ለኛ አይሆኑም ያልናቸውን ምዕራፎች፣ አንቀጾችና አረፍተ ነገሮች እንደልባችን ቆርጠናቸዋል:: አሳጥረናቸዋልም::

ምናልባት የዴል ካርኔጊን ሥራዎች በተጻፉበት ቋንቋ ያነበበ የኛን «ትርጉም» ሲያይ እንዴ! ብሎ ይገረም ወይም ይደነግጥ ይሆናል:: ለሱ የዴል ካርኔጊ ዋና ዋና ህሳቦች አሉ:: ሌሎቹን ትተናቸዋልና አይዞህ! ለፍሬ ካላቸው ያሉት ይበቃሉ ነው መልሳችን::

ትርጉሙን ስንሰራ የተጠቀምንበት የዴል ካርኔጊ ሥራዎች በከፊል ተጠራቅመው ከሚገኙበት How to Enjoy Your Life and Your Job የተሰኘው መጽሐፍ ነው:: ሆኖም በሱ አልተወሰንም:: ቀድሞ እንዳልነው ከሱ ውስጥ የፈለግነውን ወስደን ያልፈለግነውን ስንጥል፣ በዚያ ጥራዝ ውስጥ ካልታቀፈው መጽሐፋቸውም ሌሎች ምዕራፎችን አክለንበታል:: ስለዚህ ይህ መጽሐፍ የሌላውም፣ የኛም ምርጫ የታከለበት የዴል ካርኔጊ ምርጥ ስራዎች ስብስብ ነው ብለን እናስባለን::

ተርጓሚዎቹ



Scanned by CamScanner

pdf by @shuktuss ሹክቱስ
t.me/BooksandYou

# ክፍል አንድ

## የመንፈስ እረፍትና ደስታ ለማግኘት የሚረዱ ሰባት ማንገዶች

Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ 1

## ራስህን ፈልግ ራስህን ሁን፣ አስታውስ በዚች አለም አንተን የመሰለ ሌላ ሰው የለም።

ስሜን ካሮላይና ከምትኖረው ከወ/ሮ ኤዴት አልረድ የተላከ አንድ ደብዳቤ አለኝ። በደብዳቤውም ውስጥ እንዲህ ትላለች።

«በልጅነቴ በጣም ስሱና አይን አፋር ነበርኩ። ወፍራም ከመሆኔም በላይ ጉንጮቼ ደግሞ ከዚያ የበለጠ ወፍራም ያስመስሉኝ ነበር። እናቴ ዘመናዊ አስተሳሰብ ስላልነበራት ቆንጆ ልብስ መልበስ ሞኝነት ነው ብላ ታስብ ነበር። አዘውትራም እንዲህ ትላለች፣ 'ሰፊ ይለበሳል፣ ጠባብ ይቀደዳል' ስለዚህ ልብሶቼ ሁሉ በልኬ የተሰሩ አልነበሩም። ሰፋፊ ነበሩ። ፓርቲ የሚባል ነገር ሂጄ አላውቅም። ተዝናንቼም አላውቅም። ት/ቤትም ሆነ ከክፍል ውጪ ከልጆች ጋር አልጫወትም ነበር። በአትሌቲክስ እንኳን የተሳተፍኩባቸውን ቀኖች አላስታውስም። በጣም የማሳዝን አይን አፋር ልጅ ነበርኩ። ከሰው ሁሉ የተለየሁና ማንም የማይፈልገኝ ይመስለኝ ነበር። ካደግሁ በኋላም በዕድሜ በብዙ ዓመታት የሚበልጠኝ ሰው አገባሁ። ግን አልተለወጥኩም።

የባሌ ወገኖች ኩሩና በራሳቸው የሚተማመኑ ነበሩ። እኔ ልሆን የሚገባኝን ግን ያልሆንኩትን ሁሉ ነበሩ። በተቻለኝ መጠን እንደነሱ ለመሆን ሞከርኩ፣ አልቻልኩም። እኔን ከሰመጥኩበት የፍርሀትና የበታችነት ስሜት ለማውጣት ያላደረጉት ጥረት አልነበረም። ሆኖም ይህ ጥረታቸው ይበልጡኑ እንድሸማቀቅና ይብልጥ የበታችነት እንዲሰማኝ አደረገኝ።



Scanned by CamScanner

የባሰ ነጭናጯና ርብትብት ሆንኩ፣ ጓደኞቼን ሁሉ ሸሸሁ:: እየቆየሁ ስሄድማ በር በተንኳኳ ቁጥር እበረግግ ጀመር:: ውዳቂ ሰው ሆኜ ተገኘሁ:: እንደዛ መሆኤንም ተገንዝቤው ነበር:: በጣም የሚያስፈራኝ ግን ባሌ አንድ ቀን ያውቅብኛል የሚለው ነበር:: ስለዚህም ውጪ በወጣን ቁጥር ደስተኛና ደፋር መስዬ ለመታየት እሞክራለሁ:: ደስተኛ መስዬ መታየቱን አበዛው እንደነበርም አውቀዋለሁ:: ስለሆነም ይህ ትዝ ባለኝ ቁጥር ለረጅም ቀናት እጨነቅ ጀመር:: በመጨረሻ መከፋቱ እየበዛብኝ ሄደና በዚህ ሁኔታ መኖሬም ዋጋ እንደሌለው ስገነዘብ ራሴን ለማጥፋት ማሰብ ጀመርኩ::»

ታዲያ የዚችን አሳዛኝ ሴት ሕይወት ለመለወጥ የሚችል ምን ነገር ተገኘ? ሕይወቷን የለወጠው ባጋጣሚ የተነገረ አስተያየት ነበረ::

የወ/ሮ አልረድ ደብዳቤ እንዲህ እያለ ይቀጥላል::

«ባጋጣሚ የተነገረ አስተያየት ሕይወቴን ቀየረው:: አንድ ቀን አማቴ ልጆቻቸውን እንዴት እንዳሳደጉ ሲናገሩ 'የሆነው ቢሆን ልጆቼ ራሳቸውን እንዲሆኑ እየደጋገምኩ እመክራቸው ነበር' ሲሉ ሰማኋቸው፣ ራሳቸውን እንዲሆኑ:: ይህ አስተያየት ነበር መሳ ህይወቴን የለወጠው:: እንዲህ ብለው ሲናገሩ ይህን ሁሉ ስቃይ ያመጣብኝ ሌላውን ለመሆን (ሌሎችን ለመምሰል) እጥር ስለነበር እንደሆነ ተገለጸልኝ::

በአንድ ቀን አዳር ተለወጥኩ! ራሴን መሆን ጀመርኩ:: ራሴን ለማጥናትም ሞከርኩ:: ምን ዓይነት ሰው እንደሆንኩ ለማወቅ



Scanned by CamScanner

t.me/BooksandYou



ጣርኩ:: በሚቻለኝ መጠን ስለልብስ ቀለሞችና ቅዶች (ፋሽኖች) ለማጥናት ሞከርኩ:: ከዚያ በኋላም የሚስማማኝን ዓይነት መልበስ ጀመርኩ:: ከዚያም በአንድ የሴቶች ማኅበር ውስጥ አባል ሆንኩ:: እነሱም አንድ ውይይት እንድመራ ፕሮግራም ሰጡኝ:: ይህም ፕሮግራም የነበረኝን ፍርሃት ሁሉ እንዳስወግድ ረዳኝ:: እንዲህ የሆነው ግን በአንዴ አልነበረም:: በተናገርኩ ቁጥር ድፍረት እያገኘሁ መጣሁ:: ዛሬ ግን በሕልሜ እንኳ ይቻላል ብዬ የማላስበውን ያህል ደስታ እያገኘሁ ነው::

ልጆቼንም ያሳደግኋቸው ከዚያ መራራ ኑሮዬ የቀሰምኩትን ልምድ እያስተማርኩ ነው:: እንዲህም እላቸው ነበር:: 'የሆነው ቢሆን ምን ጊዜም ራሳችሁን ሁኑ፤ ሌላውን ለመምሰል አትሞክሩ'::»

«እራስን ለመሆን የሚደረገው ጥረት ረጅም ታሪክ ያለውና በሁሉም ሰው ውስጥ የሚገኝ ነው» ይላሉ ዶክተር ጃም ጉርደን አልኩ ይህ ሌሎችን ለመምሰል የመፈለግ ዝንባሌ በአብዛኛው ለአእምሮ ህመምና ጭንቀት መነሻ ነው::

ስለ ሕፃናት አስተዳደግ አስራ ሶስት መጻሐፍትና በሺህ የሚቆጠሩ የጋዜጣ ጽሁፎችን ያቀረቡት አንጄሎ ፓተር የተባሉ ሊቅ «በአዕምሮም በአካልም ራሱን መሆን ሲችል ሌሎችን ለመምሰል እንደሚመኝ ሰው ጭንቀት የሚበዛበት የለም» ይላሉ::

ይህ ሌሎችን የመምሰል ፍላጐት በተለይ ሆሊ ውድ በተባለው የአሜሪካ የፊልም መሥሪያ ከተማ ውስጥ ጐልቶ ይታያል:: ከታወቁት የሆሊውድ የፊልም አዘጋጆች አንዱ የሆኑት አቶ ሳም ውድ ወጣት



Scanned by CamScanner

ተዋንያንን በሚያሰሩበት ጊዜ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥርባቸው ይኸው ሌሎችን የመምሰል ፍላጐት መሆኑን ይገልጻሉ።

አቶ ሳም ውድ አስተያየታቸውን በመቀጠል፣ «ወጣት ተዋንያን የላና ተርነር ቅጅ ወይም የክላርክ ጌብልስ የቅጅ ቅጅ ሊሆኑ ይፈልጋሉ» ካሉ በኋላ፤ እሳቸው ለወጣት ተዋንያኑ እንዲህ እያሉ ደጋግመው እንደሚነግሯቸው ገልጸዋል።

«ተመልካቹ የነላና ተርነርግ ችሎታ አይቶታል፤ ጠግቦታል። ከእናንተ የሚጠብቀው አዲስ ነገር ነው (ሌላ ነገር) ነው።»

አቶ ሳም ውድ በፊልም አዘጋጅነት ሙያ ተሰማርተው በመላው አለም ተደናቂ የሆኑ ፊልሞችን አዘጋጅ ከመሆናቸውም በፊት በእርስት አሻሻጭነት ሙያ ላይ ተሰማርተው ነበር። እዚያም ሆነው በራሳቸው የሚተማመኑ ወጣት አሻሻጮችን (Salesmen) ለማፍራት እንደበቁ ይናገራሉ። አስተያየታቸውን በመቀጠል፣ «ይህ ራስን የመሆን ነገር» በፊልም አለም ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሥራ መስክ አስፈላጊ እንደሆነ ይመሰክራሉ። «በማስመሰል ምንም ፍሬ ያለው ነገር መስራት አይቻልም።» ሳም ውድ በማከል፣ «ከልምድ እንዳገኘሁት ሌሎችን ለመምሰል ከሚሞክሩ ሰዎች ጋር ከመሥራት አለመሥራቱ ይመረጣል።»

በቅርቡ የአንድ ዘይት ፋብሪካ ፐርሶኔል የሆኑትን አቶ ጳውሎስ ቦይንተንን «ሰዎች ለመቀጠር ሲጠይቁ የሚፈጽሙት ትልቁ ስህተት ምንድነው?» ብዬ ጠይቄያቸው ነበር። እኒህ ሰው ከዚህ በፊት ከ60,000 በላይ ለሚሆኑ ሥራ ፈላጊዎች የቃለ መጠይቅ ፈተና የሰጡ፣ ይህንንም በመመርኮዝ «ሥራ ለማግኘት የሚረዱ ስድስት መንገዶች (Six Ways to Get a Job)» የሚል መጽሐፍ የጻፉ ነበሩና እንዲህ ሲሉ መለሱልኝ፤



Scanned by CamScanner

«ሥራ ፈላጊዎች የሚፈጽሙት ትልቁ ስህተት ራሳቸውን ላለመሆን የሚያደርጉት ሙከራ ነው:: አንድ ጥያቄ ሲጠየቁ ምን ጊዜም ቢሆን ለጥያቄው መልስ ይሆናል ብለው ያመኑበትን ሳይሆን አንተ ትፈልገዋለህ ብለው ያመኑበትን መልስ ይነግሩሃል::»

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ሌሎችን ለመምሰል የመሞከሩ ጉዳይ የሚያዋጣ ነገር አይደለም:: ምክንያቱም ማንም ቀጣሪ አስመሳይ ሠራተኛ አይፈልግም:: እስቲ አስቡት የውሸት ገንዘብ የሚፈልግ ሰው አለ?

አንዲት በመልኳ የምታፍር ዘፋኝ ለመሆን የምትመኝ ልጅ ነበረች:: በተለይ የሚያሳፍሯት ሰፊው አፏና ገጣጣ ጥርሷ ነበሩ:: ልጅቷ ተሳካላትና ሕዝብ ፊት ቀርባ ለመዝፈን በቃች ነገር ግን በምትዘፍንበት ጊዜ አፏን ለማጥበብና ጥርሷን ለመከለል ስለሞከረች አድማጮቿን ልትስብ አልቻለችም:: እንዲያውም አብዛኞቹ ሁኔታዋን ስለተረዱ ሳቁባት:: በዚህ ጊዜ ዘፋኝ የመሆን ተስፋዋ መንምኖ ታያት:: ከአድማጩ መካከል በዚያ ወቅት ሁኔታዋን የተገነዘበና ችሎታ እንዳላት ያመነ አንድ ሰው ጠርቶ እንዲህ አላት፤

«አየሽው ስትጫወቺ እመለከትሽ ነበር፤ ልትደብቂው የሞከርሽውን ነገር ደግሞ አውቄዋለሁ:: በጥርስሽ ታፍሪያለሽ አይደለም?»

ይህን ስትሰማ ልጅቷ አፈረች:: ሰውዬው ግን ንግግሩን በመቀጠል፤ «ምን ልታደርጊው ትችያለሽ? ገጣጣነት ወንጀል ነው እንዴ? በፍጹም አይደለም እና በምንም ዓይነት ጥርሶችሽን ለመደበቅ አትሞክሪ:: ለወደፊቱ ተዝናንተሽ ዝፈኚ፤ አትፈሪ:: አለማፈርሽን ሲያይ ተመልካቹ ይወድሻል:: በዚያም ላይ ማን ያውቃል እነኝህ ዛሬ



Scanned by CamScanner

የምታፍሪባቸው ጥርሶችሽ ነገ ብዙ ሀብት ያስገኙልሽ ይሆናል::»

ይቺ እንዲህ የተባለችው ልጅ ካስ ዳሊ ነበረች:: ዳሊ የሰውዬውን ምክር ከተቀበለች በኋላ ጥርሶቿን ረሳች:: ተመልካቹን ብቻ ማሰብ ጀመረች:: አፏን ከፈት አድርጋ ከልቧ ስትዘፍን ተመልካቹም ተማረከላት:: የፊልምና የሬዲዮም ኮከብ ተዋናይና ዘፋኝ ሆነች:: ዛሬ ወጣት ተዋንያን ዳሊን ለመምሰል ሙከራ ያደርጋሉ::

ታዋቂው ፈላስፋ ዊሊያም ጀምስ ራሳቸውን መሆን ስላልቻሉ ሰዎች ሲያወሳ አብዛኛው ሰው ካለው ችሎታ ከመቶ አስሩን እጅ እንደሚጠቀምበት ተናግሯል:: እራስን ለመሆን ካለመሞከር የተነሳ ካለን ችሎታ ዘጠና በመቶው ባክኖ ይቀራል ማለት ነው::

ይኸውልህ አንተም እኔም ይህን ያህል ችሎታ አለን:: ስለዚህ እንደሌሎች ባለመሆናችን ስንጨነቅ ወርቃማ ጊዜያችንን አናጥፋ::

ብታውቀው በዚች አለም ላይ የተለየህ ፍጡር ነህ:: ከዚህ በፊት ዘመን ከተፈጠረ ጀምሮ አንተን የመሰለ ሌላ ሰው ኖሮ አያውቅም:: ወደፊትም በሚመጡት ዘመናት ሁሉ አንተን የሚመስል ሰው አይኖርም:: ይህ በሳይንስም ተረጋግጧል:: አንተ ስትፀነስ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የወንዴ ዘሮች ወደ እናትህ ማህፀን ውስጥ ይገባሉ:: አንተን ያስገኘው አንዱ ነው:: ከቀሩት መካከል አንተን ያስገኘውን የመሰለ የወንዴ ዘር የለም:: እኒያ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የወንዴ ዘሮች ማስፀነስ ቢችሉና እናትህ ያን ያህል ልጆች አርግዘው ለመውለድ የሚችሉ ቢሆን እንኳ አንተን የመሰለ ሌላ ልጅ ሊወልዱ አይችሉም::

ስለዚህ ነገር እርግጠኛ ለመሆን ከፈልግህ የሄሬዲቲና የጄኔቲክስ መጻሕፍትን መርምር::

ራስን ስለመሆን እርግጠኛ ሁኜ ለመናገር እችላለሁ:: ምክንያቱም



Scanned by CamScanner

ይህ ነገር ጠልቆ ስለሚሰማኝና ኬመራራ ልምድ ያተረፍኩት ስለሆነ ነው:: በምሳሌ ለማስረዳት ያህል ከሚዙሪ የእርሻ ቦታ ተነስቼ ለመጀመሪያ ጊዜ ኒውዮርክ እንደገባሁ ተዋናይ የመሆን ትልቅ ፍላጐት ስለነበረኝ በአሜሪካ የቲያትር ጥበብ አካዳሚ ተመዘገብሁ:: ተዋናይ የመሆን ፍላጐት ያደረብኝ በዚያን ጊዜ ታዋቂ ተዋናይ የነበሩትን እነ ጆን ድሩ፣ ዋልተርሀም፣ ደን እቴክ ስኪነር በአጭር ጊዜ በመታወቃቸውና በያኔው የኔ ግምትም ይህ ሥራ በቀላሉ ዝነኛ ሊያደርገኝ የሚችል መስሎ ስለተሰማኝ ነው:: እንዲያውም ለመታወቅ የሚፈልጉ ሰዎች ይቺን ቀላል መንገድ እንዴት ሊደርሱባት አልቻሉም እያልኩ እደነቅ ነበር:: ከላይ የጠቀስኳቸውን ታዋቂ ተዋንያን አንድ በአንድ በመቅዳትና የሁሉንም ችሎታ በማጣመር ከነሱ በላይ ሆኜ ለመታየት እሞክር ነበር:: ይህንን ነገር አሁን ሳስበው ያስቀኛል:: እኔ እኔን እንጂ ሌላ ሰው ልሆን እንደማልችል እስክረዳው ድረስ ሰዎችን ለመምሰል በመሞከር ከሕይወቴ አያሌ አመታትን አሳልፌአለሁ::

ያ አሳዛኝ ልምድ የመጨረሻ ትምህርት ሊሆነኝ በተገባ ነበር:: ነገር ግን በቀላሉ የማይገባኝ ሰው ስለነበርኩ ትምህርት አልሆነኝም:: እንደገና ሀ ብዬ መጀመር ነበረብኝ:: ከአያሌ አመታት በኋላ በሕዝብ ፊት ደፍሮ ስለመናገር የሚገልጽ እስከ ዛሬ ድረስ ተጽፎ የማያውቅ ወደር የሌለው መጽሐፍ ለመጻፍ ተነሳሁ:: ይህን መጽሐፍ ስለመድረስ የነበረኝ አስተያየት በፊት ተዋናይ ለመሆን የነበረኝን የተሳሳተ አስተያየት ይመስላል:: ማለትም በዚህ ርዕስ ላይ ከጻፉ ደራሲያን ሁሉ ሀሳብ ወስጄ አንድ ሁሉንም ነገር ያጠቃለለ መጽሐፍ ለመድረስ አሰቤ ነበር ማለት ነው:: በርከት ያሉ መጽሐፍት በማንበብ ሀሳቦቻቸውን እያጠራቀምኩ አዲስ በምጽፈው መጽሐፍ ውስጥ



Scanned by CamScanner

ማጠናቀር ጀመርኩ:: ሆኖም እንደገና የተሳሳትኩ መሆኔ ተገለጸልኝ:: በድጋሚ በመሞኘቴ ሳቅሁ:: ይሄ የሀሳቦች ድሪቶ ገለባና የማይስብ በመሆኑ አንድም ሰው በትዕግስት ሊያነበው የሚችል አልነበረም:: ሆኖም አመት የለፋሁበትን ጽሁፍ ቀዳድጄ ጥዬ እንደገና በአዲስ መልክ መሥራት ጀመርኩ:: ለራሴም እንዲህ አልኩት፤

«ስህተቱንም ችሎታውንም እንዳለ ተቀብለህ ዴል ካርኔጊን መሆን አለብህ፤ ሌላ ሰው ልትሆን አትችልምና::» ስለዚህም ሌሎችን ለመሆን መሞከሬን አቆምኩና ሸንጬን ገትሬ ከመጀመሪያው አንስቶ ሳደርገው ይገባኝ የነበረውን ነገር በአዲስ መንፈስ ተነስቼ ሠራሁ:: በሕዝብ ፊትም ደፍሮ ስለመናገር የሚያስተምር መጽሐፍ ደረስኩ:: መጽሐፉም የተመሰረተው በራሴ ልምዶች፣ በተመለከትኳቸው፣ ባመንኩባቸው ነገሮች ላይ ብቻ ነበር:: ከዚህ ጽሑፍ የእንግሊዝኛ ስነ ጽሁፍ ሊቅ የነበሩት ሰር ዋልተር ራሊ ስለዚህ ጉዳይ የደረሱበትን ዕውቀት አገኘሁት:: ሰር ዋልተር ስለጻፉት ነገር ሲናገሩ «እንደ ሼክስፒር አልጽፍም፤ እንደ እኔ እንጂ» ብለው ነበር::

## ራስህን ሁን

እነ ቻርሊ ቻፕሊን፣ እነ ዊል ሮጀርስ፣ እነ ሜሪ ማርጋሬት፣ መክብራይድ፣ እነ ጆን አትሪና ሌሎችም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ታላላቅ ሰዎች ራስን የመሆንን ነገር የተማሩት ከብዙ ጊዜ ጥረትና ሙከራ በኋላ ነው:: ይህንን ጉዳይ ደጋግሜ ያመጣሁት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን ስለማውቅ ነው::

ቻርሊ ቻፕሊን ፊልም መሥራት እንደጀመረ አዘጋጁ አንድ የታወቀ የጀርመን ኮሜዲያን እያስመሰለ እንዲሠራ ደጋግሞ ይነግረው ነበር:: ሆኖም ቻርሊ ቻፕሊን በራሱ መንገድ መሥራት እስኪጀምር



Scanned by CamScanner

t.me/BooksandYou



የተሳካለት ኮሜዲያን ሊሆን አልቻለም ነበር።

ቦብ ሆፕም ተመሳሳይ ችግር ደርሶበታል። ምንም እንኳን ለአያሌ አመታት በዘፋኝነትና በዳንስ ሥራ ላይ ቢቆይም ራሱን አውቆ በራሱ እስኪሰራ ድረስ ታዋቂነትም አላገኘም ነበር።

ጂን አትሪ ከቴክሳስ ክ/ሀገር የመጣ ቢሆንም እሱ ግን የቴክሳስን የአነጋገር ቅላጼና አለባበስ ትቶ እንደ(የ) ኒው ዮርክ ሰው ለመልበስና ለመናገር ሲሞክር መሳቂያ መሳለቂያ ሆኖ ነበር። ነገር ግን ባንጆ የተባለውን ክራር መሰል የሙዚቃ መሳሪያ እየመታ የቴክሳስን የእረኞች ዘፈን ሲዘፍንና ይህንንም ሥራዬ ብሎ ሲይዘው የተዋጣለትና በመላው አለም የታወቀ ዘፋኝ ሆነ፤ በፊልምም በሬዲዮም።

በዚች ምድር ላይ አንተን የሚመስል ሰው የለም። በዚህም ደስ ሊልህ ይገባል። ተፈጥሮ ባደለችህ ደስታ ጸጋ ተጠቀምበት። ሁሉም ነገር የሚወጣው ከራስህ ነውና ማዜም የምትችለው ያንተ የሆነውን ብቻ ነው። መሳልም የምትችለው ያንተ የሆነውን ብቻ ነው። አካባቢህ፣ ልምድህ፣ ከዘር የወረስከው ባህርይ ያደረጉህን ብቻ መሆን አለብህ። ለማንኛውም የራስህ የሆነውን ነገር አዳብረው። በሕይወት ጨዋታ ውስጥም የራስህ የሆነችውን ትንሽ የሙዚቃ መሳሪያ ተጫወት።

የመንፈስ ዕረፍትንና ደስታን አዳብሮ ከጭንቀት ነፃ ለመሆን የሚከተለውን መመሪያ አስተውል።

ሌሎችን ለመምሰል አንሞክር፤

ራሳችንን እንፈልግ!

ራሳችንን እንሁን!



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ 2

## ድካምና ጭንቀትን ለማስወገድ የሚረዱ አራት ጥሩ የአሠራር ልምዶች

1ኛ. <u>በወቅቱ ከምትሠራው ሥራ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን ወረቀቶች ሁሉ ከጠረጴዛህ ላይ አስወግድ</u>

በችካጐ የአንድ ባቡር ጣቢያ ፕሬዚደንት የሆኑት ሮላንድ ዊሊያምስ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩ፤

*«በጠረጴዛው ላይ ብዙ ወረቀቶች የከመረ ሰው ለጊዜው አስፈላጊ የሆኑትን ብቻ ትቶ ሌሎችን ቢያነሳ ሥራው የተቃና ይሆንለታል:: ይህንንም መልካም የቤት አያያዝ እለዋለሁ:: ሥራን ለማቃናትም የመጀመሪያው እርምጃ ነው እላለሁ»* ይላሉ::

ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ በሚገኘው የኮንግሬስ ቤተ መጻሕፍት ኮርኒስ ላይ በታዋቂው እንግሊዛዊ ገጣሚ አሌክሳንደር ፓፕ የተጻፉ አምስት ቃላት ይታያሉ፤ እንደዚህ የሚሉ:-

*«የገነት የመጀመሪያው ሕግ ሥርዓት ነው::»* *ሥርዓት የሥራም የመጀመሪያው ሕግ መሆን ይገባዋል:: ግን ይሆን? አይደለም::* የአብዛኛው ሠራተኛ ጠረጴዛ ለረጅም ጊዜ ተነክተው በማያውቁ ወረቀቶች የተሞላ ነው:: እንዲያውም ይግረማችሁ አንድ በኒው ኦርሊንስ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ጋዜጣ አዘጋጅ እንዳወሳኝ ጸሐፊው አንድ ቀን ከጠረጴዛዎቹ አንዱን ስታጸዳ ለሁለት ዓመታት ያህል ጠ ፍቶባቸው የነበረውን አንድ የጽሕፈት መኪና እንዳገኘች ነግሮኛል::

መልስ ባልተሰጣቸው ደብዳቤዎች፤ ባልታዩ ሪፖርቶች የግል



Scanned by CamScanner

ማስታወሻዎች የተሟላ ጠረጴዛን ማየት ራሱ በሠራተኛው ላይ መደናገርን፣ ውጥረትንና ጭንቀትን ያሳድራል፡፡ የነዚህ ወረቀቶች መከመር በሠርቹው አያልቅ ጭንቀት ውስጥ ስለሚከተን ውጥረት እና ድካምን ብቻ ሳይሆን የደም ብዛትን፣ የልብ ድካምንና የጨጓራ በሽታን ሊያስከትል ይችላል፡፡

ዶክተር ዊሊያም ሳድለር የተባሉት ዝነኛ የአዕምሮ ሀኪም በሳቸው ይታከም ስለበረ የአንድ ኩባንያ ስራ አስኪያጅ ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ፡፡ «ሰውዬው ለህክመና ሲመጣ የውጥረት የመሸበርና የመጨነቅ ስሜት ይታይበት ነበር፡፡ ወደ እብደትም እያመራ እንደነበር ቢረዳውም ሥራውንም ለመልቀቅ ግን ዝግጁ አልነበረም፡፡ ከዚያ በፊት የሀኪም ዕርዳታ እንደሚያስፈልገው ያውቅ ነበር፡፡»

ዶክተር ሳድለር እንዲህ ይላሉ፣ «ሰውዬው ታሪኩን እየነገረኝ ሳለ ስልክ ተደወለልኝ፡፡ የተፈለግሁት ከምሠራበት ሆስፒታል ነበር፡፡ ሆኖም የሰውዬውን ጉዳይ አንጠልጥሎ ከመተው ይልቅ አንድ እልባት ማስያዝ እንደሚገባኝ ወሰንኩ፡፡ ይህ ደግሞ ልምዴ ነው፡፡ ምን ጊዜም አንድ ነገር ከጀመርኩ ሳልጨርሰው አልተወውም፡፡ መነጋገሪያውን እንዳስቀመጠኩ በድጋሚ ስልኩ ጮኸ፡፡ አሁንም በጣም አስቸኳይ ነበር፡፡ ቢሆንም መልዕክቱን ከተነጋገርንበት በኋላ መልሼ ዘጋሁትና ሰውዬውን ማነጋገር ጀመርኩ፡፡ በጣም ስለታመመ አንድ ሰው ሁኔታ ሊያማክረኝ የመጣ የሥራ ባልደረባዬ ለሶስተኛ ጊዜ ከሰውዬው ጋር የማደርገውን ንግግር አቋረጠኝ፡፡ ከሱ ጋር ከጨረስኩ በኋላ ወደ ታካሚው ተመልሼ ስላስጠበቅሁት ይቅርታ መጠየቅ ስጀምር በደስታ ተቀበለኝ፡፡ በፊቱ ላይ ሲመጣ ከነበረው የተለየ ሁኔታ ይታይበት ነበር፡፡



Scanned by CamScanner

'ዶክተር ይቅርታ አይጠይቁኝ:: ባለፉት አሥር ደቂቃዎች ውስጥ የኔ ችግር ምን እንደሆነ የተረዳሁት ይመስለኛል:: በቀጥታ ወደ ቢሮዬ ተመልሼ የአሰራር ልምዴን አስተካክላለሁ... ከመሄዴ በፊት ግን የጠረጴዛዎን ኪሶች ለማየት ይፈቅዱልኛል?'»

ዶክተር ሳድለር የጠረጴዛቸውን ኪሶች ከፈቱ፣ ሁሉም ባዶ ነበሩ:: ከጽሕፈት መሳሪያዎች በስተቀር::

«እስቲ ይንገሩኝ ዶክተር» አለ ታካሚው:: «ያላለቀላቸውን ወረቀቶች የት ነው የሚያስቀምጧቸው?»

«እጨርሳቸዋለሁ::»

«መልስ ያልሰጡባቸው ደብዳቤዎችስ የት ያስቀምጧቸዋል?»

«መልስ እሰጥባቸዋልሁ::» አሉና ቀጥለውም «የኔ መመሪያ አንድ ደብዳቤ መልስ ሳይሰጥበት መቀመጥ የለበትም የሚል ነው:: ስለዚህም ደብዳቤው እንደደረሰኝ መልሱን ለጸሐፊዎ እየነገርኩ አስጽፈዋልሁ::» ከስድስት ሳምንታት በኋላ ይኸው የኩባንያ ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ሳድለርን ወደ ቢሮው እንዲመጡ ጋበዛቸው:: እሱም ጠረጴዛውም ተለውጠው ነበር:: የጠረጴዛውን ኪሶች ከፍቶ አንድም ያልተከናወነ ሥራ እንደሌለ ለዶክተር ሳድለር አሳያቸው::

«ከስድስት ሳምንታት በፊት በሁለት ቢሮዎች ውስጥ ሶስት የተለያዩ ጠረጴዛዎች ነበሩኝ:: በሁሉም ላይ ያላለቁ ዶሴዎች ተከምረው ሳይ ሥራው የሚውጠኝ መስሎ ይሰማኝ ነበር:: እርስዎ ጋ ደርሼ ከተመለስኩ በኋላ አንድ መኪና ሙሉ ሪፖርቶችንና አሮጌ ወረቀቶችን ጠርጌ አወጣሁ:: ዛሬ በአንድ ጠረጴዛ ላይ ብቻ እሠራለሁ:: ማንኛውንም ሥራ እኔ ጋ እንደደረሰ አከናውነዋለሁ:: ይኸውልህ! ዛሬ የተወዘፈ ሥራ ባለመኖሩ የዱሮው ውጥረትና ጭንቀት ለቆኛል፤ ፈጽሞም



Scanned by CamScanner

ድኛለሁ። በጤናዬ በኩል ምንም ዓይነት ችግር የለብኝም።»

የቀድሞው የአሜሪካ የፍትና ሚኒስትር የነበሩት ቻርልስ ኢባንስ ሂውዝ እንዲህ ብለዋል። «የሥራ ብዛት ሰዎችን አይገድላቸውም። የሚገድላቸው በችሎታቸው አለመጠቀማቸውና ጭንቀታቸው እንጂ።»

2ኛ. ሥራህን እንደ አስፈላጊነቱ በቅደም ተከተል አከናውን

የከተሞች አገልግሎት ሰጪ ኩባንያ በመባል የታወቀውን ድርጅት መሥራች የሆኑት ሄንሪ ዶኸርቴ የፈለጉትን ያህል ደሞዝ ቢከፍሉም ከሠራተኛው ሊያገናኛቸው ያልቻሉት ሁለት ነገሮች እንዳሉ ይናገራሉ። እነሱም፡-

ሀ. የማመዛዘን ችሎታ

ለ. ሥራን እንደየአስፈላጊነቱ በቅደም ተከተል የማከናወን ችሎታ ናቸው።

ቻርለስ ሉክማን የተባለ ከምንም ተነስቶ በአሥራ ሁለት አመታት ውስጥ የአንድ ትልቅ ኩባንያ ፕሬዚደንት በመሆን በአመት በመቶ ሺህ ብር የሚቆጠር ገንዘብ ለማጠራቀም የበቃ ወጣት እዚህ ደረጃ ላይ እንዴት እንደደረሰ ሲናገር ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሄንሪ ዶኸርቴ ለማግኘት አስቸጋሪ ያሏቸውን ችሎታዎች ለመጠቀም በመቻሉ መሆኑን ይናገራል። በአሜሪካ ውስጥ ከሚገኙት የተሳካላቸው የኢንሹራንስ አሻሻጮች አንዱ የሆነው ፍራንክ ቤት ማር የነገ ሥራውን ዛሬ እንደሚያቅድ ማለትም በነገው ቀን ስንት ኢንሹራንስ ሸጦ መዋል እንዳለበት የሚተልም ሰው ነበር። ያቀደውን ያህል ኢንሹራንስ ካልሸጠ ቀሪውን በነገው ሽያጭ ላይ አክሎ ለመሸጥ ያቅድ ነበር።

ከረጅም የሥራ ልምድ እንደተረዳሁት ሁልጊዜ ሥራዎችን ሁሉ እንደ አስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል ለማከናወን ያዳግት ይሆናል፤



Scanned by CamScanner

ሆኖም አይቻልም ብሎ ከማስቀመጥ በመጀመሪያ ሊሠራ የሚገባውን በቅድሚያ ለማከናወን ማቀድ እንደሚያስፈልግ አውቃለሁ::

ዝነኛው የተውኔት ደራሲ በርናንድ ሾው ነገሮችን እንደየአስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል መሥራትን መመሪያ ባያደርገው ኖሮ ታዋቂ ደራሲ ሳይሆን የባንክ ቤት ገንዘብ ያዥ ሆኖ ይቀር ነበር:: በየቀኑ አምስት ገጾችን የመጻፍ ቋሚ ዕቅድ ነበረው:: ለዘጠኝ ዓመትም በዚህ ዓይነት ሠራ፤ ከዚህ ሥራው ያገኘው ሰላሳ ብር ብቻ ነበር:: ይኸውም በቀን አንድ ሳንቲም ያህል ማለት ነው:: በመላው ዓለም ዝነኛ የተውኔት ደራሲ ለመሆን ግን በቅቷል:: በአንድ ደሴት ውስጥ ብቻውን ይኖር የነበረውን ሮቢንሰን ክሩዞ እንኳ በየቀኑና በየሰዓቱ ምን መስራት እንዳለበት ዕቅድ አውጥቶ ነበር::

3ኛ. <u>አንድ ችግር ባጋጠመህ ጊዜ ለመወሰን የሚያስችሉህ መረጃዎች ካሉ ውሳኔ ስጥባቸው፤ ከመወሰን ወደኋላ አትበል</u>

የቀድሞ ተማሪዬና የአንድ ትልቅ ድርጅት የቦርድ ዲሬክተሮች አባል የነበረ ሚቼ ኤች ፒ ሀውል በየስብሰባው ብዙ ጉዳዮች ለውይይት ቀርበው ብዛኛዎቹ ውሳኔ ሳይሰጥባቸው ይቀሩ ስለነበር እያንዳንዱ የቦርድ አባል በርከት ያሉ ሪፖርቶችን እቤቱ ወስዶ ማጥናት ነበረበት ብሎ አጫውቶኛል::

በመጨረሻ አቶ ሀውል የቦርዱን አባላት ባንድ ጊዜ ሳንድ ጉዳይ ውሳኔ እንዲሰጥ አግባባቸው:: ውሳኔው አንዳንዴ ተጨማሪ መረጃዎችን የሚጠይቅ ሆኖ ይገኛል:: የሚሰጠው ውሳኔ አንድን ነገር ለመጸፈም ወይም ላለመፈጸም ሊሆን ይችላል::

ዋናው ነገር ግን ወደሚቀጥለው ጉዳይ ከማለፉ በፊት በተያዘው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሰጥቶ ማለፉ ነው::



Scanned by CamScanner

t.me/BooksandYou



አቶ ሀውል እንደነገረኝ ቦርዱ በዚህ መንገድ መሥራት ከጀመረ አንስቶ ውጤቱ አስደናቂና አመርቂም ነበር:: ከዚያ በኋላ ቀጠሮዎች እያነሱና ውዝፍ ሥራዎች እየተቃለሉ ሄዱ:: እያንዳንዱ አባልም ሪፖርቶቹን ተሸክሞ ወደቤቱ ከመሄድ ዳነ:: ውሳኔ ባልተሰጣቸው ጉዳዮች ሳቢያ የነበረው ጭንቀትም ጠፋ:: ይህ ወርቃማ መመሪያ ለዚያ ቦርድ አባላት ብቻ ሳይሆን ለኔና ላንተም ይጠቅማል::

## 4ኛ. ማስተባበርን መምራትንና መቆጣጠርን ተማር

አብዛኛው አሠሪ በቀላሉ ለውድቀት የሚዳረገው ኃላፊነትን፣ ለሌሎቹም በማከፋፈል ፋንታ ሁሉንም ነገር ብቻዬን ልጨርሰው ሲል ነው:: የዚህም ውጤት በሥራ ጊዜ ተውጦ መደናበር ነው:: ይህ ሰው ዘወትር እንደተጣደፈ፣ እንደተጨነቀ፣ እንደተከፋና እንደተወጠረ ይኖራል:: በእርግጥ ኃላፊነትን ለሰዎች ማከፋፈል ከባድ ነው:: ይህን በደንብ አውቀዋለሁ:: እኔንም ያስጨንቀኝና ያስቸግረኝ የነበረ ነገር ይህ ነው:: ኃላፊነትም ለማይገባቸው ሰዎች አሳልፎ መስጠቱም አደገኛ እንደሆነ ከልምድ አውቄዋለሁ:: ቢሆንም አሠሪው ጭንቀትንና ውጥረትን፣ ድካምን ለማስወገድ ከፈለገ ኃላፊነቱን ለሚገባቸው ሰዎች ማከፋፈል አለበት::



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ 3

## የድካም ስሜት ለምን እንደሚሰማና እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል

የአእምሮ ሥራ ብቻውን አያደክምህም የሚል አስተሳሰብ አለ:: እንዲህ ሲባል የማይሆን ነገር ይመስላል:: ነገር ግን ሳይንቲስቶች የሰው አእምሮ ድካም ሳይሰማው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሠራ ለማወቅ ሞክረው ነበር:: ባደረጉትም ምርምር ያልጠበቁትን ውጤት አገኙ:: ይኸውም በሥራ የተጠመደ አንጐል ውስጥ የሚያልፈው ደም ምንም ዓይነት የድካም ምልክት አያሳይም:: በአንጻሩ ደግሞ የጉልበት ሥራ በሚሠሩ ሰዎች አንጐል ውስጥ የሚያልፈው ደም በድካም ምልክት ተመርዞ አግኝተውታል:: እንግዲህ አንጐልን በሚመለከት ከሆነ ለአስራ ሁለት ሰዓት ወይም ለሳምንት ያህልም እንኳ ያለማቋረጥ ቢሠራ የድካም ስሜት እንደማያሳይ ተረጋግጧል:: ታዲያ ምንድነው ድካም እንዲሰማ የሚያደርገው?

የአእምሮ ህክምና ሊቃውንት (ሳይኪያትሪስቶች) «የድካም ስሜት የሚመጣው አእምሮህ ይደክመኛል ብሎ ሲወስን ነው» ይላሉ:: ታዋቂው የእንግሊዝ የአእምሮ ሕክምና ሊቅ ጄ ኤ ሀድፊልም (The Psychology of Power) በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዲህ ይላሉ::

ሁልጊዜ የሚያስጨንቀን ድካም የሚመጣው በአብዛኛው አእምሯችን ይደክመኛል ብሎ በመወሰኑ ነው እንጂ ሰውነታችንን ሊያደክመው የሚያስችል ነገር እምብዛም አያጋጥመንም:: ታዋቂው ሳይካትሪስት ዶክተር ብሪልም ይህን ሀቅ ያረጋግጣሉ::

በቢሮ ውስጥ ቁጭ ብሎ የአእምሮ ሥራ የሚሠራውን ሰው



Scanned by CamScanner

የሚያደክመው ውስጣዊ ስሜቶች ምንና ምን ናቸው? ደስታ? ርካታ? በፍጹም አይደሉም:: በዚህ ሰው ላይ የድካም ስሜት የሚፈጥሩበት መሰልቸት፣ መቆጨት፣ ብሠራም አልመሰገንም ብሎ ማሰብ፣ መታከት፣ መጣደፍ፣ መጨነቅ ወዘተ... የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው:: በዚህ የተነሳ የመጣበት የሰውነት ድካም እንደ ጉንፋን፣ ራስ ምታት ለመሳሰሉት በሽታዎች ከመዳረጉም በላይ የሥራ ውጤቱን ያዳክምበታል:: በእርግጥም የምንደክመው በውስጣችን በሚፈጠረው አግባብ የሌለው የአእምሮ ጭንቀት ነው::

አንድ የኢንሹራንስ ኩባንያ ድካምን በተመለከተ በበራሪ ወረቀት ላይ እንዲህ የሚል መልዕክት አስተላልፎ ነበር::

ከባድ ሥራ ብቻውን በጥሩ እንቅልፍና እረፍት የማይወገድ ድካም አሳድሮ አያውቅም... ጭንቀት፣ ውጥረትና ውስጣዊ የሰውነት መሸበር ናቸው ከፍተኛ ድካም የሚያስከትሉ:: የአእምሮ ወይም የጉልበት ሥራ የድካም መነሻ ይመስሉናል እንጂ ዋናዎቹ መንስኤዎች ከላይ የተጠቀሱት ሶስት ነገሮች ናቸው... አስታውስ የተሰወረ ጠ -ንቻ በስራ የዳበረ ጡንቻ ሲሆን በጭንቀት የተወጠረ አእምሮ ግን ጤናማ አይደለም:: ስለዚህ ሁሉን ነገር አቅልለህ እይ:: በጣም አስፈላጊ ለሆነ ሥራ ጉልበትህን ቆጥብ:: እስቲ ለአንድ አፍታ ቆም በልና ልብ ብለህ ራስህን መርምር:: ይህን መጽሐፍ ስታነብ ሀሳቡ ግልጽ ሆኖልሃል? አይኖችህ ፈዘዋል? ዘና ብለህ ነው የተቀመጥከው ወይስ አጉንብሰሃል? ፊትህ እንዴት ነው? ጨፍግጓል? በዚች ቅጽበት ሙሉ በሙሉ ተዝናንተህ ያልተቀመጥክ እንደሆነ በአእምሮም በአካልም ውጥረት እንደፈጠረብህ መሆኑን እወቅ:: በዚህ ሰዓት በራስህ ላይ ውጥረትና ድካም እየፈጠርክ መሆኑን አስተውል::



Scanned by CamScanner

የአእምሮ ሥራ በምንሠራበት ጊዜ እንደዚህ ያለውን የማያስፈልግ ውጥረት የምንፈጥረው ለምንድን ነው? ጆስላይን እንዲህ ይላል::

«ከባድ ሥራ ብዙ ጥረት ይፈልጋል:: ያለዚያ በቅጡ ሊሠራ አይችልም የሚለው ሁለንተናዊ እምነት የድካም ሁሉ መነሻ መሆኑን ደርሼበታለሁ:: ስለዚህም በተመስጦ ስንሠራ እንጨነቃለን፣ እንሸማቀቃለን:: ጉልበት ለመጨመር ጡንቻዎቻችንን እንወጥራለን:: ይህ ደግሞ አእምሮአችንን በፍጹም አይረዳውም::»

ስለዚህ ጉዳይ አንድ በጣም የሚያስደንቅና የሚያሰቅቅ እውነት አለ:: ይኸውም ብዙ ሰዎች ገንዘብ አናጠፋም ብለው ወስነው ያን ገንዘብ አጥፍተው ራሳቸውን በራሳቸው ሲያስጨንቁ ይበልጥ ያጠ ፋሉ፣ የባሰውንም ይጨነቃሉ::

ደስተኛ ሁን! ሥራ ስትሠራ ሁልጊዜ ዘና ብለህ መደሰትህን አትርሳ:: ይህ ቀላል ነውን? አይደለም ይህን ለማድረግ ዕድሜህን ሙሉ ካንተ የኖረውን ልማድ መቀየር ይኖርብህ ይሆናል:: ነገር ግን ሕይወትህን ይለውጠዋልና ዋጋ አለው:: ዊሊያም ጀምስ «የአሜሪካን ሕዝብ ጭንቀት፣ እብደት፣ ውጥረት ወዘተ... የመሳሰሉት ሁሉ የሚመነጩት ከመጥፎ ልማዶች ነው፣ ከዚህ ውጭ አይደሉም» ይላል::

የአእምሮ ውጥረት ልማድ ነው:: ደስተኛ መሆንም ልማድ ነው:: እናም መጥፎ ልማዶች መወገድ ሲገባቸው ጥሩ ልማዶች ደግሞ መኮትኮት አለባቸው:: መዝናናት ከምን ይጀምራል? ከአእምሮ ወይስ ከስሜት? ከሁለቱም አይደል? በመጀመሪያ ሰውነትህን ዘና አድርግ:: እስኪ በተግባር እንየው:: ሰውነትህን ለማዝናናት ከአይንህ እንጀምር እንበል:: ይህን አንቀጽ አንብበህ እንደጨረስክ ደገፍ ብለህ ተቀመጥ:: አይኖችህን ክደን እና በሀሳብህ ለአይኖችህ እንዲህ በላቸው:: 'ተዝናኑ፣



Scanned by CamScanner

ተዝናኑ፣ አትጨናቀሩ፣ ተዝናኑ፣ ተዝናኑ' ይህን ለአንድ ደቂቃ ያህል በዝግታ ደጋግመው... ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የአይኖችህ ጡንቻዎች መታዘዝ መጀመራቸውን አልተገነዘብክምን:: አንድ የሆነ እጅ ውጥረቱን ጠርጐ የወሰደው መስሎ አልተሰማህምን? መልካም:: ምንም እንኳ ይህ ነገር የማይሆን ቢመስልም አንተ ግን በዚያች ደቂቃ ውስጥ የመዝናናትን ጥበብ፣ ቁልፍና ሚስጢር አግኝተሃል ማለት ነው::

ይህንን ልምምድ በእጅህ፣ በእግርህ፣ በፊትህ፣ በትከሻህና በመላ አካላትህ ሞክረው:: ነገር ግን የሰውነት ዋናው ክፍል አይን መሆኑን አትዘንጋ:: እንዲያውም ዶክተር ኤድመን ጀኮብሰን የአይንህን ጡንቻዎች ካዝናናህ ያሉብህን ችግሮች ሁሉ ትረሳለህ እስከማለት ይደርሳሉ:: አይኖችህ ሰውነትህን ለማዝናናት ቁልፍ የሆኑበት ምክንያት ሰውነታችን በአጠቃላይ ከሚጠቀምበት የስሜት ኃይል እሩቡ የሚጠፋው በነሱ ስለሆነ ነው:: ለዚህም ነው ጥሩ የማየት ችሎታ ያላቸው ብዙ ሰዎች አይናቸውን ከአቅሙ በላይ ስለሚያሰሩት የመጨናበስ አደጋ የሚደርስባቸው::

የታወቀች የልቦለድ ደራሲ የሆነችው ቨኪባውም በልጅነት ህይወቷ ውስጥ ትልቅ ትምህርት ከሰጣት አንድ አዛውንት ጋር ባጋጣሚ መገናኘቷን ትገልጻለች:: ቫኪቤውም በድንገት ትወድቅና ጉልበቷ ይላጣል፤ ወለምም ይላታል:: አዛውንቱ ይደነግጡና ያነሷታል:: እኝህ አዛውንት ከዚህ በፊት የሰርከስ ኮሜዲያን ነበሩ:: አቧራውን ከልብሷ ላይ እያራገፉና የተጎዳውን እግሯን እያሻሹ እንዲህ አሏት::

«ለመውደቅሽ ምክንያቱ ሰውነትሽን ዘና ማድረግ አለመቻልሽ ነው:: ልክ እንደ ነጠላ፣ እንደ ተሻሸ አሮጌ ነጠላ የሚተጣጠፍ



Scanned by CamScanner

ሰውነት እንዳለሽ አድርገሽ መቁጠር አለብሽ:: ነይ ይህ ነገር እንዴት እንደሚቻል ላሳይሽ::»

አዛውንቱ ሺኪባውምንና ሌሎችን ሕፃናት ሰብስቦ እንዴት መውደቅ፣ መዝለል፣ መገለባበጥ እንዳለባቸው አስተማራቸው:: እየደጋገሙም እንዲህ ይሏቸው ነበር::

«ሰውነታችሁን እንደተሻሸ አሮጌ ነጠላ አድርጋችሁ ቁጠሩት፣ እናም ተዝናኑ» የትም ቦታ በማንኛውም ሁኔታ መዝናናት ትችላለህ:: ብቻ ለመዝናናት ብዙ አትጨነቅ:: መዝናናት የውጥረትና የጭንቀት መወገድ ነውና:: እንግዲህ ቅድም እንደተባለው ከአይኖችህ ጀምረህ የሠራ አካልህን ለማዝናናት ሞክር ራስህን ልክ እንደ ጨቅላ ልጅ ከውጥረት ነጻ የሆን አድርገህ ቁጠር::

ከዚህ በታች ራስን ለማዝናናት የሚረዱ አምስት ነገሮች ተሰጥተዋል::

1. *ሰውነትን ስለማዝናናት የተጻፉ መጻሕፍትን አንብብ::*
2. *አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙህ ዘና በል፣ አትሸበር:: ሁልጊዜ እንደተሻሸ አሮጌ ነጠላ ሰውነትህን መተጣጠፍ የሚችል ከውጥረት ነጻ የሆነ እንደሆን አትርሳ::*
3. *በተቻለህ መጠን የሚመች ቦታ መርጠህ ሥራ:: በሰውነትህ ውስጥ ውጥረት ሲፈጠር የጀርባ ህመምና የስሜት መድከም እንደሚያስከትል አስታውስ::*
4. *በቀን አራቴ ወይም አምስት ጊዜ ራስህን መርምር:: እንዲህም በል 'ይህን ሥራ አላግባብ አከብጄ ተመልክቼው ይሆን? ለምሠራው ሥራ የሚያገለግሉ ጡንቻዎችን እየተጠቀምኩ ይሆን?' እንዲህ*



Scanned by CamScanner

t.me/BooksandYou



*ብለህ መጠየቅህ የመዝናናትን ልማድ ለማዳበር ይረዳሃል::*

*5. የዕለት ተግባርህን አከናውነህ እንዳበቃህ ራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቀው:: 'ምን ያህል ነው የደከመኝ? የሠራሁት የአእምሮ ሥራ ሳይሆን የአሠራሩ ስልት ነው ማለት ነው'::*

ዳንኤል ጆሳለን ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላሉ::

«ምን ያህል እንደሠራሁ የምለካው በድካሜ መጠን ሳይሆን ባለመድከሜ ነው» ቀጥለውም «የዕለት ተግባሬን አከናውኜ እንዳበቃሁ በተለየ ሁኔታ ከደከመኝ ወይም ቁጣ ቁጣ ካለኝ አንጐሌ እንደተዳከመ እረዳለሁ:: በዚህም ያን ዕለትም ያለምንም ጥያቄ በጥራትም ሆነ በብዛት ጥሩ ሥራ ያልሠራሁበት ቀን መሆኑን እገነዘባለሁ::»

እያንዳንዱ ሰው ይህን ሁኔታ አጥብቆ ቢያጤን በደም ብዛት የሚያልቀው ሰው መጠን በአንድ ሌሊት ይቀንስ ነበር:: የአእምሮ ህክምና ሆስፒታሎችም ከመጨናነቅ ይተርፉ ነበር::



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ 4

## ድካምን፣ ጭንቀትንና ቁጭትን የሚያስከትለውን ስልቹታ ስለማስወገድ

የድካም ዋንኛ መነሻ ስልቹታ ነው:: ይሀንንም በምሳሌ ለማስረዳት ሜሪ የተባለችውን ታይፒስት እንወስዳለን:: ሜሪ አንድ ቀን ድክምክም ብላ እቤቷ ገባች:: በአንድ ወገን ራስ ምታቱ፣ በአንድ ወገን የወገብ ቁርጥማቱ ያሰቃያት ጀመር:: እቤት እንደ ደረሰች ራትም አልበላ፣ ውሃም አልጠጣ እተኛለሁ አለች:: እናትዬዋ እራት በልታ እንድትተኛ ለመነቻት... እናትዬዋን ሳለማስቀየም ስትል እሺ አለች:: እንደነገሩ እየበላች ሳለ ስልክ ተደወለ:: እጮኛዋ ነበር በዕለቱ ለተዘጋጀው የዳንስ ምሽት የጋበዛት:: ይሄኔ የሜሪ አይኖች በሩ፤ መንፈሷም ታደሰ:: እየሮጠች ወደ መኝታ ክፍሏ ገባችና የምትወደውን ልብሷን ለብሳ ብቅ አለች:: ... ያን ዕለት እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ደነሰች:: ከዳንሱ ስትመለስ ምንም ዓይነት የድካም ስሜት አይታይባትም ነበር:: ከደስታዋ ብዛት የተነሳ እንቅልፍ ሊወስዳት አልቻለም::

ከዚህ ምሳሌ እንደምንረዳው በጣም ደስ የሚለንን ነገር በምንሠራበት ጊዜ ባብዛኛው የድካም ስሜት የማይሰማን መሆኑን ነው:: ሌላ ምሳሌ ለመጨመር እኔ ራሴ ለዕረፍት ወደ ካናዳ ሂጄ ሳለ በሉዊስ ሀይቅ አካባቢ ወደሚገኙት ተራራማ ቀበሌዎች ሂጄ ነበር:: እዛም አብዛኛውን ቀን ያሳለፍኩት በኮራን ወንዝ አሣ በማጥመድ ነበር:: እዚህ ወንዝ ለመድረስም ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ማቋረጥ ነበረብኝ:: ጫካው ጥቅጥቅ ከማለቱ የተነሳ ሀረጎች የተጋደሙ ግንዶች እየጠለፉ



Scanned by CamScanner

ያሰቃዩኝ ነበር፡፡ ቁጥቋጦዎችና ቋንጥሮች ይበጫጭቁኝና ይቆነጥሩኝ ነበር፡፡ ያም ሆኖ ለስምንት ሰዓት ያህል እንዲህ ተሰቃይቼ የድካም ስሜት አልተሰማኝም፡፡ ለምን ይመስልሃል? ምክንያቱም በፍላጐትና በደስተኝነት የማደርገው ስለነበር ነው፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ስድስት ያህል ትላልቅ አሳዎችን አጥምጄ እመለሳለሁ፡፡ አሣ ማጥመድ ሥራዬ ሆኖ ቢሰለቸኝ ኖሮ ምን እንደሚሰማኝ ታውቃለህ? ድክምክም ይለኝ ነበር፡፡

አድካሚ በሆነው የተራራ መውጣት ተግባር እንኳ ተራራውን መውጣት ከመጀመርህ በፊት ከሰለቸህ እዚያው እንዳለህ ተራራው በመውጣትህ ከሚሰማህ የድካም ስሜት የበለጠ ትደክማለህ፡፡

ደክተር ኤድዋርድ ቶርንዳይክ ስለ ድካም መንስኤ ሙከራ ለማድረግ የተወሰኑ ወጣቶችን ለአንድ ሳምንት ያህል እንቅልፍ ሳይተኙ እየተዝናኑ አቆዩአቸው፡፡ ከብዙ ምርምር በኋላም ዶክተሩ ባቀረቡት ሪፖርት ውስጥ እንዲህ ይላሉ፡፡

የሥራ መጓተት ዋናው ምክንያት ስልቹታ ነው፡፡

የአእምሮ ሥራ የምትሠራ ከሆነ የሚያደክምህ በፍጹም የሠራኸው ሥራ ብዛት አይደለም፡፡ ይልቅስ የምትደክመው ባልሠራኸውና ያደክመኛል ብለህ በገመትከው የሥራ ቁልል ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል በቅርቡ በሥራ ላይ አንድንድ ነገሮች በተደጋጋሚ ጣልቃ እየገቡ ሥራህን ያቋረጥክበትን ቀን አስከያንለት ለደብዳቤዎች መልስ አልሰጠ ህም፡፡ ቀጠሮዎች አፍርሰሃል፡፡ እዚህም እዚያም ችግር ሲያጋጥምህ ውሏል፡፡ በጠቅላላው ያን ቀን ልክ አልነበረምና ምንም አጥጋቢ ሥራ አልሠራህም፡፡ ሆኖም እቤትህ ስትገባ እጅግ ደክሞህ፣ ራስ ምታት እየፈለጠህ ነበር፡፡ በማግስቱ ሥራህ ላይ ምንም ችግር አላጋጠመህም፡፡



Scanned by CamScanner

ስለሆነም ትናንት ከሠራኸው አርባ እጅ ያህል ሠራህ:: ነገር ግን እቤትህ የገባኸው መንፈስህ ታድሶ ነበር:: እንደዚህ ዓይነት ነገር ሳያጋጥምህ አልቀረም፤ እኔን አጋጥሞኛል:: ከዚህ ምን እንማራለን? የድካም መነሻው የሥራ ብዛት ሳይሆን ጭንቀት፣ ብስጭትና ቁጭት መሆናቸውን ነው::

ይህንን ምዕራፍ እየጻፍኩ ሳለ አቋርጬው ሲኒማ ገባሁ:: በፊልሙ ውስጥ የነበረው አንድ ገጸ ባህርይ እንደዚህ ሲል ሰማሁት፤

«የታደሉ ሰዎች የሚወዱትን ነገር የሚሠሩ ናቸው::» እንዲህ ዓይነቱ ሰዎች ዕድለኛ የተባሉበት ምክንያት ብዙ ኃይል፣ ብዙ ደስታ፣ አነስተኛ ጭንቀትና አነስተኛ ድካም ስለሚሰማቸው ነው:: ፍላጎትህ ባለበት ኃይልህም አለ:: ከጨቅጫቃ ሚስት ጋር አሥር ሜትር ከመጓዝ ከምታፈቅርህ ጋር አሥር ኪሎ ሜትር መጓዝ ይቀላል::

ከስልቺታ ለመላቀቅ ምን ማድረግ ይሻላል?

አንድ ታይፒስት ያደረገችውን ልንገርህ:: ሥራዋ በየዕለቱ ተመሳሳይ ቅጾችን መሙላት ነበር:: ስለዚህም ትሰለቻለች:: ታዲያ ምን አደረገች መሰለህ:: ሥራዋን በፍላጎት ለመሥራት ቆርጣ ተነሳች፤ ይህም ተሳካላት:: እንዴት ሊሳካላት ቻለ? የተሳካላት ከራሷ ጋር ውድድር በመግጠሟ ነበር::

የጠዋት ሥራ ከመጀመሯ በፊት ባለፈው ዕለት የሞላቻቸውን ቅጾች ትቆጥራለች:: በዕለቱም ከነሱ የበለጡ ቅጾችን ለመሙላት ትወስናለች:: ይህንን ውድድር በተደጋጋሚ ካደረገች በኋላ ሥራዋን በፍላጎት ማከናወን ቻለች:: በዚህም ከክፍሉ ሠራተኞች ሁሉ ብልጫ አገኘች:: በመብለጧ ምን አገኘች? አድናቆት አይደለም:: ምስጋና? በፍጹም:: ዕድገት? በጭራሽ:: ደሞዝ ጭማሪ? እንዲያውም:: ያገኘችው



Scanned by CamScanner

ነገር በመስልቸት የሚመጣባትን ድካም በማስወገድ የመንፈስ እርካታ ነበር:: ይህም ደግሞ የመሥራት ኃይልና ፍላጎት እንዲያድርባት ከማድረጉም በላይ የዕረፍት ጊዜዋን በጭንቀትና በቁጭት ሳይሆን በደስታ እንድታሳልፈው ረዳት:: ይህም ታሪክ እውነተኛ መሆኑን ሙሉ በሙሉ ልመስክር እችላለሁ:: ምክንያቱም የዛሬዋ ሚስቴ ያቺ ልጅ ናትና::

ከጥቂት ዓመታት በፊት በአንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ በትርፍ ጊዜው እየሠራ የሚማር ሀርለን ሀዋርድ የተባለ ሰው ነበር:: ሥራውም በት/ቤቱ ምግብ ቤት ውስጥ ሳህን ማጠብ፣ የሂሳብ መኪናዎችን መወልወልና ጀላቲን እየለካ ማቅረብ ነበር:: ሃዋርድ ይህን ሥራ ሲያከናውን ሌሎች ልጆች ግን ኳስ መጫወትና ከልጃገረዶች ጋር በመዳራት ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ያይ ነበር:: ስለዚህም ሥራው በጣም ያስጠላውና ይሰለቸዋል:: ሀዋርድ ምንም አማራጭ ስላልነበረው ሥራውን በፍላጎት የሚሠራበትን መንገድ አቀደ:: የጀላቲን አሠራር ማጥናት ጀመረ:: ጀላቲ እንዴት እንደሚሠራ፣ በውስጡ ምን ምን ነገሮች እንደሚገቡበት፣ አንዳንድ ዓይነት ጀላቲ ከሌላው ለምን እንደሚሻል መረመረ:: ባጭሩ ሀዋርድ የቅመማ ዘዴ Chemistry አጠና:: በት/ቤቱ ውስጥ የኬምስትሪ ትምህርት ኮከብ ለመሆን በቃ:: ከዚህም አልፎ ወደ ኮሌጅ ሲገባ የምግብ ቅመማ (Food Technology) ትምህርት የማጥናት ፍላጎት ስላደረበት የምግብ ቴክኖሎጂን (Food Technology) በአንደኛ ደረጃ መርጦ ማጥናት ጀመረ:: በዚህ ወቅት የኮካኮላ ፋብሪካ በኮካኮላና በቸኮላታ ጥቅሞች ላይ የተመሰረተ ምርጥ ድርሰት ለጻፈ የኮሌጅ ተማሪ የገንዘብ ሽልማት እንደሚሰጥ አስታወቀ:: ይህን ሽልማት ማን የሚወስድ ይመስልሃል? ልክ ነህ ሀርለን ሀዋርድ ነው::



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ 5

## ተፈጥሮ ከለገሰችህ ጸጋዎች አንዱን እንኳን በሚሊዮን ብር ትሸጣለህ

ለአያሌ አመታት የማውቀውን ጓደኛዬን ሀሮድ አቦትን ከጭንቀት እንዴት ነፃ ሆነህ ትኖራለህ? ብዬ ስጠይቀው የሚከተለውን የማይረሳ ታሪክ ነገረኝ::

«ድሮ በጣም እጨነቅ ነበር:: ጭንቀቴን ሁሉ እንዳስወግድ ያደረገኝ በ1934 ዓ.ም. በመጸው ወራት በመንገድ ላይ ስሄድ የገጠመኝ ትዕይንት ነው:: ትዕይንቱ ከአስር ሰከንድ በላይ አልወሰደም:: ሆኖም በእነኝህ አስር ሰኮንዶች ባለፉት አስር ዓመታት ያላወቅሁትን የአኗኗር ዘዴ እንድማር አደረገኝ:: ከዚህ በፊት ለሁለት ዓመት ያህል በዚያ ከተማ ውስጥ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ ነበረኝ:: ይህ ሱቅ በጣም ስላከሰረኝ ከባንክ ያለኝን ገንዘብ አውጥቼ እንድጨርስ ብቻ ሳይሆን ለመክፈል ሰባት ዓመት የሚፈጅ ዕዳ ውስጥም ጨምሮኝ ነበር:: እና ያንን ትዕይንት ያየሁት ወደ ካንሳስ ከተማ ሄጄ ሥራ ለመፈለግ የሚረዳኝ ገንዘብ ለማግኘት በምጓዝበት ወቅት ነበር:: ተስፋ ቆርጫለሁ፤ ግን በድንገት እግር የሌለው ሰው አየሁ:: እሱም በሁለት እጁ ብርኩማ ይዞ እየተንፏቀቀ መንገዱን አቋርጦ ወደ እግረኛ መሄጃው ለመውጣት ሲፍጨረጨር አየሁት:: አይኖቻችን ተጋጠሙ:: ፈገግ ብሎ እንዲህ ሲል የሞቀ ሰላምታ ሰጠኝ:: 'እንደምን አደሩ ጌታዬ? የዛሬው ቀን ደስ ይላል አይደል?' ይህን ሰው ሳይ በጣም የታደልኩ መሆኔንና አላግባብ እጨነቅ እንደነበር ተገነዘብኩ:: ሁለት እግሮች አሉኝ - እንደልቤ መራመድ እችላለሁ:: ስለራሴ በማዘኔ አፈርኩ:: ራሴንም እንዲህ አልኩት:: 'ይህ ሰው ያለ እግር ደስተኛ ከሆነና በራሱ ከተማመነ



Scanned by CamScanner

እኔ እግር ያለኝ ሰው እንደሱ የማልሆንበት ምንም ምክንያት የለም::'
ወዲያው ኩራት በሰራ አካላቴ ተሰራጨ:: ከባንኩ ልበደር ያሰብኩት መቶ ብር ብቻ ነበር:: ግን ሁለት መቶ ብር ለመጠየቅ ወሰንኩ:: 'ወደ ካንሳስ የምሄደው ሥራ ባገኝ በማለት ነው' ብዬ ለባንኩ ለመናገር አስቤ ነበር:: አሁን ግን እርግጠኛ ሆኜ ሥራ ለማግኘት ወደ ካንሳስ እንደምሄድ ለመንገር ወሰንኩ:: ብድሩንም ሥራውንም አገኘሁ::

ዛሬ በመጸዳጃ ክፍሌ መስታወት ላይ የሚከተሉት ቃላት ተጽፈው ይገኛሉ::

'እግር የሌለው ሰው እስከማይ ድረስ ጫማ ስለሌለኝ እከፋ ነበር!' እነኝህንም ቃላት ጠዋት ጠዋት ፂሜን ስላጭ አነባቸዋለሁ::»

በፓሲፊክ ውቅያኖስ ላይ ለሃያ አንድ ቀናት ተስፋ የለሽ የወሮበላ ኑሮ ያሳለፈው አንድ ጓደኛዬ ከዚያ ኑሮው ስላገኘው ትምህርት ሲናገር እንዲህ ይላል::

«ከዚያ ልምድ ያተረፍኩት አንድ ትልቅ ትምህርት የምትጠጣውን ንፁህ ውሃ፣ የምትበላውን ምግብ በፈለገው ሰዓት ካገኘህ ስለ ምንም ነገር መጨነቅ እንደማይገባህ ነው::»

ታይም መጽሔት በጦርነት ቆስሎ ሆስፒታል ስለገባ አንድ ሃምሳ አለቃ አንድ ጽሑፍ አቅርቦ ነበር:: ሃምሳ አለቃው በቦንብ ፍንጣሪ ጉሮሮውን ተመቶ መናገር አይችልም ነበር:: ይህ ሰው በጽሑፍ «እሞት ይሆን ዶክተር?» ሲል ጠየቀ:: ዶክተሩም «አትሞትም» ብሎ መለሰለት:: «ወደፊትስ መናገር እችል ይሆን?» ብሎ ጻፈ:: የሐኪሙ መልስ «አዎ!» የሚል ነበር:: ቁስለኛው ይህን እንደሰማ የሚከተለውን ጻፈ::



Scanned by CamScanner

«ታዲያ ምን ይፈጠር ብዬ ነው የምጨነቀው?»

እስቲ አንተም እንዲሁ ረጋ በልና ራስህን ጠይቅ:: ምናልባትም መጨነቅህ የማያስፈልግና እርባና የለሽ ሆኖ ታገኘው ይሆናል::

በህይወታችን ውስጥ ከሚያጋጥሙን ነገሮች መካከል ዘጠና በመቶ ያህሉ መሆን ያለባቸው ሲሆኑ አስር በመቶው ደግሞ መሆን የማይገባቸው ናቸው:: ስለዚህ ደስተኛ ለመሆን ከፈለግህ መሆን የሚገባቸውን ተቀብለን መሆን የሌለባቸውን መተው አለብን::

እጅ አለህ፣ እግር አለህ፣ ዓይን አለህ፣ ቤተሰብ አለህ እነኝህ ደግሞ በተረት ውስጥ ከሚያጋጥሙን እጅግ በርካታ ሀብት የሚልቁ ናቸው:: ለመሆኑ ከእነኝህ ነገሮች አንዱ በሚሊዮን በሚቆጠር ብር ሽጥ ብትባል ትስማማለህ? እግርህን በስንት ትሸጣለህ፣ እጅህንስ? የመስማት ችሎታህንስ? ልጆችህንስ ለእነኝህ ነገሮች ዋጋ ተምንላቸውና የምታገኘውን ሀብት ደምር:: ሀብታም አይደለህምን? ሆኖም በዓለም ላይ የሚገኘውን የወርቅ ክምር ቢሰጡህ እንኳ ከእነኝህ ነገሮች አንዷን አትሸጥም:: እኔና አንተ ተፈጥሮ የሰጠችን ፀጋ ለማየት ብንችል ሀብታም መሆናችንን ስለምንገነዘብ ደስተኛ ሰዎች እንሆናለን::

ለመሆኑ ተፈጥሮ ባደለችን ፀጋ እንረካለን? ባለመታደላችን አንረካም? ስለዚህ ጉዳይ ታዋቂው ፈላስፋ ሾፐንሀወር እንዲህ ይላል::

«ምን ጊዜም የምናስበው ያለንን ነገር ሳይሆን የሌለንን ነገር ነው::» አዎ ይህ ስላለን ሳይሆን ስለሌለን ነገር ማሰባችን በምድራችን ላይ ያለ ትልቅ ትራጄዲ ነው:: ምናልባት ከዚህ በፊት የተደረጉ ጦርነቶችና የተነሱ ወረርሽኞች ካደረሱት ስቃይ የበለጠ በምድራችን ላይ እንዲዳረስ ምክንያት ሆኗል::

በዩኒቨርስቲ ውስጥ የክፍል ጓደኛዬ የነበረችው ሉሲ ያጫወተችኝ



Scanned by CamScanner

ትዝ አለኝ:: ኑሮዋ ሁሉ በመጣደፍ የተሞላ ነበር:: ባንድ ወገን ኦርጋን ስታጠና፣ በሌላ በኩል በአንድ የጤና ጣቢያ ውስጥ ትሠራ ነበር:: ሙዚቃም ታስተምር ነበር:: በዚህ ላይ ወደ ፓርቲዎችና ዳንስ ቤቶች መሄድ ነበረባት:: ፈረስም ትጋልብ ነበር:: አንድ ቀን ጠዋት ወደ መጸዳጃ ክፍሏ ስትሄድ ተዝለፍልፋ ወደቀች:: የተጠራው ሐኪም ለአንድ ዓመት ያህል ተኝተሽ ሙሉ ዕረፍት መውሰድ አለብሽ ብሎ አዘዛት::

ሉሲም ደነገጠች፤ አለቀሰች:: እንዴት አድርጌ ልገፋው ነው? ብላ ተጨነቀች:: ሆኖም ዶክተሩ ያዘዛትን ከመፈጸም ሌላ ምርጫ አልነበራትም:: አንድ ሰዓሊ የሆነ ጎረቤቷ ሊጠይቃት መጥቶ እንዲህ አላት:: «አንድ ዓመት ሙሉ የአልጋ ቁራኛ መሆን አሳዛኝ ሊመስልሽ ይችላል:: ግን አይደለም:: እንዲያውም ለማሰብና ከራስሽ ጋር ለመተዋወቅ ዕድል ይኖርሻል:: የመንፈስ ብርታትም ታገኛለሽ::»

ሉሲ ተረጋጋች:: መጻሕፍት ማንበብ ጀመረች:: አንድ ቀን በሬዲዮ «መግለጽ የምትችለው የምታውቀውን ነገር ብቻ ነው» የሚል አስተያየት ሰማች::

ሉሲ «ይህን የመሰለ አባባል ከዚህ በፊት እሰማ ነበር? ግን እንደዚያ ቀን በግልጽ ገብቶኝና ተሰምቶኝ አያውቅም» ትላለች:: ከዚያ ቀን በኋላ ለመኖር ከሚረዷት ነገሮች ሌላ ላለማሰብ ወሰነች:: ስለጤና፣ ስለደስታ ማሰብ ጀመረች:: የማየትና የመስማት ችሎታ አላት:: ደስ ደስ የሚሉ ሙዚቃዎችን በሬዲዮ ትሰማለች:: ሰፊ የማንበቢያ ጊዜ አላት:: ጥሩ ምግብ ትመገባለች፤ ጥሩ ጓደኞች አሏት:: ይህን ሁሉ አሰበች እና ደስተኛም ሆነች::

«ዛሬ» ትላለች ሉሲ «እሞት አፋፍ መድረሴን እስካውቅ ድረስ



Scanned by CamScanner

t.me/BooksandYou



እንዴት መኖር እንደነበረብኝ አለመገንዘቤን ሳስበው እፍረት ይሰማኛል።»

ዶክተር ሳሙኤል ጆንሰንም «የነገሮችን በጐ ገፅታ መመልከት መቻል በወር አንድ ሺ ብር ከማግኘት ይበልጣል» ይላሉ። ይህን ያሉት ዶክተር ሳሙኤል ራሳቸው ለብዙ ዓመታት በመከፋት፣ በመቆጨትና በመራብ የተሰቃዩና በመጨረሻም በሀገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ደራሲያንና የንግግር ችሎታ ያላቸው ሰዎች ሁሉ የበለጠ የተከበሩና የታፈሩ ሰው ለመሆን በቅተዋል።

እኔና እንተም ባለን ተደስተን መኖርን ባለመቻላችን ልናፍር ይገባናል። ከፊል ዕድሜያችንም በህልም ዓለም ውስጥ እያየን እንዳናይ መደሰት ስንችል እንዳንደሰት ሆነን አሳልፈናል።

**ጭንቀትን አስወግደን መኖር የምንፈልግ ከሆነ የሚከተለውን መመሪያ እንመልከት**

**ችግሮቻችንን ሳይሆን ተፈጥሮ የለገሰችንን ፀጋ እናስብ።**



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ 6

## የሞተን ውሻ የሚደበድብ እንደሌለ አስታውስ

በ1929 እ.ኤ.አ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚገኙ የትምህርት ባለሙያዎችን በሙሉ ያስደነገጠ አንድ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ይህን ሁኔታ ቀረብ ብሎ ለማየት ከመላው አሜሪካ ምሁራን ወደ ቺካጉ ጉረፉ፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት ሮበርት ሀቺንስ የተባለ ሰው ባስተናጋጅነት፣ በእንጨት ቆራጭነት፣ በድጋፍ ሰጭ አስተማሪነት፣ በጨርቃ ጨርቅ ደላላነት እየሰራ ከየል ዩኒቨርስቲ ተመረቀ፡፡ ከስምንት ዓመት በኋላም በአሜሪካ ውስጥ ከሚገኙ አራቱ ታላላቅ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ አንዱ በሆነው የቺካጎ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ሆነ፡፡ ለመሆኑ ዕድሜው ስንት ይመስላችኋል? ሠላሳ! ፈጽሞ የማይታመን ነገር ነው፡፡ ነባር የትምህርት ባለሙያዎች ነገሩን ሲሰሙ በመገረም እራሳቸውን ነቀነቁ፡፡ በዚህ አስደናቂ «ልጅ» ላይ የትችት ናዳ ወረደበት፡፡ አንዱ ይህን ይላል፣ ሌላው ያን ያወራል፡፡ አንዱ ወጣት በመሆኑ ሲተቸው ሌላው ልምድ የለውም ብሎ ይተቸዋል፡፡ ሌላው ደግሞ አልበሰለም ብሎ ይወርፈዋል፡፡ ጋዜጦች እንኳን ሳይቀሩ ተረባረቡበት፡፡

ፕሬዚዳንት ተብሎ በተሰየመበት ዕለት የሮበርት ሀቺንስ አባት ጓደኛ የሆነ ሰው «ልጅህን ጋዜጦች ሁሉ ሲያጥላሉት በማየቴ በጣም ደነገጥኩ» ሲል ለአባትዬው ነገረው፡፡ አባትዬውም «አዎ ነገሩ በጣም አሰቃቂ ነበር፡፡ ግን ወዳጄ የሞተን ውሻ ማንም እንደማይደበድበው ብታስተውል መልካም ነው» ሲል መለሰለት፡፡

አዎ አንድ ውሻ ኃይለኛ በሆነ መጠን ሰው ሁሉ ስለሚፈራው እሱን በመምታት ይረካል፡፡ ወይም ያሸነፈው ይመስለዋል፡፡



Scanned by CamScanner

የዌልስ ልዑል የነበረውና በኋላ ኤድዋርድ ስምንተኛ ተብሎ እንግሊዝ አገር የነገሰው ንጉስ እንዲህ ዓይነት ነገር አጋጥሞታል:: ኤድዋርድ በ14 ዓመቱ አካባቢ ዳርት ማውዝ በተባለው የባህር ኃይል ኮሌጅ ውስጥ ይማር ነበር:: አንድ ቀን ጥቂት የባህር ኃይል መኮንኖች ኤድዋርድን ሲያለቅስ አገኙትና ለምን እንደሚያለቅስ ጠየቁት:: በመጀመሪያ ሊነግራቸው አልፈቀደም:: ቆይቶ ግን የባህር ኃይሉ ዕጩ መኮንኖች ስለመቱት እንደሆነ ተናገረ:: የኮሌጁ አዛዥ ኤድዋርድን የመቱትን ዕጩ መኮንኖች ጠርቶ ልዑሉ እንዳልከሰሳቸው እሱ ግን ለምን እንደመቱት ማወቅ እንደሚፈልግ ገለጸላቸው::

ዕጩ መኮንኖቹ እርስ በእርሳቸው ትንሽ ካጉረመረሙና ከተንሾካሾኩ በኋላ የመቱት ተመርቀው በባህር ኃይሉ ውስጥ ተመድበው በሚሰሩበት ጊዜ ንጉሱን በካልቾ መትቸዋለሁ ብለው ለማውራት ፈልገው እንደሆነ ነገሩት::

ስለዚህ ሲጉሽሙሆ ሲነቅፉህ ማስታወስ የሚገባህ ሰዎች አንተን ያህል ሰው በመንካታቸው ትልቅ የሆኑ ስለሚመስላቸው መሆኑን ነው:: ይህም ማለት ሌላ እንዳይመስልህ:: በሰራኸው ሥራ የሰዎችን ትኩረት ማግኘትህን ነው የሚያሳየው:: ብዙ ሰዎች ከነሱ የበለጠ አዋቂ የመሰሏቸውንና ደህና ኑሮ የሚኖሩ ሰዎችን በማጣጣል እረመኔያዊ እርካታ ያገኛሉ:: ለምሳሌ ይህን ምዕራፍ እየጻፍኩ ሳለሁ የነፃ አውጪው ሠራዊት መሥራች የነበረውን ጀኔራል ዊሊያም ቡዝን የሚያጣጥል ደብዳቤ ካንዲት ሴት ደረሰኝ:: በደብዳቤዋ ላይ ጀኔራሉ ችግረኞችን ለመርዳት ከተሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ስምንት ሚሊዮን ብር በልቷል የሚል ነበረበት:: እርግጥ ክሱ ዋጋ ቢስ ነበር:: ሴትዮዋ እውነትን ፍለጋ ሳይሆን ከሷ እጅግ የላቀ አንድ ሰው መቦጨቅ እንዳለበት የሚገፋፋ እርኩስ መንፈስ ስላደረባት ነበር:: መራራ ደብዳቤዋን



Scanned by CamScanner

ወርውሬ ጥፎ ይችን ሰው ባለማግባቴ ዕድሌን አመሰገንኩ፡፡ ደብዳቤዋ ስለ ጀኔራል ቡዝ ምንም አዲስ ነገር አልነገረኝም፡፡ ግን ስለ ሴትዬዋ ብዙ እንዳውቅ አድርጉኛል፡፡ ከአያሌ ዓመታት በፊት ሾፐንሀወር እንዲህ ብሉ ነበር፡፡ «ጋጠ ወጦች በትላልቅ ሰዎች ስሁተትና ድክመት ካለመጠን ይደሰታሉ፡፡»

አንድ የየል ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ጋጠ ወጥ ይሆናሉ ብሉ ማሰብ ይከብዳል፡፡ ሆኖም ቲሞዝ ዳዊት የተባለ የቀድሞው የየል ፕሬዝዳንት የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ለመሆን ይወዳደር የነበረን አንድ ሰው ስሙን በማጥፋት ደስታ ያገኙ እንደነበር ታይቷል፡፡

እኚህ ሰው ሰውዬው ፕሬዚዳንት ከሆነ «ሚስቶቻችንና ሴት ልጆቻችን ለሽርሙጥና እንደሚጋለጡ፤ ክብራችንን ባደባባይ እንደምንገፋ፤ በመጥፎ ነገሮች ሁሉ እንደምንበከል ይታየኛል፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰው ከስነ ምግባር የራቀ ባለጌ በእግዜርም በሰውም የተጠላ ፍጡር ነው» እያሉ ያስጠነቅቁ ነበር፡፡ ይህን ስታነቡ ሰውየው ስለ ሂትለር የሚናገሩ አይመስላችሁም? ነገር ግን አልነበረም፡፡ ይሄ ሁሉ መአት የተወራው በቶማስ ጀፈርሰን ላይ ነበር፡፡ ተደነቃችሁ፣ የትኛው ቶማስ ጀፈርሰን? ይሄ የነጻነትን አዋጅ ያወጀው እንዳትሉ፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ ያ ሁሉ ነገር የተነገረው ስለዚህ ሰው ነበር፡፡

ስለዚህ ...

**ትክክለኛ ያልሆነ ትችት ቢፈታተንህና ቢያስጨንቅህ ፍቱን የሆነ መመሪያ ይኸውልህ፡፡**

**ትክክለኛ ያልሆነ ትችት በተዘዋዋሪ ምስጋና መሆኑን አስተውል፡፡ ማንም የሞተን ውሻ እንደማይደበድብ አስታውስ፡፡**



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ 7

## ይህን ብታደርግ ነቀፋ አያሸብርህም

አንዴ ሜጀር ጄኔራል ሰሚር በትለርን አነጋግሬ ነበር። ጄኔራሉ ወጣት ሳሉ በሰው ፊት ትልቅ ሆኖ የመታየት ምኞት ነበራቸው። ያኔ ትንሽ ትችት ቢሰነዝሩባቸው ያስቆጣቸውና ያሳምማቸው ነበር። ሆኖም ለ30 ዓመት ያህል በባህር ኃይል ውስጥ ከቆዩ በኋላ ባገኙት ልምድ ቆዳቸው እንደጠነከረ ይናገራሉ።

«ያኔ ተወቅሻለሁ፣ ተሰድቤአለሁ፣ ፈሪ፣ ውሻ፣ እባብ፣ ምስጥ ተብያለሁ። በእርግማን አዋቂዎች ተረግሜያለሁ። ልነግራችሁ የሚያሳፍረኝን ነገሮች ሁሉ ተብያለሁ። ታዲያ ይህ ያስጨንቀኝ መሰለህ? በጭራሽ። ዛሬ አንድ ሰው ሲሰድበኝ ወይም ሲያወግዘኝ ስሰማ ማን እንደሚናገር እንኳ ዞር ብዬ አላይም።»

አብዛኞቻችን ምናምንቴ ነገሮችን እንደ ቁም ነገር በመቁጠር እንበሳጫለን። ትዝ ይለኛል፣ አንዴ አንድ ጋዜጠኛ ለጐልማሶች በሚሰጠው ትምህርት ላይ ተገኝቶ ሥራዬን እኔንም አንኳስሶ ጻፈ።

ነገሩ በኔ ላይ እንደተሰነዘረ ጥቃት በመቁጠር ጨስኩላችሁ። ሂጄ ወዲያው ለጋዜጣው ክፍል ሥራ አስኪያጅ ስልክ ደውዬ በጋዜጣው ላይ እውነተኛውን ነገር ጠቅሰው እንዲጽፉ አስጠነቀቅሁ። ቅጣቱ የወንጀሉ ተመጣጣኝ መሆን አለበት የሚል ዕምነት ነበረኝ። ዛሬ ያን ድርጊቴን ሳስታውሰው እፍረት ይሰማኛል። ምክንያቱም በኋላ እንደተረዳሁት ጋዜጣውን ከገዙት ሰዎች መካከል ግማሹ ያንን ጽሑፍ አላነበቡም፣ ካነበቡት መካከል ግማሹ እንደ ቀላል ጨዋታ ወሰዱት። በጽሑፉ ከተናደዱት ውስጥ ግማሹ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ



Scanned by CamScanner

ረሱት:: ዛሬ ሰዎች ስለኔ ወይም ስላንተ እንደማያስቡና እንደማይጨነቁ ተገንዝቤያለሁ:: ጠዋትም ማታም ቀንም ሰዎች የሚያስቡት ስለራሳቸው ነው:: ስለኔ ወይም ስላንተ ሞት ከመጨነቅ ይልቅ ስለያዘቻቸው ትንሽ ራስ ምታት ሺህ ጊዜ ማሰብን ይመርጣሉ::

እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው ነገር አለ:: እኔ ማንኛውንም ትችት እንስማ ማለቴ ሳይሆን ትክክል ያልሆኑ ትችቶች ሊያስጨንቁን አይገባም ማለቴ ነው::

ቻርልስ ሺዋብ ለፕሪስተን ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ንግግር ሲያደርግ ከአንድ የብረት ፋብሪካ ሠራተኛ ከሆነ ጀርመናዊ ሽማግሌ ያገኘው ትምህርት ከተማራቸው ትምህርቶች ሁሉ የበለጠ መሆኑን ተናገረ:: ይህ ጀርመናዊ ሽማግሌ ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ስለጦርነቱ ጊዜ ሞቅ ያለ ክርክር ፈጥሮ ኖሮ ሠራተኞቹ በንዴት ገፍትረው ወንዝ ውስጥ ይከቱታል::

«ሽማግሌው ወደ ቢሮዬ ሲመጣ» ይላሉ አቶ ሺዋብ «ልብሱ ርሶና በጭቃ ተለውሶ ነበር:: ነገሩን ከሰማሁ በኋላ ሰዎቹን ምን እንዳላቸው ብጠይቀው 'ስቄ አለፍኳቸው' አለኝ::»

ሚስተር ሽዋብ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የጀርመናዊውን ሽማግሌ ቃላት መመሪያ አደረጋቸው:: ቃላቱም «ስቆ ማለፍ» የሚሉት ናቸው::

ይህ መመሪያ በተለይ ትክክለኛ ላልሆነ ትችል የተጋለጥክ ከሆነ በጣም ጠቃሚ ነው:: ለሚናገርህ ሰው መልስ ትሰጠዋለህ፤ ስቆ ለሚያልፍ ግን ምን ማድረግ ትችላለህ?

አብርሃም ሊንከን ከየአቅጣጫው ለሚሰነዘርባቸው ትችት ሁሉ መልስ አይሰጡም ነበር:: ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩም «ትክክል መስሎ የታየኝን እና የማውቀውን አደርጋለሁ... ይህንንም እስከ ፍፃሜ ድረስ



Scanned by CamScanner

እገፋበታለሁ:: ፍፃሜው ትክክል ከሆነ ስለኔ ሲነገር የነበረው ነቀፌታ ሁሉ ዋጋ ያጣል:: ፍፃሜው ካላማረ አስር መላዕክት ምለው ተገዝተው ትክክል ነበር ቢሉም ከስህተት ሊያነፃኝ አይችልም» ብለዋል::

**ስለዚህ እኔና አንተ ትክክል ያልሆነ ትችል ሲሰነዘርብን የሚከተለውን መመሪያ እናስታውስ::**

**ልታደርግ የምትችለውን ነገር ሁሉ አድርግ፣ በተረፈ ግን ለሚሰነዘሩብህ ትክክል ያልሆኑ ትችቶች ዋጋ አትስጥ:: ስቀህ እለፋቸው::**



Scanned by CamScanner

pdf by @shuktuss ሹክቱስ

# ክፍል ሁለት

## ከሰዎች ጋር ለመግባባት የሚረዱ ዋና ዋና መንገዶች

Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ 8

## ከሰዎች ጋር ለመግባባት የሚረዳ ትልቅ ሚስጥር

አንድ ሰው አንድ ነገር እንዲሰራ ለማድረግ የሚረዳ በምድር ላይ ያለው ዘዴ አንድ ብቻ ነው። ያ ምን እንደሆነ አስበህ ታውቃለህ? ዘዴው በሰዎች ላይ የመስራት ፍላጐት እንዲያድርባቸው ማድረግ ነው። አስታውስ። ከዚህ ሌላ ዘዴ የለም። እርግጥ ነው አንድ ሰው ላይ ሽጉጥ ደግነህ ሰዓቱን ልትቀበለው ትችላለህ። ወይም አንድ ተቀጣሪህን ከስራ አባርርሃለሁ እያልክ በማስፈራራት ብዙ ሥራ ልታሠራው ትችላለህ። አንድን ልጅ አለንጋ በማሳየት አንድ ነገር ልታሠራው ትችላለህ። ሆኖም እነኝህ አስጨናቂ መንገዶች አስፈላጊ ያልሆኑ አለመግባባትን ያስከትላሉ።

እኔ አንተን አንድ ሥራ ለማሠራት የምጠቀምበት ዘዴ ሥራውን በፍላጐትህ እንድትሠራው ማድረግን ብቻ ነው። ዝነኛው የሥነ አእምሮ ሊቅ ሲግመንድ ፍሮይድ ከሁለት ነገሮች እንደተገኘን ይናገራሉ። እነሱም የወሲብ ግፊትና ታላቅ ለመሆን መመኘት ናቸው። ፕሮፌሰራ ጆን ዲዊ የተባሉት ታላቅ ፈላስፋ ይህን የፍሮይድን አባባል ትንሽ ለየት አድርገው ያቀርቡታል። እሳቸውም በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ከፍተኛ ግፊት ያለው «ተፈላጊ የመሆን ምኞት ነው» ይላሉ።

ታላቅ የመሆን ምኞት የሚለውን ሀረግ አስታውስ። በዚህ መጽሐ ፍ ውስጥ ደጋግመን የምንለው ሐረግ ነው። ምን ትፈልጋለህ? በጣም ያስፈልጉኛልና ላጣቸው አይገባም የምትላቸው ነገሮች የተወሰኑ ናቸው። አብዛኛው ሰው የሚከተሉትን ነገሮች ይፈልጋል።

1. ጤናና የህይወት መጠበቅ

2. ምግብ
3. መኝታ
4. ገንዘብና ገንዘብ የሚገዛቸው ነገሮች
5. የፍትወተ ሥጋ ርካታ
6. የልጆችን ደህንነት
7. ታላቅ የመሆን ስሜት

ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹ በአብዛኛው ሊሟሉ ይችላሉ። ነገር ግን ከመብላትና ከመተኛት ዕኩል የምንፈልገው አንደኛው ነገር ተሟልቶ ታይቶን አያውቅም። እሱም ፍሮይድ ታላቅ የመሆን ምኞት ያለው ዲዊ ደግሞ ተፈላጊ የመሆን ምኞት ብሎ የጠራው ነው።

አብረሃም ሊንከን አንድ ደብዳቤ ሲጽፉ፣ «ማንኛውም ሰው መመስገን ይወዳል» ብለው ጀምረው ነበር። ዊሊያም ጀምስ እንዲህ ይላል። «በሰው ተፈጥሮ ውስጥ የሚገኘው ጥልቅ ምኞት ለመወደድ መንሰፍሰፍ ነው» ልብ አድርግ። ስለመመኘት፣ ስለመፈለግ አልተነገረም። ለመወደስ ሲሉ «መንሰፍሰፍ» እንጂ።

ይህ ሳያቋርጥ የሚጥረመር የመመስገን ረሀብ በሰዎች ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ነገር ነው። ስለዚህም ይህንን የልብ ረሃብ አርክቶ የሚኖር ሰው ከሰዎች ጋር በቀላሉ መግባባት ይችላል።

ታላቅ የመሆን ፍላጎት ሰውን ከእንስሳ ከሚለዩት ነገሮች አንዱ ነው። ለማስረዳት ያህል፦

በልጅነቴ ለውድድር የሚቀርቡ ከብቶችና አሳማዎች ይዘን ከአባቴ ጋር ወደ ከተማ እንሄድ እንደነበረ ትዝ ይለኛል። ባብዛኛቹ ውድድሮች ባደለብናቸው አሳሞችና ከብቶች ሽልማት እናገኝ ነበር። ታዲያ

አንድ አንግዳ ወደ ቤት በመጣ ቁጥር ሽልማቶቹን አውጥቶ ሲያሳይ ከፍተኛ የትልቅነት መንፈስ ይሰማው ነበር።

<u>በውድድሩ አንደኛ የወጡት አሳሞችና ከብቶች ግን ነገሩን ከቁብ አይቆጥሩትም</u>።

ይህ ታላቅ የመሆን ስሜት ነው አንዱን በትምህርት ያልገፋ የግሮሰሪ ትኬት ቆራጭ አሮጌ በርሜል ውስጥ ሻግተው የተቀመጡ የህግ መጻሕፍትን በ50 ሣንቲም ሂሳብ ገዝቶ እንዲያነብ ያደረገው። ይህ ሰው ማን መሰለህ? አብርሃም ሊንከን ነበር። ይኸው ስሜት ነው ቻርልስ ዲከንስን ታላቅ ደራሲ ያደረገው። ሮክ ፌለርም ተጠቅሞበት ሊጨርሰው የማይችለውን ገንዘብ እንዲያጋብስ ያደረገው።

ይህ ፍላጎት ነው ፋሽን እንድትለብስ፣ በቅርቡ የመጣች መኪና እንድትይዝ፣ ስለ ልጆችህ ጉብዝና እንድታወራ የሚገፋፋህ።

ይህ ታላቅ የመሆን ስሜት ነው በአፍላ ዕድሜ ላይ ያሉ ልጆችን የከተማ ወሮበላ ተደባዳቢ የሚያደርጋቸው።

ተፈላጊ የመሆን ስሜትን እንዴት እንደምታገኝ ብትነግረኝ ማንነትህን እነግርሃለሁ። ይህ ነገር ባህርይህን ይወስነዋልና። ዲሊንገር የተባለ የታወቀ የባንክ ዘራፊ ሽፍታና ነፍሰ ገዳይ እንዴ በፖሊሶች ተከቦ ሳለ አንድ መጋዘን ውስጥ ዘሎ ገባና ድምጹን ከፍ አድርጐ በኩራት «እኔ ዲሊንገር ነኝ!» ሲል ተናገረ።

ይህ ሰው ዋነኛ የህዝብ ጠላት በመሆኑ ምን ያህል እንደሚኮራ ይታያችኋል? በሌላ በኩል ሮክፌለር በቻይና ውስጥ ሆስፒታል በማሰራት የተፈላጊነት ስሜቱን ያረካል። አስተውል! በዲሊንገርና በሮክፌለር መካከል ያለው ዋና ልዩነት የታላቅነት ስሜታቸውን የሚገለጹበት መንገድ ነው።

እስካሁን እንዳየነው ሰዎችን አንድ ነገር እንዲሰሩ የሚገፋፉቸው ታላቅ የመሆን ወይም የተፈላጊነት ምኞት ነው። ስለዚህ ከሰዎች ጋር ለመግባባት ትልቁ ምስጢር ምን ይመስልሃል? በፈረንሣይ የአሜሪካን አምባሳደር የነበረው ቤንጃሚን ፍራንክሊን ከሰዎች ጋር በመግባባት የታወቀ ነበር። ይህ ተሰጥኦ ያስገኘለት ምን እንደሆነ ተጠይቆ እንዲህ ብሎ መልሷል።

«ስለማንም ሰው መጥፎ ወሬ አላወራም (አላማም)... ሆኖም ስለሰዎች የማውቀውን ጥሩ ነገር ሁሉ እናገርላቸዋለሁ። ቂል ሰው ሌላውን ይተቻል፣ ያማል፣ ይኮንናል... መግባባት ይሏችኋል ይህ ነው።»

ቶማስ ካርላይን እንዲህ ይላል «ትልቅ ሰው ለበታቾቹ በሚያሳየው ከበሬታ ትልቅነቱን ያሳያል።»

ሰዎችን ከመኮነን እንቆጠብና እስቲ ሀሳባቸውን ለመረዳት እንሞክር። አንድን ነገር ለምን እንደሚፈጽሙ ለመረዳት እንጣር። ይህ ጥረት ከመኮነንና ከመተቸት የበለጠ ፍሬያማ ሆኖ እናገኘዋለን። ስለሰዎች ያለንን መጥፎ አስተያየትም በመለወጥ ለሰዎች ሚዛንና መቻቻልን ርህራሄን እንድንማር ያደርገናል። ሁሉን ማወቅ ሁሉን ይቅር ማለት ነው።

ሰዎችን በማግባባት በችሎታቸው ታዋቂ በመሆናቸው በአመት አንድ ሚሊዮን ብር ደሞዝ ያገኙ የነበሩት አቶ ቻርልስ ሽዋብ ስለ ችሎታቸው ምስጢር ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ።

«... የአንድን ሰው ችሎታ ለማዳበር ያንን ሰው ማመስገንና ማበረታታት በጣም አስፈላጊ መሆኑን አውቃለሁ።»

«በችሎታ ልቀው ከሚገኙ ሰዎች እንደሚሰጥ ትችት የአንድን

ሰው የመስራትንና የማደግ ጉጉት የሚገድል ነገር የለም:: በበኩሌ ማንንም ተችቼ አላውቅም:: በሰዎች በፍላጎት መስራት እምናለሁ:: ሁልጊዜ ለማመስገን ጉጉት አለኝ:: ስህተት ላይ ይቀፈኛል:: ጥሩ ሥራ ካየሁ ግን ከልብ የመነጨ ምስጋና ከማቅረብ አልቆጠብም» አቶ ሽዋብ ያደረጉት ይህን ነበር:: አብዛኞቻችን ግን ተቃራኒውን ነው የምንፈጽመው:: አንድን ነገር ካልተቀበልን ግን ተቃራኒውን ነው የምንፈጽመው:: አንድን ነገር ካልተቀበልን ትችታችንን እናዥጎደጉደዋለን፤ ከተቀበልነው ግን ዝም እንላለን::

አንዳንድ ሰዎች ይህን ሲያነቡ ይሄማ ድሮ የምናውቀው ነው:: ዝም ብሎ መቀባጠር ነው:: ባዶ ሽንገላ ነው:: አይ ይሄንማ ከዚያ በፊትም ሞክሬው ነበር፤ አይሠራም:: ለሞኛ ሞኞች ካልሆነ ለእኛ አይሆንም ይሉ ይሆናል:: እርግጥ ነው ሽንገላ ለሚያመዛዝኑ ሰዎች አይሠራም:: ምክንያቱም ጥልቀት የሌለው፤ ራስን ከመውደድ የመነጨና ከዕውነት የራቀ ስለሆነ ነው::

እርግጥ አንዳንድ ሰዎች የውዳሴ ክንቱ ረሃብና ጥም ስላለባቸው ያገኙትን ሁሉ ይቀበላሉ:: ጠኔ የያዘው ሰው ቅጠላ ቅጠልና ትላትል ከመብላት እንደማይመለስ ሁሉ::

ለመሆኑ በምስጋናና በሽንገላ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ቀላል ነው አንዱ እውነት ሲሆን፤ ሌላው ከእውነት የራቀ ነው:: አንደኛው ከልብ ሲመነጭ ሌላው ከአንገት በላይ የሚሰነዘር ነው:: አንዱ ሌሎችን ከመውደድ የሚመነጭ ሲሆን ሌላው ከራስ ወዳድነት የሚመነጭ ነው:: አንደኛው በመላው ዓለም የሚደነቅ ሲሆን ሌላው በመላው ዓለም የተወገዘ ነው::

ባንድ ሰው መቃብር ላይ የሚከተለውን እንብቤያለሁ::

«ሊያጠቁ የሚከተሉህን ጠላቶች አትፍራ፣ የሚሸነግሉ ወዳጆችህን ፍራ!» ስለዚህም ከሰዎች ጋር በመግባባት አብሮ ለመኖር ስለ አከናወኗቸው ታላላቅ ነገሮች እናስብ፣ የሌላውን ሰው መልካም ተግባር መርምረን ለማግኘት እንጣር። ሽንገላን እናስወግድ። ሰዎችን ከልባችን ከማመስገን አንቆጠብ። ይህን ብናደርግ ሰዎች የተናገርነውን ይቀበሉናል። የፈለግነውንም በደስታና በፍላጎት ይፈጽሙልናል።

# ምዕራፍ 9

## ይህን ማድረግ የሚችል ሁሉም ይደግፈዋል፤ የማይችል ግን ብቻውን ይቆማል።

በበጋ ወራት በየዓመቱ ወደ ሜይን ክፍለ ሀገር እየሄድኩ አሣ አጠምዳለሁ። ከዚህ ጉዞ ያየሁት አንድ ነገር አለ። በበኩሌ ክሬምና ዳቦ በጣም እወዳለሁ። ስለዚህም አሣ ለማጥመድ በምሄድበት ጊዜ እኔ የምወደውን ሳይሆን እነሱ የሚወዱትን መሰብሰብ ይኖርብኛል። መንጠቆ ላይ ክሬም ወይም ዳቦ አልሰካበትም፤ ትል ወይም ፌንጣ እሰካበትና እንዲህ እላቸዋለሁ፤ «ይህን ነገር መብላት አትፈልጉምን?»

ሰዎችን ለማቅረብ በምንፈልግበት ጊዜስ ለምን በዚህ ዘዴ አንጠቀምም? ፍሎይድ ጆርጅ የተባለ ሰው የተጠቀመው በዚህ ዘዴ ነበር። አንድ ሰው ፍሎይድ ጆርጅን በጦርነቱ ጊዜ የነበሩ እንደ ነዊልሰን አርላንድ የመሳሰሉ መሪዎች ሲረሱ እሱ ግን በምን ዘዴ ቢጠቀም ሌላው የሚፈልገውን በመንጠቆ ላይ መሰካት ቢችል እንደሆነ ገልጾታል። ስለዚህ ሰዎችን ለማቅረብ በምድር ላይ ብቸኛ መንገድ እነሱ ስለሚፈልጉት ነገር ማውራትና እንዴት ሊያገኙት እንደሚችሉ ማሳየት ነው።

ነገ አንድ ሰው አንድ ነገር እንዲያደርግልህ ስትፈልግ ከዚህ በላይ የተባለው ትዝ ይበልህ።

ለምሳሌ ልጅህ ሲጃራ እንዳያጨስ ብትፈልግ ስለ ሲጃራ መጥፎነት አትስበከለት። ሆኖም ሲጃራ ማጨስ የአንድ እግር ኳስ ክበብ ተጫዋች እንዳይሆን ወይም በሩጫ ውድድር እንዲሸነፍ የሚያደርገው መሆኑን ንገረው።

የሌላውን ፍላጎት የመጠበቅ ነገር ከማንኛውም ነገር ጋር ማለትም ከህፃናት ወይም ከተኛ ወይም ከዝንጀሮ ጋር በምናደርገው ግንኙነት ሁሉ ሊታሰብበት የሚገባ ነገር ነው:: ለምሳሌ ራልፍ ዋልዶ ኤመርሰንና ልጁ አንድ ቀን አንድ ጥጃ ወደ ጋጥ ለማስገባት ሞከሩ:: ሆኖም አብዛኛው ሰው የሚፈጽመውን ስህተት ፈጸሙ:: እነሱ የሚፈልጉትን እንጂ ጥጃው የሚፈልገውን አላደረጉም:: ኤመርሰን ከኋላ ሆኖ ይገፋል፣ ልጁ ከፊት ሆኖ ይጎትታል:: በዚህ ጊዜ ጥጃው ወደኋላ ወድሮ እምቢ አለ:: ይህን ከንቱ ጥረት ታይ የነበረችው ሠራተኛ ጥጃው ምን እንደፈለገ ገባት:: ጠጋ አለችና ጣቷን በዘዴ ለጥጃው አጎረሰችው:: ጥጃው ጣቷን መጥባት ሲጀምር ቀስ ብላ ወደ ጋጡ እየተራመደች ይዛው ገባች:: ሠራተኛዋ ምንም እንኳ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ባይኖራትም በዚያች ወቅት ከኤመርሰን የበለጠ ማስተዋል ችላ ነበር::

ከተወለድክ ጀምሮ ያደረግሃቸውን ለምሳሌ ለቀይ መስቀል ማኀበር 100 ብር የሰጠህበት ጊዜ ቢኖር እንኳ ሌላውን ከመውደድ የመነጨ በጐ ሥራ መሥራት ስለፈለግህ ነው:: ከመርዳት ፍላጐትህ ይልቅ የብር ፍላጐትህ ቢያይልብህ ኖሮ መቶ ብሩን ባልሰጠህ ነበር:: እርግጥ አስተዋጽኦውን እንድታደርግ የጠየቀህ ሰው እምቢ የማትለው ሆኖ ሊሆን ይችላል:: ሆኖም አንድ እውነት አለ:: ብሩን የሰጠኸው ምናልባት ከሰውዬው አንድ የፈለግኸው ነገር ስለነበረ ነው::

ፕሮፌሰር ሀሪ ኤቨርስትሪት ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ:: «ተግባር የሚመነጨው ከመሠረታዊ ፍላጐት ነው... በንግድ፣ በቤት ውስጥ፣ በፖለቲካ ሰዎች አንድ ነገር እንዲያደርጉ ለሚመክሩና ለሚቀሰቅሱ የምሰጠው ትንሽ ምክር፣ በመጀመሪያ ሰው ለዚያ ነገር በጣም እንዲጓጓ እንዲያደርጉ ነው:: ይህን ማድረግ የሚችል ሁሉም ይከተለዋል:: ያልቻለ ብቻውን ይቆማል::»

## ዴል ካርኔጊ

ከብዙ ዓመታት በፊት ጉሮሮዬን አሞኝ ያፍንጫና የጉሮሮ ሀኪም ዘንድ ሄድኩ። ሀኪሙ ገና እንደገባሁ ስለ ጉሮሮዬ ሳይሆን ስለሥራዬ ጠየቀኝ። በሽታው ምን ያህል እንደጸናብኝ የማወቅ ፍላጐት አልነበረውም። ፍላጐቱ ከኔ ምን ያህል ገንዘብ ሊያገኝ እንደሚችል ማወቅ ነበር። ሆኖም የሀኪሙ ባህርይና ድርጊቱ ስላስጠላኝ ትቸው ወጣሁ፤ ስለዚህም ሊያገኝ የፈለገውን ነገር አላገኘም።

ዓለም በእንደዚህ ዓይነቶቹ ጠቅመው መጠቀም በማይፈልጉ ስግብግቦች የተሞላች ነች። ስለሆነም በቁጥር አነስ ብለው የሚገኙት ለሌሎች ከልብ የመነጨ አገልግሎት የሚሰጡት ከፍተኛ ጥቅም ያገኛሉ፤ ብዙ ተወዳዳሪዎች የሏቸውም።

ይህን መጽሐፍ አንብበህ ነገሮችን ሌሎች ከሚያዩበት አቅጣጫ የማየት ዝንባሌህ ከጨመረ የሙያህን መሠረት ለመጣልህ ትልቅ ማረጋገጫ ይሆናል።

አንዲት ቁርስ አልበላም እያለች የምታስቸግር ልጅ የነበረችው ቤተሰብ ልጅቷን ቁርስ እንድትበላ ለማድረግ «ወፍራም እንድትሆኚ እንፈልጋለን፣ እንድታድጊልን እንፈልጋለን» እያሉ ያባብሏት ነበር። ሆኖም ልጅቷን በማስፈራራትና በማስገደድ ቁርስ እንድትበላ ተሞከረ። ይህ ድርጊት የባሰውን እንዳትበላ አደረጋት። ይህን ያየ የአባትየው ጓደኛ ወላጆቿን እንዲህ ሲል መከራቸው። «እንዳያችሁት ካስገደዳችሁዋት ይበልጥ ትጠላዋለች። ስለዚህ ለምን ፍላጐት እንዲያድርባት አታደርጉም? የእናንተ ጥያቄ መሆን ያለበት እንዴት አድርገን ፍላጐት እንዲያድርባት ማድረግ እንችላለን የሚል ነው።»

ይህን የሰማው ቤተሰብ ምክሩን በሥራ ላይ ለማዋል የልጅቷን ባህርይ አጠና። ልጅቷ እናቷ የምትሠራውን መሥራት ትወድ ነበር።

t.me/BooksandYou



አንድ እናቷ አዋቂ መስላ መታየት ትፈልግ ነበር። አንድ ቀን ጠዋት ለቁርስ ሻይ ሲቀርብ ከዚህ በፊት እናቷ እንደምታደርገው ሻይ ውስጥ ስኳር እንድትጨምር ፈቀዱላት። ዳቦውም ቀረበ። አባትና እናት ድርሻቸውን ሲያነሱ ልጅቷም ሻዩን አማስላ ዳቦውን እንስታ እያማገች ትገምጠው ጀመር። ከዚህ ቀን ጀምሮ ቁርሷን በፍላጐት ትበላ ጀመር።

ስለዚህ፣ ሰዎች አንድ ነገር እንዲያደርጉ ከፈለግህ የሚከተለውን አስታውስ።

«በመጀመሪያ ሰውየው የፈለግኸውን ነገር እንዲያደርግ ለዚያ ነገር ከፍተኛ ጉጉት እንዲያድርበት አነሳሳው» ይህን ማድረግ የሚችል ሁሉም ይከተለዋል፣ ያልቻለ ብቻውን ይቆማል።

# ምዕራፍ 10

## ይህንን ካደረግህ የትም ተቀባይነትን ታገኛለህ

ይህን መጽሐፍ ለምን ታነባለህ? ጓደኛ ለማፍራት?... በዓለም የታወቀውን ጓደኛ የማፍሪያ ጥበብ የሚያውቀውን ነገር ለምን አታጠናውም፣ እሱስ ማነው? ነገ ጠዋት መንገድ ላይ ታገኘዋለህ። ገና በ10 ሜትር ርቀት ላይ እንዳለህ ጭራውን ያወዛውዝልሃል። ቆም ብለህ ብትደባብሰው ፍንድቅ በማለት ምን ያህል እንደሚወድህ ያሳይሃል። ያኔም ፍቅር ከማሳየት የበለጠ ሌላ ምንም የሚፈለግብህ ነገር እንደሌለ ትረዳለህ። ገንዘብ ሊበደርህ ወይም ርስት ሊሸጥልህ ወይም ሊያገባህ ፍላጐት እንደሌለው ታውቃለህ።

ለመሆኑ በዓለም ላይ ከሚገኙት እንስሳት ሁሉ ለመኖር መሥራት የሌለበት ውሻ ብቻ መሆኑን ትዝ ብሎህ ያውቃል። ዶሮ ለመኖር እንቁላል መጣል አለባት፣ ላም ወተት መስጠት አለባት፣ ውሻ ግን ፍቅር እየሰጠህ ብቻ ይኖራል።

የአምስት ዓመት ልጅ በነበርኩበት ጊዜ አባቴ በሃምሳ ሳንቲም አንድ ቡችላ ገዛ። ያ ቡችላ የልጅነቴ ብርሃንና ደስታ ነበር። ውሻው ከት/ቤት የምመለስበትን ሰዓት ጠብቆ የምመጣበትን መንገድ አተኩሮ ሲመለከት ይቆይና ድምጼን እንደሰማ ወይም የምሳ ሳሕኔን እያወዛወዝኩ ስመጣ ሲያይ እንደ ጥይት ተተኩሶ በደስታ እየፈነጠዘ ይጠመጠምብኛል። በእግሬ መሃል ይገባል፣ ይልሰኛል። ይህ ውሻ ለአምስት ዓመታት ያህል ታማኝ ጓደኛዬ ነበር። አንድ ቀን፣ ያን ቀን ምንግዜም አልረሳውም። ከኔ አስር ሜትር ርቀት ላይ እንዳለ መብረቅ ገደለው። የውሻዬ ሞት በህይወቴ የመጀመሪያው ትራጀዲ ነበር። ውሻዬ ሆይ

የሳይኮሎጂ መጽሐፍ አላነበብክ፤ ደሞስ ምን ያደርግልሃል? አንተ እንደሆን በደመነፍስ ነው የሌሎችን ሰዎች ፍላጐት በመረዳት በርከት ያሉ ጓደኞችን ማፍራት እንደሚቻል የምታውቀው:: ሰዎች ይውደዱኝ ከተባለ በሁለት ዓመት አንድም እንኳ ጓደኛ ማፍራት የማይቻል መሆኑን የተረዳኸው::

ስለዚህ እኔና አንተም የሰዎችን ፍላጐት ለመረዳት እንሞክር:: ሰዎች ፈልገውን ይምጡ የሚለውን ዕምነት እናስወግድ:: እንዲህ ብናደርግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ጓደኞች ማፍራት እንችላለን::

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ እኔም አንተም በኑሯችን ውስጥ ለመታየት ውን ውን የሚሉ አያሌ ሰዎችን እናያለን:: እርግጥ ነው ይህ መንገድ ጓደኛ ለማፍራት አይጠቅምም:: ሰዎች ስላንተ ደንታ የላቸውም፤ ስለኔም ደንታ የላቸው:: ጧት፣ ቀን፣ ማታ ለራሳቸው ብቻ ነው የሚያስቡት::

አንድ የቴሌፎን ኩባንያ በስልክ ንግግሮች ውስጥ በከፍተኛ መጠን የሚደጋገመውን ቃል ለማወቅ አንድ ጥናት አካሄደ:: ተደጋግሞ የሚነገረውን ቃል ሳትደርስበት አልቀረህም:: ልክ ነህ «እኔ» የሚለው ቃል ነው:: «እኔ፣ እኔ» በአምስት መቶ የቴሌፎን ንግግሮች ውስጥ 3990 ጊዜ ተደጋግሞ ተነግሮ ነበር:: «እኔ፣ እኔ፣ እኔ፣ እኔ...» በዚህ ጥናት መሠረት ሰው ሁሉ ማንን እንደሚወድ አወቅህ?

ከብዙ ጓደኞችህ ጋር የተነሳኸው ፎቶግራፍ ቢቀርብልህ ቀድመህ የምታየው የማንን ምስል ነው?

ሰዎች ይወዱኛል ብለህ የምታስብ ከሆነ ይህን ጥያቄ መልስልኝ:: ዛሬ ማታ ብትሞት ነገ እቀብርህ ላይ ስንት ሰዎች ይገኛሉ?

ካልወደድካቸው ሰዎች አንተን የሚወዱበት ምን ምክንያት አለ?

እርሳስ ፈልገና መልሱን ፃፍ።

ሩጫችን ሁሉ ሰዎችን በማስደነቅ እንዲወዱን ለማድረግ ከሆነ የልብ ጓደኛ ልናገኝ አንችልም። አስታውስ የልብ ጓደኛ እኮ እንዲህ በቀላሉ አይገኝም። ታላቁ ናፖሊዮን ሞክሮት ያልተሳካለት ነገር ነው። ከዦሴፊን ጋር በመጨረሻ ባደረጉት ንግግር ላይ ናፖሊዮን፣

«ጆሴፊን እኔ በዓለም ላይ መልካም ዕድል ካጋጠማቸው ሰዎች አንዱ ነኝ። ሆኖም በዚች ቅጽበት ከልቤ የምተማመነው ባንቺ ነው» ብሏት ነበር። ታሪክ አዋቂዎች እሷንስ በርግጥ ያምናት ነበር? የሚል ጥርጣሬ አላቸው።

አልፍሬድ አድለር የተባሉት ታላቅ የአስትሪያ ሳይኮሎጂስት እንዲህ ይላሉ።

«በሰዎች ላይ ትልቅ ጉዳትን የሚያደርስ፣ በህይወቱም ከፍተኛ ችግር የሚያጋጥመው ሰዎችን ከልቡ የማይወድ ሰው ነው። የሰው ልጆች ደካማነትና ውድቀት የሚመነጨውም ከእንዲህ ዓይነቱ ሰዎች ነው።»

አንድ የታወቀ አሳታሚ ድርጅት የመጻሕፍት አዘጋጅ (Editor) ስለ አጫጭር ልቦለዶች አመራረጥ ሲያወሳ የሚጠቀምበት ዘዴ አንዱን ጽሁፍ አንስቶ ጥቂት አንቀጾች ካነበበ በኋላ ስለ ደራሲው የሚጠይቀውን ጥያቄ በመመለስ ነበር። ደራሲው ሰዎችን ይወዳል ወይስ አይወድም?

«ደራሲው ሰዎችን ከወደደ ሰዎች ድርሰቱን ይወዱለታል። ሰዎችን ከጠላ ድርሰቱም የተጠላ ይሆናል» ካለ በኋላ በመቀጠል፣ «ምንም እንኳ እየሰበኳችሁ መሆኔ ቢሰማኝም ለዚህ ይቅርታችሁን እየጠየቅሁ እላችኋለሁ። ጥሩ ደራሲ ለመሆን ከፈለጋችሁ ሰዎችን መውደድ

ማስፈለጉን አትርሱ።»

ሰዎችን መውደድ ልቦለድ ለመጻፍ ከረዳ አትጠራጠሩ ሰዎችን ለማትረብም ይረዳል።

ወ/ሮ ሹማን ሀይክን የተባለች ዘፋኝ በደረሱባት የተለያዩ ችግሮች ምክንያት ተስፋ ቆርጣ እራሷንና ልጆቿን እስከማጥፋት ደርሳ ነበር። ግን ጥርሷን ነክሳ ለሞያዋ ትኩረት ሰጥታ በመሥራቷ አድማጮቿን ሁሉ ለመማረክ ቻለች። አድማጮቿን ለመሳብ የተጠቀመችበት ዘዴ ምን እንደሆነ ስትጠየቅ፣ ስለሰዎች እንደምታስብና አድማጮቿን በጣም ትወድ እንደነበር ገልጻለች። ይህ ፍቅር በሰዎች ዘንድ ተወዳጅነትን አስገኝላት።

የታወቀው አስማተኛ ሀዋርድ ተርስተን ተደናቂነት ያገኘበትን ዘዴ ሲገልጽ፣

«እኔ ከሌሎች የተሻለ ችሎታ ኖሮኝ አይደለም። አብዛኛው ሰውም የአስማት ትዕይንት ብዙ መታለል እንዳለበት ያውቃል። ታዲያ ይህን እያወቀ የሚመጣውን ሰው ሌሎች 'ይህን ቂል ህዝብ እንጫወትበት፣ እናታልለው' ብለው ትዕይንታቸውን ይጀምራሉ። እኔ ግን ሰው የተሰበሰበው እኔን ለማየት በመሆኑ ባለውለታነቱ ይሰማኛል። የምወደውን ሥራ እየሠራሁ ኑሮዬን እንድመራ የሚረዱኝ እነሱ ናቸው። ስለዚህ ያለኝን ሁሉ ለነሱ እሰጣለሁ እላለሁ። እየህ ተመልካቾቼን በጣም እወዳለሁ።»

ሁላችንም ሥጋ ነጋዴ፣ እንጨት ፈላጭ፣ ሸማኔ፣ ደራሲም ሆን ሙዚቀኛ የሚያደንቁንን ሰዎች እንወዳለን። ስለዚህ ሌሎች እንዲወዱን እነሱን መውደድና ማድነቅ አለብን። ጊዜያችንን፣ ኃይላችንን፣ ሀሳባችንን ለነሱ መስጠት ይገባናል።

አንድ የታወቀ የእንግሊዝ ባለሥልጣን ደቡብ አሜሪካን ለመጐብኘት አቀደ። ጉዞውን ከመጀመሩ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ «የአገሩን ሥርዶ በአገሩ በሬ» እንዲሉ የእስፓኝ ቋንቋ አጠና። ደቡብ አሜሪካ ደርሶ በእስፓኝ ንግግር ሲያደርግ አገሬው በዚህ ድርጊቱ ወደደው።

በጣም ቀላል ነገር ልንገርህ። የጓደኞቼን የልደት ቀኖች እነሱ ሳያውቁት እየመዘገብኩ እስቀምጣለሁ። የአንዱ ጓደኛዬ የልደት በዓል በደረሰ ጊዜም የእንኳን አደረሰህ ደብዳቤ እጽፋለሁ፣ ወይም ቴሌግራም አደርግለታለሁ። ሰውዬው ስለኔ ምን ያህል እንደሚያስብ ገምተው። ለሱ በዚህች ዓለም ላይ እንደኔ ጓደኞቹን የሚያስታውስ ሰው ያለ አይመስለውም።

ሌላው የሠላምታ ጉዳይ ነው።

ጓደኛ ማፍራት ከፈለግህ ለሰዎች ሞቅ ያለና ናፍቆት የተቀላቀለበት ሠላምታ ስጣቸው። ስልክ በተደወለልህ ጊዜም የደወለልህን ሰው ድምጽ በመስማትህ መደሰትህን የሚገልጽ ሰላምታ ስጥ። ሀሉ ስትል እንኳ ድምጽህ ናፍቆትህን ይግለጽ።

**ስለዚህም ወዳጇ ሰዎች እንዲወዱህ የምትሻ ከሆን ታላቁ መመሪያ ይኸውልህ።**

**ሰዎችን ከልብህ ውደድ!**

# ምዕራፍ 11

## ከሰዎች ጋር እንዴት በቀላሉ መግባባት እንደሚቻል

አንዴ የአደራ ደብዳቤ ለመላክ ፖስታ ቤት ሰልፍ ይዤ ሳለ ደብዳቤዎችን የሚመዝነውና የሚመዘግበው ሰው ሥራው እንደሰለቸው ተመለከትኩ:: ሁልጊዜ ፖስታ መመዘን፣ ተገቢውን ቴምብር መስጠት፣ ገንዘብ መቀበል፣ ደረሰኝ መስጠት፣ ሥራው ከዓመት ዓመት ይህ በመሆኑ ሊሰለች ይገባዋል:: ስለዚህም ለራሴ እንዲህ አልኩት፣

«ያ ሰውዬ እንዲወደኝ ለማድረግ እሞክራለሁ:: እንዲወደኝ ለማድረግ ደግሞ ስለኔ ሳይሆን ስለሱ አንድ መልካም ነገር ጣል ማድረግ እንዳለብኝ እውቅ ነው:: ሰውዬው ላይ ከልቤ እንዳደንቀው የሚያደርግ ምን ጥሩ ነገር አለ? ይህ ጥያቄ አንዳንድ ጊዜ ለመመለስ አስቸጋሪ ነው:: በተለይ የማናውቃቸውን ሰዎች የሚመለከት ከሆነ:: ነገር ግን ያን ዕለት ቀላል ሆኖ ተገኘ:: ሰውዬው ላይ የማደንቀው ነገር ወዲያው ታየኝ::

ሰውዬው የኔን ደብዳቤ ሲመዝን ከልብ በመነጨ አነጋገር፣ 'እንዳንተ ዓይነት ጸጉር ቢኖረኝ እንዴት ደስ ይለኝ ነበር' አልኩት:: ደንገጥ አለና ቀና ብሎ በፈገግታ እየተመለከተኝ፣ 'እረ እንዲያውም እንደድሮው አይደለም' አለ በትህትና:: 'በጣም ቆንጆ ነው' ብዬ አረጋገጥኩለት:: እጅግ በጣም ተደሰተ:: ሁለታችንም ደስ እያለን ጥቂት ተጫወትን እና ስንለያይ እንዲህ አለኝ::

'ፀጉሬን የሚያደንቁ ብዙ ናቸው'::»

ያን ዕለት ያ ሰው ወደ ምሳው የሄደው በደስታ ሰክሮ በአየር ላይ እየተንሳፈፈ ነበር ለማለት እችላለሁ:: ማታ አቤቱ እንደ ደረሰ

ለሚስቱ ይህን አጋጣሚ እንደ ነገራት አልጠራጠርም። እቤቱ እንደገባ መስታወቱን እየተመለከተ «እንዴት ዓይነት ቆንጆ ፀጉር ነው» እንዳለ እተማመናለሁ።

ይህንን ታሪክ ለሰዎች ነገርኳቸውና ከመካከላቸው አንዱ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ። «ከሰውዬው ምን ለማግኘት ስለፈለግህ ነው እንደዚህ ያልከው? » ምን ነበር ለማግኘት የፈለግሁት? ምን ለማግኘት መሞከሬ ነበር?

የሚያስጠላ ራስ ወዳድነት ሰፍኖብን ምንም ደስታ የማናፈልቅና ጥቅም ካላየን በስተቀር ሰዎችን በማድነቅ ያንን ደስታ ወደ ሰዎች የማናስተላልፍ ከሆነ ከማይቀርልን ውድቀት ላይ እንደርሳለን።

በበኩሌ ከዚያ ሰው አንድ ጥቅም አግኝቻለሁ። ያም በገንዘብ የሚለካ አይደለም። ደስታ ሰጠሁት፣ ውለታ ጣልኩበት። እሱ ግን ውለታውን ለመመለስ መንገድ አልነበረውም። ውለታ ሳይጠብቁ ውለታ እንደመጣል የሚያስደስት ነገር የለም። በዚህ ዓይነት ያገኘኸው የርካታ ስሜት አጋጣሚው ካለፈ በኋላ ለረጅም ጊዜ በግ እያለ ሲያስደስትህ ይኖራል።

ስለሰው ልጆች ጠባይ አንድ ሁሌ የሚሠራ ህግ አለ። ያንን ህግ ብንከተል ወይም ለዚያ ህግ ብንገዛ በአብዛኛው ችግር አይገጥመንም። እንዲያውም ያ ህግ በተገዛንለት ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ጓደኞችና ቋሚ የሆነ ደስታን ያጐናጽፈናል። ለዚያ ህግ ባንገዛ ደግሞ መጨረሻ የሌለው ችግር ያጋጥመናል፣ ህጉ እነሆ!

<u>ሁልጊዜ ሌላው ሰው የተፈላጊነት ስሜት እንዲሰማው አድርግ።</u>

ከዚህ ቀደም እንደጠቀስነው ፕሮፌሰር ጆን ዲዊ ተፈላጊ የመሆን ምኞት በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ የሚገኝ ከፍተኛ ግፊት እንደሆነ

ይናገራሉ። ፕሮፌሰር ዊሊያም ጀምስም እንዲህ ይላሉ፤

«በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ዋናው ነገር በሌሎች የመሞገስ ጉጉት ነው።» ከዚህ በፊት እንዳመለከትኩት ይህ ስሜት ነው ከሌሎች እንስሳት የሚለየን። ይህ ስሜትም ነው ለሥልጣኔና ለዕድገት ምንጩ።

ዘወትር በምታገኛቸው ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖርህ ትፈለጋለህ? ችሎታህን በትክክል ሰዎች እንዲገነዘቡልህና በአካባቢህ ተፈላጊ መሆንክን እንዲያውቁልህ ትሻለህ? ተራና ከአንገት በላይ የሆነ ሽንገላ መስማት አትፈልግም ይሆናል። ከልብ ለመነጨ ሙገሳ ግን ትጓጓለህ። ጓደኞችህና አብረውህ የሚኖሩ ሰዎች ቻርለስ ሽዋብ እንዳለው ከልባቸው መቀበልና እንደተሰማቸው ማድነቅ የሚችሉ እንዲሆኑ ትመኛለህ? ሁላችንም እንፈልጋለን። ስለዚህም ወርቃማውን ህግ እንከተል።

<u>ሰዎች ሊያደርጉልን የምንፈልገውን እኛም ለሌሎች እናድርግ</u>!

የት? መቼ እናድርግላቸው? መልሱ ይኸውና፤ ሁልጊዜ፤ የትም ቦታ።

ለምሳሌ አንድ ቀን የአንድ የባለሥልጣን ቢሮ የት እንደሚገኝ እንግዳ ተቀባዩን ጠየቅሁት። ቆንጆ የደንብ ልብሱን ግጥም አድርጎ በኩራት መልከ ቃላቱን እየተጫነ እንዲህ ሲል መለሰልኝ። «ቢሮቸው... አሥራ ስምንተኛው ፎቅ... 1816 ቁጥር» ወደ አሳንሰሩ እየሮጥኩ ሄድኩን ድንገት ቀጥ አልኩ። ወደ እንግዳ ተቀባዩ ተመልሼ «ጥያቄዬን የመለስክልኝ አስደናቂ በሆነ መንገድ ነው። ግልጽና ትክክልም ነው። እንደ ሰዓሊ ነው ቁጭ ያደረግህልኝ። ይሄ ደግሞ የተለመደ አይደለም። እና እንዲህ ዓይነት ሠራተኛ በመሆንህ ደስ ይበልህ ልልህ ነው የተመለስኩት» አልኩት።

በደስታ እየተፍለቀለቀ በመልሶቹ መካከል አረፍ ይል የነበረው ለምን እንደሆነና እያንዳንዱን ቃል ለምን እንደተናገረ አስረዳኝ:: የተናገርኳቸው ጥቂት ቃላት የመንፈስ ኩራት ሰጡት:: ይህን ተናግሬ ወደ አሥራ ስምንተኛው ፎቅ ስገሰግስ በሰው ልጆች ደስታ ላይ አንድ ጠብታ እንደጨመርኩ ሲሰማኝ ደስ አለኝ::

ይህን ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል አምባሳደር ወይም የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ኃላፊ እስክትሆን መጠበቅ የለብህም፤ በየቀኑ ተአምር ልትሠራበት ትችላለህ::

ለምሳሌ ምግብ ቤት ገብተህ ቀይ ወጥ አዘህ ክትፎ ቢመጣልህ ይህን አላዘዝኩም ብሎ ከመቆጣት ይልቅ ረጋ ብለህ፤ «ሳስቸግርህ ቅር ይለኛል:: ሆኖም ከክትፎ ይልቅ ቀይ ወጥ ይሻለኛል:: ያዘዝኩትም እሱን ነበር» ብትል አሳላፊው «ነበር እንዴ? ግድ የለም ይለወጣል» ይልሃል:: አክብሮት ስላሳየኸውም ይደሰታል፤ ያከብርሃልም::

«ሳስቸግርህ ቅር ይለኛል፣ ይህን በማድረግ ብትረዳኝ፣ እባክህን ይህንን ብትረዳኝ ቅር ይልሃል፣ አመሰግናለሁ» እነዚህን የመሳሰሉ አጫጭር ሀረጎች የዕለት ከዕለት ኑሯችንን ሊያሻሽሉልን ከመቻላቸውም በላይ የጨዋነት ምልክቶችም ናቸው::

ከአንድ ጃፓናዊ የተሻልክ መስሎ ይሰማሃል? ይሰማህ ይሆናል:: በእውነቱ ግን ጃፓኖች ደግሞ ከአንተ የተሻልን ነን ብለው ያስባሉ:: እንዲያውም አንድ ጊዜ አንድ ሽወግ አጥባቂ ጃፓናዊ አንዲት ጃፓናዊት ወይዘሮ ከአንድ ፈረንጅ ጋር ስትደንስ አይቶ በቁጣ ሲገነፍል ታይቷል::

በህንድ ውስጥ ከሚገኙ ሂንዱዎች እበልጣለሁ ብለህ ታስባለህ? እንዲህ ማሰብ መብትህ ነው:: ግን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሂንዱዎች ደግሞ ካንተ እጅግ የላቁ መስሎ ይታያቸዋል:: ስለዚህም የረከሰ ነው

ብለው ስለሚያስቡ እቤትህ የበሰለ ምግብ እንኳ ለመቅመስ ይጠየፋሉ::

ከኤስኪሞዎች የበለጥኩ ነኝ ብለህ ታስባለህ? ግሰቡ አሁንም መብትህ ነው:: ግን ኢስኪሞዎች ስላንተ ምን እንደሚያስቡ ማወቅ ትፈልጋለህ? መልካም:: ከኤስኪሞዎች መካከል አብዛኞቹ እቤትህ ተቀጥሮ ከመሥራት ይልቅ በረሃብ መሞት ወይም በየመንገዱ መንከራተትን ይመርጣሉ:: በነሱ አስተሳሰብ ፈረንጅ የሚለው ቃል ራሱ እጅግ ቀፋፊ ነው::

እያንዳንዱ ከሌሎች አገሮች የመብለጥ ስሜት አለው:: ወኔና አርበኝነትን፣ ጦርነትን የሚያመጣው ይኸው ስሜት ነው::

ሀቁ ግን የምታገኘው ሰው ሁሉ በአንድ መንገድ ካንተ የበለጠ ሆኖ ይሰማዋል:: ስለሆነም ለስለስ ባለ መንገድ ተፈላጊ መሆኑንና ይህንንም ከልብህ እንደተረዳህለት መግለጽ ከሰውየው ጋር ልብ ለልብ ለመገናኘት የሚረዳህ ፍቱን መንገድ ነው::

ኤመርሰን ያለውን አስታውስ:: «የማገኘው ማንኛውም ሰው በአንድ መንገድ ከኔ እንደሚበልጥ አውቃለሁ:: ስለሆነም አንድ ነገር ከሱ እማራለሁ:: ስለሱም ለማወቅ ይረዳኛል::»

የሚያሳዝነው ነገር ግን አብዛኛው ሰው ያለው ዕውቀት በአንዳንድ ጉረኞች አባባልና ነቀፋ ይዋጥና እኔ ለዚህ ሥራ ብቁ አይደለሁም የሚል ስሜት እንዲያድርባቸው ያደርጋል:: ሊያቀጣጥል የሚችል ውስጣዊ ችሎታቸውን የውጪው ጫጫታና ግርግር፣ ትዕቢትና ተጽእኖ ያጠፋዋል:: እነኝህን ሰዎች ኑሮ ታቅለሸልሻቸዋለች::

ተንቀሳቃሽ ስዕሎችን ለመቅረጽ የሚያገለግለውን ፊልም የፈለሰፈው ጆርጅ ኢስትማን ነው:: ይህ ሰው ብዙ ሀብት የነበረውና

የታወቀ ነጋዴም ነበር:: ይህን ሁሉ ያከናወነ ሰው ቢሆንም እንደ እኔና እንዳንተ ለትንሽ ውዳሴ ይጓጓ ነበር::

ለምሳሌ ከአያሌ ዓመታት በፊት ኢስትማን የሙዚቃ ት/ቤትና ለእናቱ መታሰቢያ ደግሞ አንድ ቲያትር ቤት ያሠራ ነበር:: ጀምስ አዳምሰን የተባለ የአንድ ወንበር ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ለትያትር ቤቱ ወንበሮች ለማቅረብ ፈለገ:: ለመሀንዲሱ ስልክ በመደወል አቶ አዳምሰን ከአብ ኤስትማን ጋር ቀጠሮ ያዘ::

አዳምሰን ከቀጠሮው ቦታ እንደደረሰ መሀንዲሱ እንዲህ አለው:: «ወንበሮች ለመሸጥ እንደምትፈልግ አውቃለሁ:: እንዲሳካልህ ከፈለግህ ከጆርጅ ኢስትማን ጋር ከአምስት ደቂቃ በላይ አትነጋገር:: በሥራ የተወጠረ ስለሆነ ጊዜውን የሚሻማውን ሰው አይወድም፣ ስለዚህ ጉዳይህን ቶሎ ጨርሰህ ውጣ::»

አዳምሰን እንደተባለው ለማድረግ ተዘጋጅቶ ከመሀንዲሱ ጋር ገባ:: አቶ ኢስትማን እፊቱ ከተከመሩት ወረቀቶች አንዱን ያነብ ነበር:: አዳምሰን እንደገባ ኢስትማን ቀስ ብሎ መነጽሩን አወለቀና፣ «እንደምን አደርክ? ምን ልርዳህ» ብሎ ጠየቀው:: በዚህ ጊዜ ከአዳምሰን ጋር የገባው መሀንዲስ አስተዋወቃቸው:: አዳምሰንም እንዲህ አለ:: «ሥራህን ጨርሰህ ቀና እስክትል ቢሮህን እያደነቅሁ ነበር:: እንዲህ ዓይነት ቢሮ ቢኖረኝ ሥራ የሚሰለቸኝ አይመስለኝም:: እየህ የኔ ሥራ በእንጨት ሥራ ሞተሮች መካከል ስለሆነ እንዲህ ዓይነቱ ቆንጆ ቢሮ ሳይ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው::» ጆርጅ ኢስትማንም እንዲህ ሲል መለሰ፣

«አ! የረሳሁትን ነገር አስታወሰከኝ:: ይሄ ቢሮ ቆንጆ ነው? አይደለም? እንደተሠራ አካባቢ ለእኔም በጣም ነበር ደስ የሚለኝ::

ነገር ግን ዛሬ በአእምሮዬ ብዙ ነገር ስለሚጉላላ እውልበታለሁ እንጂ አስተውዬው አላውቅም::»

በዚህ ጊዜ አዳምሰን ጠጋ አለና አንድ መደርደሪያ እየነካካ «ከእንግሊዝ ዋርካ ነው የተሠራው አይደለም?» አለው:: «ከጣሊያን ዋርካ ትንሽ ለየት ይላል» አለ::

«አዎ ከእንግሊዝ አገር የመጣ ዋርካ ነው:: የመረጠልኝ አንድ የእንጨት ዓይነቶችን የሚያውቅ ጓደኛዬ ነው» አለ ኢስትማን:: ከዚህ ቀጥሎ በክፍሉ ውስጥ የሚገኙትን ከእንጨት የተሰሩ ዕቃዎች እያመለከተ ስለአመጣጠናቸው፣ ስለቀለም ቅባቸው እንዴት በእጅ ተቀርጸው ጌጥ እንደወጣላቸውና ስለሌላውም ሁኔታ ካስረዳው በኋላ ዕቃዎቹ በሚሰሩት ጊዜ ዲዛይን በማውጣትና በመገጣጠም ሥራ ላይ እሱም እንደተሳተፈ ነገረው:: በክፍሉ ውስጥ እየተዘዋወረ ዕቃዎቹን እያደነቁ አንድ መስኮት አጠገብ ቆም አሉ:: ጆርጅ ኢስትማን በተለመደው ለስላሳ አነጋገሩ የሰውን ልጅ ለመርዳት ያቋቋማቸውን አንዳንድ ድርጅቶች ለምሳሌ አንድ ዩኒቨርስቲ፣ ሆስፒታል፣ የመጠሪያ ቤት፣ የህፃናት ሆስፒታል፣ የመሳሰሉትን ነገረው:: አዳምሰን ለእንደዚህ ዓይነት በጐ ተግባር ገንዘቡን የሚያወጣ ሰው ደስ እንደሚያሰኘውና እንዲህ ዓይነት ሰው በማግኘቱም ይበልጥ እንደተደሰተ ገለጸለት::

ጆርጅ ኢስትማን ባለመስታወት ከመዲና ከፍቶ ካሜራ አወጣ:: በህይወቱ ያለዚህ ካሜራ ሌላ አልነበረውም:: ካሜራው ከእንግሊዝ አገር የተገዛ ነበር::

አዳምሰን ኢስትማን እዚህ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ያለፈባቸውን ሁኔታዎች በዝርዝር ይጠይቀው ጀመር:: ኢስትማንም ከልቡ በልጅነቱ

ስለነበረበት ድህነት፣ እናቱ ቀላቢት ሆና እሱ ደግሞ አንድ ኢንሹራንስ ቢሮ ውስጥ በቀን ሃምሳ ሣንቲም እየተከፈለው ይሠራ እንደነበር በሰፊው ተረከለት። ኢስትማን በሚተርክበት ጊዜ አዳምሰን ቀስ ብሎ ጥያቄዎችን እየሰነዘረ በተመሰጦ ያዳምጠው ነበር።

ጀምስ አዳምሰን ወደ ኢስትማን ቢሮ የገባው በአራት ሰዓት ከሩብ ሲሆን ከአምስት ደቂቃ የበለጠ እንዳይቆይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ነበር፤ ነገር ግን እዚያው እንደተቀመጠ ሁለት ሰዓት አለፈ። ሆኖም ወሬያቸው አላበቃም ነበር። በመጨረሻ ኢስትማን ወደ አዳምሰን ዞር ብሎ እንዲህ አለው።

«በቅርቡ ጃፓን ሄጄ ሳለ ጥቂት ወንበሮች ገዝቼ እመዝናኛዬ ቦታ አስቀመጥኳቸው። ይገርምሃል ጥቂት እንደቆዩ ፀሐዩ ቀለማቸውን ሳጠው። ቀለም ገዛሁና ቀባኋቸው። ምን ዓይነት የቀለም ቅብ ሥራ እንደምሠራ ማየት ትፈልጋለህ?»

«እንዴታ»

«እንግዲያስ አብረን ወደ ቤት እንሂድና ምሳችንን በልተን አሳይሃለሁ።»

ከምሳ በኋላ ከጃፓን ያመጣቸውን ወንበሮች አሳየው። እያንዳንዳቸው ከብር ከሃምሳ በላይ የሚያወጡ አልነበሩም። ግን በንግድ አለም በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ ሰው ጆርጅ ኢስትማን እነኚህ ወንበሮች ስላሉት ኩራት ይሰማው ነበር። ምክንያቱስ? ቀለም የቀባቸው ራሱ ነዋ።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ አዳምሰን ሄደ። ለትያትር ቤቱ የሚያስፈልጉትን ወንበሮች ግምት ዘጠና ሺህ ብር ደረሰ። ጨረታውን ማን ያሸነፈ ይመስልሃል? ጀምስ አዳምሰን ወይስ ከተፎካካሪዎቹ አንዱ?

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ኢስትማን እስከሞተበት ዕለት ድረስ ሁለቱ ሰዎች የቅርብ ጓደኞች ነበሩ።

ይህን አንድን ሰው የማሞገስ ድንጋይ የሚያለሰልስ ተአምር እኔና አንተ የት ቦታ በስራ ላይ እናውለው? ለምን ከቤታችን አንጀምርም? እንዲያውም ከቤታችን የበለጠ አስፈላጊ የሚሆንበት ግን በሥራ ላይ የማይውልበት ቦታ የለም። ባለቤትህ አንዳንድ ጥሩ ነገሮች ሳይኖሯት አይቀርም። ቢያንስ በዕድሜህ አንድ ጊዜ ጥሩ ነገር እንዳላት አይተህ ነበር። ያ ባይሆንማ አታገባትም ነበር። ግን እስኪ አስበው። ስለቁንጅናዋ አድናቆትህን ከገለጽክላት ስንት ዓመት አለፈ? አስታውስ! ያላገባሃትን ሴት ማሞካሸት የፍላጐት ጉዳይ ነው። ያገባሃትን ሴት ማሞካሸት ግን አስፈላጊ ነው። ኑሮህን የተስተካከለ ያደርገዋልና። እንዲህም ስለተባለ ትተኸው የኖርከውን ነገር በድንገት አትጀምረው። ሚስትህ ትጠራጠራለችና። ዛሬ ወይም ነገ ማታ ቀለል ያለ ስጦታ ይዘህላት ግባ። ስጦታም ብቻ ሳይሆን ፈገግታና ሞቅ ያሉ የፍቅር ቃላትም ያስፈልጋታል። ይህን ነገር ብዙ ባሎችና ሚስቶች ቢፈጽሙ ዛሬ ያለው የትዳር መፋለስ ይቀንስ ነበር።

አንዲት ሴት እንድታፈቅርህ ማድረግ ትፈልጋለህ? ደግ። ሚስጥሩ ይኸው በትክክል ይሠራል። ግን የኔ ሀሳብ አይደለም። ከዶሮቲ ዲክስ ነው የተበደርኩት። ዶሮቲ ዲክስ አንድ ጊዜ የሃያ ሦስት ሴቶችን ልብ ያረካና ያላቸውን ገንዘብ ሁሉ በሱ ስም እንዲያዛውሩ ያደረገ ሰው አነጋግራ ነበር። (በነገራችን ላይ ይህን ሰው ያነጋገረችው እስር ቤት ውስጥ ነው) የሴቶችን ልብ ለመማረክ ወይም ፍቅር ለማስያዝ የቻልከው በምን ዘዴ ነው? ብላ ጠየቀችው። ጥያቄውን ሲመልስ ምንም የማታለል ዘዴ እንደማይጠቀም ገልጾ፣ ማድረግ ያለብሽ ለሴት

ልጅ ስለራሷ ማውራት ነው ብሏል።

ለወንዶችም ይኸው ሀቅ ይሠራል። «አንድ ሰው ስለራሱ እውራለት» ብሏል ዴዝሬሊ። «ስለራሱ አውራለት የፈለገኸውን ሰዓት ያህል ያዳምጥሃል።» ስለዚህ ወንድሜ ሆይ በሰዎች ዘንድ መወደድ ብትሻ የሚከተለውን መመሪያ አጢን።

ሰውየው የተፈላጊነት ስሜት እንዲሰማው አድርግ፤ ይህንንም ከልብህ ፈጽመው።

አሁን ይህን መጽሐፍ እጠፍና ይህንን በማምገስ ሰዎችን የማትቀረብ ፍልስፍና አጠንቅቀህ ባለው ሰው ላይ ሞክረው፤ እና ተአምር ሲሰራ ታየዋለህ።

pdf by @shuktuss ሹክቱስ

t.me/BooksandYou

# ክፍል ሦስት

ሰዎችን ለማሳመን የሚረዱ መንገዶች

# ምዕራፍ 12

## ጠላት ለማፍራት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል

አንድ ሰው ስህተት መሥራቱን በንግግር የምትገልጽለትን ያህል በማየት፣ በድምጽ አወጣጥህና በሰውነት እንቅስቃሴህ ልትገለጽለት ትችላለህ። ተሳስተሃል ብለህ ንገረው እንበል። ስህተቱን አምኖ የሚቀበል ይመስልሃል? በፍጹም። ምክንያቱም እውቀቱን የማመዛዘን ችሎታውን፣ ኩሩነቱንና ለራሱ ያለውን ክብር ስላጣጣልክበት ሊቀበልህ አይችልም። እንዲያውም አጸፋውን እንዲመልስ ይገፋፋል። ከዚህ በኋላ የአፍላጦንን ወይም የኢማኑኤል ካንትን ሎጂክ እንኳ ብታቀርብለት በጄ ብሎ አይቀበልህም።

ምንጊዜም ቢሆን «ይህንን ነገር ላስረዳህ» ብለህ አትጀምር መጥፎ ነው። ይህንን ነገር ላስረዳህ ብለህ ስትጀምር ሰውየው የሚሰማህ፣

«እኔ ካንተ የተሻልኩ ነኝ አዳምጥኝና ሀሳብህን ላስለውጥህ» ብሎ ነው።

ይህ ደግሞ የሰውየውን ክብር ይነካዋል። ቅራኔ ይቆሰቁሳል። ሰውዬው መናገር ከመጀመርህ በፊት ጠብ ይፈጥራል። በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የሰዎችን ሀሳብ ማስለወጥ ከባድ ነው። ስለዚህ ለምን በጠማማ መንገድ ትጀምራለህ? ለምን ሰንካላውን መንገድ ትመርጣለህ?

ለአንድ ሰው አንድ ነገር ለማስረዳት ስትሻ ለማስረዳት መሻትህን ማንም ሰው አይወቅብህ። ለዘብ ብለህ በዘዴ ግባበት።

ሎርድ ቼስተርፊልድ ለልጁ እንዳለው «ከቻልክ ከሰዎች የተሻለ አዋቂ ሁን። ነገር ግን አዋቂ ነኝ አትበላቸው።»

ከሃያ አመታት በፊት እምንባቸው ከነበሩ ነገሮች መካከል ዛሬ የማምንበት የጊዜ ቤት ሠንጠረዥን ብቻ ነው:: ስለ እንስታይን ሳነብማ የጊዜ ቤት ሠንጠረዦቼንም እጠራጠረዋለሁ:: ከሃያ አመት በኋላ ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያልኩትን ነገር ሁሉ ላላምንበት እችላለሁ:: ስለ ብዙ ነገሮች ሳስብ እንደ ቀድሞው እርግጠኛ አልሆንም:: ሶቅራጥስ ለተማሪዎቹ እየደጋገመ እንዲህ ይላቸው ነበር ይባላል::

«አንድ ነገር ብቻ አውቃለሁ:: ምንም ነገር አለማወቄን» እንዲህ ከሆነ እኔ ከሶቅራጥስ በላይ ነኝ ብዬ ተስፋ አላደርግም:: ስለዚህም ሰዎችን ተሳስታችኋል ማለትን ትቻለሁ:: ይህም ዋጋ እንዳለው ተገንዝቤያለሁ::

አንድ ሰው ስህተት ነው ብለህ የምትገምተውን ወይም የምታምነውን ነገር ቢናገር እንዲህ ብሎ መጀመሩ የሚሻል አይመስልህም?

«እሃ... እንዲያ ነው? እኔ ደግሞ የማስበው ትንሽ ለየት ይላል:: በእርግጥ ተሳስቼ ሊሆን ይችላል:: አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ እሳሳታለሁ:: ሆኖም በደንብ እንዲገባኝና እንዳስተካክለው ስለምፈልግ እስኪ ነገሩን በደንብ እንመርምረው» ይህ እንግዲህ ትልቅ ተአምር ነው:: ብዙ ለውጥም ያሳይሃል:: ተሳስቼ ይሆናል ትለዋለህ ደስ ይለዋል:: መሳሳቱን ለማሳየት ደግሞ እስኪ ነገሩን እንመርምረው ትለዋለህ:: ውይይቱ በመግባባት መንፈስ ይቀጥላል:: ከሰማይ በላይ የመጣም ቢሆን ከመሬት በታች የፈለቀም ቢሆን ወይም ከባህር ውስጥ የሚኖር ነገር ተሳስቻለሁ ካልከው አይቃወምህም::

አንድ ሳይንቲስት ያደረገው እንደዚህ ነው::

አንድ ጊዜ ስቲፈንሰን የተባለውን የታወቀ እሳሽና ሳይንቲስት

እነጋግሬው ነበር። ስቲፈንሰን ለአሥራ አንድ ዓመታት ያህል አርክቲክ ዋልታ አካባቢ የቆየና ለስድስት ዓመታት ያህል ሥጋና ውሃ ብቻ በመመገብ የቆየ ሰው ነው። አንድ ትልቅ ሙከራ እንዳከናወነ ሲነግረኝ ምን ለማግኘት ሙከራውን እንደሰራው ጠየቅሁት። መልሱን መቼም አልረሳውም። እንዲህ ነበር ያለኝ።

«አንድ ሳይንቲስት አንድ ነገር ለማረጋገጥ አይሞክርም። አንዳንድ እውነታዎችን ለማግኘት ብቻ ይሞክራል።» እንደ ሳይንቲስት ለማሰብ ትፈልጋለህ? አይደለም እንዴ? ታዲያ ማን ከለከለህ? ራስህ አይደለህምን?

ተሳስቻለሁ ብለህ በማመን የሚደርስብህ ችግር የለም። እንዲያውም የምታነጋግረው ሰው ጭቅጭቁን እንዲያቆምና እንዳንተ ግልጽና ሰፋ ያለ አመለካከት ያለው ሰው መሆን እንዲፈልግ ታደርገዋለህ። ተሳስቼ ይሆን? ስትለው አይ እኔም ተሳስቼ ሊሆን ይችላል እንዲልህ ታደርገዋለህ።

አንድ ሰው መሳሳቱን በትክክል ብታውቅና ይህንንም ፊት ለፊት ብትነግረው ምን የሚከተል ይመስልሃል? ጭቅጭቅ።

ጥቂት ሰዎች ናቸው እውነትን ተከትለው የሚጓዙ። አብዛኞቻችን አስቀድሞ በያዝነው ጥላቻ ወይም በተሳሳተ እምነት የተሞላን ነን። አብዛኞቻችን ያለችንን እውቀት እንደ እውቀት መጨረሻ የምንቆጥር፣ በቅናት፣ በጥርጣሬ፣ በፍርሃት፣ እና በእብሪት የተወጠርን ነን። እምነታችንንም በቀላሉ ለመለወጥ ዝግጁ አይደለንም። ስለዚህ ለክርክር የምንደረድራቸው ምክንያቶች ሁሉ ቀድሞ የነበረንን እምነት ሳለመለወጥ የምናቀርባቸው መሆናቸውን አውቀን ይህም አጉል ግትርነት መሆኑን ተገንዝበን የሌሎች አስተሳሰብ ከኛ አስተሳሰብ ጋር

በማጣጣም ስህተታችንን አምነን ለመታረም መቻል ይኖርብናል።

ስንሳሳት ስህተት መሆኑን ራሳችን እናውቀው ይሆናል። እናም በለዘብታና በዘዴ መሳሳታችንን ከተናገርን ስህተት መስራታችንን በማንም ሰው ፊት ለማመን አናፍርም። እንዲያውም ስህተት መስራታችንን ለመናገር በመድፈራችን ኩራት ይሰማናል።

ቤንጂያሚን ፍራንክሊን በወጣትነቱ ተከራካሪና እውነቱን በግድ ለማሳመን የሚጥር ሰው ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ከጓደኞቹ ጋር ሲከራከር አንድ ፈዘኛ ጓደኛው ለብቻው ጠርቶ እንዲህ አለው።

«ቤን አስቸጋሪ ሰው እኮ ነህ። የሚቃወሙህን ሰዎች ሁሉ በነገር ጥፊ ታጮላቸዋለህ። ጥረትህ የሰዎችን እምነት ለመለወጥ ስለሆነ ማንም ሊሰማህ አይፈልግም። እንዲያውም እንዳየሁት ጓደኞችህ ተዝናንተው የሚጫወቱት አንተ ሳትኖር ነው። እርግጥ ነው ብዙ ታውቃለህ። ስለዚህ አንተን መምከር ያስቸግራል። እንዲያውም ማንም ሰው ምንም ነገር ሊያስረዳህ አይሞክርም። ምክንያቱም ኃይለኛ ክርክር እንደሚገጥመው አስቀድሞ ያውቃል። ስለዚህ ከአሁን በኋላ ባለህ ዕውቀት ላይ የምትጨምር አይመስለኝም። የምታውቀው ደግሞ በጣም ትንሽ ነው።»

ስለቤንጃሚን ፍራንክሊን ከማውቃቸው መልካም ነገሮች አንዱ ይህንን የሚቆጠቁጥ ዘለፋ አዘል ምክር በጸጋ መቀበሉን ነው። ቤንጃሚን ፍራንክሊን አዋቂና ትልቅ ሰው ስለነበር ይህን ወደ ውርደትና ውድቀት የሚያመራውን ሁኔታ ለመገንዘብና በወቅቱ ለማረም ችሏል።

«ከዚያ በኋላ» ይላል ፍራንክሊን «የሌሎችን አስተያየት በቀጥታ ከመቃወምና የእነሱን አስተያየት እንዳመጣልኝ ከመውንዘር መቆጠብ ጀመርኩ። ይህም ብቻ አይደለም። ትክክል ነኝ ሊያሰኙ

የሚችሉ እንደ 'በርግጥና' 'የማይጠረጠር' የመሳሰሉ ቃላትን እርግፍ አድርጌ ትቼ በምትካቸው 'እንደሚመስለኝ' ደግሞ 'ሳስበው' 'ለእኔ እንደሚታየኝ ከሆነ' የሚሉና የመሳሰሉ ቃላትና ሐረጐችን ተካሁ።

ይህ አቀራረብ ምንም እንኳ ስጀመረው ከፍተኛ ችግር ቢፈጥርብኝም እየቆየሁ ስለለመድኩት እየቀለለኝ መጣ። እንዲያውም ከዚያ ጊዜ ወዲህ ባሉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ ያስተሳሰብ ግትርነትን (ቀኖናዊነትን) የሚጠቁም ቃል ወይም ሐረግ ተንፍሼ አላውቅም።»

ኢፍ ጂ ማሆኒ የተባለ የነዳጅ ዘይት ማጣሪያ ዕቃዎች ፋብሪካ ሥራ አስኪያጅ አንድ ጊዜ ያጋጠመውን እንዲህ ብሎ አጫውቶኛል።

«አንድ ሰሞን ልጠቅሰው የማልፈልግ የነዳጅ ዘይት ማጣሪያ ድርጅት ኃላፊ የተለያዩ ዕቃዎችን እንድሰራለት ጥያቄ ባቀረበልን መሠረት የዕቃዎቹን ንድፍ አዘጋጅተን አቀረብንለት፤ ተስማማ። ዕቃዎቹን ለመሥራት ተዋዋልን። በመካከሉ አንዳንድ በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች ዕቃዎቹ በተገቢው ሁኔታ ያለመሰራታቸውን ስለነገሩት በመካከላችን አለመግባባት ተፈጠረ። ሰውዬው ስልክ ደውሉ ዕቃዎቹን ማምረት እንድናቆም ሲነግረኝ መለስ ብዬ የዕቃዎቹን ንድፍ ተመለከትኩ። ምንም ስህተት አልነበረበትም። ጓደኞቹ ስለ እንደዚህ ዓይነት ዕቃ ምንም እንደማያውቁም ተገንዘብኩ። ነገር ግን ሰውዬውን በቀጥታ ተሳስተሃል ማለቱ አደገኛ እንደሆነ ስለተረዳሁ ዝም ብዬ ወደ መሥሪያ ቤቱ ሄድኩ። ቢሮው እንደ ገባሁ ሰውዬው እሳት ለብሶ እሳት ጐርሶ ጠበቀኝ። እየጮኸ ዛተብኝ። ቀጥሎም፤ 'እሺ አሁንስ ምን ልትሠራ ነው የመጣኸው?' ሲል ጠየቀኝ። ረጋ ብዬ እሱ እንድንሠራለት የሚፈልገውን ሁሉ ለመፈጸም ዝግጁ መሆኔን ነገርኩት።

'ክፍለህ ስለምታሠራን በፈለከው ገንዘብ፤ የምትፈልገውን ዓይነት

ማገኘት አለብህ። ሆኖም የኃላፊነት ጉዳይም አለ። ይህን ኃላፊነት አንድ ሰው መውሰድ አለበት። በፈለግኸው መንገድ ይሠራ ካልክ ንድፉን አዘጋጅና ስጠን። ምንም እንኳ እስከዛሬ ለዚህ ሥራ እስከ 200 ብር ወጪ ብናደርግም አንተን ለማስደሰት ኪሳራውን ችለን በሰጠኸን ንድፍ መሠረት እንሠራልሃለን። አንድ ነገር ግን ሳስጠ ንቅቅህ እወዳለሁ። በዚህ መሠረት ይሠራ ብለህ ስህተት ቢፈጠር ኃለፊነቱ የራስህ ይሆናል። እኛ በነደፍነው መሠረት ተሠርቶ ስህተት ቢፈጠር ኃላፊነቱ የእኛ ይሆናል።'

እንዲህ ስለው ቀዝቀዝ አለ። በመጨረሻም 'እሺ ቀጥሉ ግን ከተሳሳታችሁ እናንተን እያድርገኝ' አለኝ። በእኛ ንድፍ መሠረት ዕቃዎቹን ሠራን። ምንም ጉድለት አልታየባቸውም። ከዚያ በኋላ ሰውዬው ደንበኝነቱን በማጠናከር በአሁኑ ጊዜ ሌሎች መሳሪያዎችን እንድንሠራለት ውል ሰጥቶናል።

ሰውዬው ሲደነፋ ሲያንጓጥጠኝ ለመታገስ ያጠፋሁት ጉልበት በቀላሉ የሚገመት አልነበረም። ሆኖም በኋላ ዋጋ ያለው ሆኖ ተገኘ። ልክ አይደለህም ሲለኝ አንተም ልክ አይደለህም ብለው ኖሮ የሚነሳውን ጭቅጭቅ አሰቡት። ምናልባትም እስከመካሰስ፣ ቂም እስከመያያዝ፣ ገንዘብ አለአግባብ እስከማባከን እንደርስ ነበር። ያም ብቻ አይደለም ይህንን የመሰለ ደንበኛም እናጣ ነበር። ዛሬ ገብቶኛል። አንድን ሰው በቀጥታ ልክ አይደለህም ማለት ትርፉ ጠላት ማፍራት ብቻ ነው።»

ስለዚህ ጠላት ሳታፈራ የሰዎችን አስተሳሰብ ለመለወጥ ከፈለግህ የሚከተለውን ወርቃማ መመሪያ ተጠቀም።

ሰዎች የሚሰጡትን አስተያየት አታጣጥል።

ስህተት ሲነገር ብትሰማ በቀጥታ ስህተት ነው ብለህ አትቃወም።

# ምዕራፍ 13

## ወደ ሰዎች የአስተሳሰብ አድማስ የሚመራ ጥርጊያ መንገድ

ተናደህ ክፉ ቃል ተናግረህ ቢሆን የቁጣ ስሜትህን በማብረድህ ቀለል ሊልህ ይችል ይሆናል። ነገር ግን ስለምትቆጣው ሰውስ አሰበሃል? እንዳንተ ቀለል የሚለው፣ ደስታህን የሚካፈል ይመስልሃል? ያንተን በጥላቻ የተሞላ ድምጽ፣ ያንተን የጥላቻ አስተያየት እያየ በቀላሉ ካንተ ጋር ለመግባባት የሚችል ይመስልሃል?

«ቡጢ ጨብጠህ ብትመጣብኝ» ይላል ዊድሮው ዊልሰን «እኔ ደግሞ ካንተ የበለጠ ተዘጋጅቼ እንደምጠብቅህ ቃል እገባለሁ። ነገር ግን በጥሞና ቀረብ ብለህ እስኪ እንመካከር፣ በሀሳብ ካልተግባባን ያልተግባባንበትን ነጥብ እንመርምረው ብትለኝ ወዲያውኑ ብዙም እንደማንራራቅ ይገባኛል። የምንግባባቸው ነጥቦች ከማንግባባቸው ነጥቦች እንደሚበልጡ እረዳለሁ። በዚህ ላይ ትዕግስትና ችሎታ ሲታከል ሁለታችን ልንስማማ እንችላለን።»

አብርሃም ሊንከን እንዲህ ይላሉ፣ «ከአንድ እንስራ ሆምጣጤ ይልቅ አንድ ጠብታ ማር ብዙ ንቦችን ትሰባለች የሚል የቆየ ተረት አለ። ይህ ተረት ለሰዎችም ይሪዳል። አንድ ሰው ያንተን አላማ እንዲከተል ለማድረግ በመጀመሪያ የልብ ጓደኛው መሆንህን እንዲያምን አድርግ። የሰውዬውን ልብ ለማግኘት የሚረዳህ የማር ጠብታ ይህ ነው። የሰውዬውን ልብ ማግኘት ማለት ወደ አስተሳሰቡ አድማስ የሚመራ ጥርጊያ መንገድ ነው።»

በእንደቡተ ርቱዕነት የታወቀው ዳንኤል ዌብስተር የተባለው ጠ

በቃ ፍርድ ቤት ቀርቦ አንድ ነገር ለማስረዳት የሚጀምረው በሚከተሉት ሐረጐች ነበር።

«ጉዳዩን ክቡር ፍርድ ቤቱ ባይስተውም የተከበራችሁ ዳኞች ይህ ነገር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መስሎ ይታየኛል። ምንም እንኳ ለክቡር ፍርድ ቤቱ የተሰወረ ባይሆንም አንዳንድ ነጥቦችን እንዳቀርብ ይፈቅድልኝ። የተከበራችሁ ዳኞች ባላችሁ የሰው ልጆችን ተፈጥሮ የማወቅ ችሎታ ያነሳናቸውን ነጥቦች ጠቃሚነት በቀላሉ እንደምትገነዘቡት እተማመናለሁ።»

ዌብስተር ነገር መሰንጠቅ፣ ማስፈራራት፣ ደረቅ ምክንያት በመደርደር ሰዎችን በግድ ለማሳመን መሞከር የመሳሰሉ ነገሮችን አይጠቀምም ነበር። በእነኝህ ፋንታ ለስለስ ያለ፣ የሰከነና ፍቅር የተሞላበት አቀራረብ በመጠቀሙ ትልቅና ዝነኛ ጠበቃ ለመሆን በቃ።

የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ እንድትሸመግል ወይም ፍርድ ቤት በጥብቅና እንድትቆም የሚጠይቅህ ሰው ላይኖር ይችላል። ነገር ግን የምትገዛው ቆም ሳጥን ዋጋ ተከራክረህ ማስቀነስ ሳያስፈልግህ አይቀርም። ለዚህ ጉዳይ በፍቅር ሰዎችን መቅረብ የሚረዳህ ይመስልሃል? እስቲ እንመልከት።

አቶ እስትሮብ የተባለ አንድ መሀንዲስ የቤት ኪራይ እንዲቀነስለት ፈለገ። የቤቱ ባለቤት ግትርና ጨቅጫቃ ነበር። ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ሌሎች ተከራዮች ሞክረው እንዳልተሳካላቸው ቢያውቅና አፓርትመንቱን ብዙ ሰው እንደሚፈልገው ቢረዳ እስትሮብ ደፍሮ የገባውን ውል እንደጨረሰ ለባለቤቱ ቤቱን የሚለቅ መሆኑን ገልጾ ጻፈለት።

«ባለቤቱና ጸሐፊው ሊያነጋግሩኝ መጡ» ይላል እስትሮብ። «ፈገግታ የተሞላ ሰላምታ ሰጠኋቸው። ያለኝን መልካም ስሜት በመግለጽ ስለጤንነታቸው ጠየቅኋቸው። ልብ አድርግ ስለ ኪራይ መቀነሱ ጉዳይ ወዲያው አላነሳሁም። ቤቱ በጣም ደስ እንደሚለኝና እያያዙም ጥሩ እንደሆነ ለባለቤቱ ገለጽኩለት። እያደገም ኪራይ ባይበዛብኝ ኖሮ ዕድሜ ልኬን ብኖርበት እንደማይከፋኝ ነገርኩት። ለካ እንዲህ ዓይነት አቀባበል በዕድሜው ሙሉ አይቶ አያውቅም ኖሯል። ስለዚህ እነጋገሬን ሲሰማ ጆሮውን ማመን አቅቶት በደስታ ፈነደቀ።

ከተከራዮቹ ጋር ስላለበት ችግር በሰፊው አወራልኝ። ለምሳሌ ከተከራዮቹ አንዱ አስራ አራት ደብዳቤዎች እንደጻፈለትና ግማሹ ያህል በስድብ የተሞሉ እንደነበሩ ነገረኝ። አንደኛው ደግሞ ጉረቤቱ ያለው ተከራይ ማንኮራፋቱን እንዲያቆም ካላደረገ የውሉ ጊዜ ሳያልቅ ቤቱን ለቆ የሚሄድ መሆኑን በማስፈራራት እንደነገረው አጫወተኝ። 'እንደ አንተ ዓይነት ረክቶ የሚያመሰግን ተከራይ በማግኘቴ ምን ዓይነት የመንፈስ እርካታ ሰጠኸኝ መሰለህ?' ቀጥሉ እኔ ቀንስልኝ ብዬ ከመጠየቄ በፊት ራሱ 'ከፈለግህ ኪራዩን ልቀንስልህ' አለኝ። ተስማማሁ። ቅናሽ ተደርጉለኝም ኪራዩ ትንሽ እንደሚበዛብኝ ገልጬ ልከፍል የምችለውን ነገርኩት። አላወላወለም በደስታ ተቀበለኝ። እንዲያውም ሲያልፍ ዞር ብሎ 'ክፍሏን ላድስልህ ምን ዓይነት ቀለም ትመርጣለህ?' ብሎ ጠየቀኝ።

ይኸውልህ ሌሎች ተከራዮች ባፈሩት ዘዴ ኪራይ ማስቀነስ ብሞክር ኖሮ አይሳካልኝም ነበር። ሆኖም በፍቅር፣ በመተዛዘን በመደናነቅ መንገድ ስቀርበው ያሰብኩት ተሳካልኝ።»

በልጅነቴ ያነበብኩት አንድ ተረት ትዝ ይለኛል።

ከዕለታት አንድ ቀን ፀሐይና ነፋስ እኔ ነኝ ኃይለኛ፣ እኔ ነኝ ኃይለኛ በመባባል ተፎካከሩ። ነፋሱ ፀሐይን አላት። «ኃይለኛነቴን በተግባር አሳይሻለሁ። እዚያ ታች ካፖርት የለበሰ አዛውንት ይታይሻል? አንቺ ካፖርቱን ለማስወለቅ ግማሽ ሰዓት ሲወስድብሽ እኔ በአምስት ደቂቃ ውስጥ አስወልቀዋለሁ» አላት። ፀሐይ በደመና ተጋረደች። ነፋሱ አውሎ ነፋስ እስኪሆን አቧራውን እያጨሰ ነፈሰ። ኃይሉ በጨመረ ቁጥር አዛውንቱ ካፖርታቸውን ይበልጥ ጥብቅ አድርገው ያዙ። ነፋሱ መረታቱን ሲያውቅ ጸጥ አለ።

ወዲያው ፀሐይ ብቅ አለችና ሞቅ ያለ ፈገግታዋን አዛውንቱ ላይ ፈነጠቀችባቸው። በዚህ በደስታ የተዋጡት አዛውንት ላባቸውን ጠረግ ጠረግ አደረጉና ካፖርታቸውን አወለቁ። ይህን ያየችው ፀሐይ ወደ ነፋሱ ዞር ብላ፣ «አየኸው ከኃይልና ከጩኸት ይልቅ ፍቅርና ትህትና ጠንካራ ናቸው» አለችው። የዚህ ተረት ደራሲ የነበረው ግሪካዊው ኤሶፕ ከዛሬ 2500 ዓመት በፊት የኖረ ፈላስፋ ነው። በዚህ ዘመን ኤሶፕ ስለሰው ልጆች ተፈጥሮ በተረቱ የተናገረው እውነት ዛሬም ነገም ይሰራል። ፀሐይ ካፖርትህን በፈገግታዋ እንደምታስወልቅህ ሁሉ ሰዎችንም በርህራሄና በፍቅር ከቀረብካቸው ከማንኛውም ሰባኪ ይበልጥ አንተን ይቀበሉሃል። አብርሃም ሊንከን ያለውን አትርሳ።

«ከአንድ እንስራ ሀሞት ይልቅ አንድ ጠብታ ማር ብዙ ንቦችን ትሰባለች።» ስለዚህም፣

**አንተ በምታምንበት ነገር ሰዎች እንዲያምኑ ለማድረግ**
**የሚከተለውን ልብ በል።**
**ነገርህን ሁሉ በፍቅር ጀምር!**

# ምዕራፍ 14

## የሶቅራጥስ ምስጢር

ከሰዎች ጋር በምትነጋገርበት ጊዜ የማትስማማበትን ነጥብ በማንሳት አትጀምር። የምትስማማበት ነጥብ ላይ አጽንኦት በመስጠት ጀምር። እንዲያውም የሚቻል ከሆነ ሁለታችሁም ላንድ ዓላማ እንደተሰለፋችሁና ልዩነታችሁ እዚያ ለመድረስ በምትጠቀሙበት ዘዴ መሆኑን ደጋግመህ ግለጽ።

ሰውዬው አዎንታን እንዲደጋግም አድርገው። አይሆንም እንዳይል በተቻለህ መጠን የሚቃወማቸውን ነገሮች አታንሳ።

«አንድ ሰው አይሆንም ብሎ ከጀመረ» ይላል ፕሮፌሰር ኤቨርስትሪት «ልትቋቋመው በማትችለው ሁኔታ ውይይትህን ይሰነክልብሃል። አይሆንም ካለ በኋላ ተቃውሞውን ለመቀጠል ሰብአዊ ክብሩ ያስገድደዋል። እርግጥ ነው ዘግይቶ ሲያስበው አይሆንም ማለቱ ትክክል እንዳልነበረ ሊገነዘብ ይችላል። ግን ሰብአዊ ክብር እያለ በየት በኩል አንዴ ያ ነገር ካፍ ከወጣ ያንኑ ይዞ መጓዝን ይጠይቃል። ስለዚህም መነሳቱ በጣም አስፈላጊ ነው»

ነገር አዋቂ የሆነ ሰው «ሲጀምር አንስቶ» የአዎንታ መልሶች ይደረድሩለታል። በዚህም የአድማጮቹን አእምሮ ወደሚፈልገው አቅጣጫ ይመራቸዋል። ወደሚፈልገው አቅጣጫ በኃይል ስለሚገፋቸውም አድማጮቹ ለመቃወም ይቸገራሉ። ያመኑበትን ነገር መልሶ መጀመር ከፍተኛ ጥንካሬ ይጠይቃል። የአእምሯቸው ሁኔታ እዚህ ላይ ግልጽ ይሆናል። አንድ ሰው «አይሆንም» ካለ እና ይህን ያለው ከምሩ ከሆነ መናገሩ ብቻ ሳይሆን መቃወሙም ነው። የሥራ

አካላቱ ለተቃውሞ ይዘጋጃል:: በስብሰባ ላይ ብዙ ጊዜ በትንሹ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በከፍተኛ መጠን ስብሰባው እንዳልማማቸው በአካል የሚያሳዩ ወይም ስብሰባውን ረግጦ እስከመውጣት የሚደርሱ ሰዎች ይታያሉ:: ማለትም አካልም አእምሮም የተባለውን ነገር ላለመቀበል ይዘጋጃሉ ማለት ነው:: በተቃራኒው ግን አዎ የሚል መልስ ከተሰጠ ከስብሰባው ራስን የማገለሉ ተግባር አይኖርም:: ስለዚህም ሲጀምሩ በርከት ያሉ አዎንታዎችን ማግኘት የሰዎችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ይረዳል::

... አንድ ሰው ሌሎችን በአንድ ጉዳይ ላይ ሊያሳምናቸው ፈልጐ ከፍተኛ ተቃውሞ ካስነሳ ጥቅሙ ምንድነው? ሰዎች ማበሳጨት፣ ደስ የሚለው ከሆነ ደካማነቱ ነውና ይቅር እንለዋለን:: ነገር ግን ፍላጐቱ ማሳመን ከሆነ ቂል እንጂ ሌላ ሊባል አይችልም::

አንድን ሰው ተማሪም ሆነ ባለሱቅ፣ ሀገርም ሆነ አዋቂ፣ ሚስትም ሆነች ባል «አይሆንም» ብሎ እንዲጀምር ካደረግኸው ሀሳቡን ለማስቀየር የዚችን ዓለም ጥበብና ትዕግስት ሁሉ ተጠቅመህም ግብህን መምታትህ ያጠራጥራል::

ጀምስ ኤበርሰን የተባለ የባንክ ሠራተኛ አንድ ቀን ሰላጋጠመው ችግርና እንዴት እንደፈታው አጫውቶኛል:: አንድ ሰው ገንዘብ ለማስቀመጥ ወደ ባንኩ ይመጣል:: ኤበርሰን ቅጽ ይሰጠዋል:: ሰውዬው ቅጹን በከፊል ከሞላ በኋላ የቀረውን ለመሙላት እንደማይፈልግ ይገልጻል::

«በዚህ ጊዜ» ይላል ኤበርሰን ረጋ ባለ ሁኔታ በቅጹ ላይ የዘለላቸው መረጃዎች ለባንኩ ይህን ያህልም አስፈላጊ እንዳልሆኑ ገለጽኩለት:: በመቀጠልም «ሆኖም...» አልኩት «ገንዘቡን ተቀብለን አስቀመጥንልህ

እንበል። ባጋጣሚ ከዚህ ዓለም በሞት ብትለይ ማንኛውም ሰው እንደሚያውቀው ገንዘቡ ለትርብ ዘመድህ መሰጠት አለበት። ይሄ ደግሞ ሕጋዊ ነው፣ አይደል?»

«አዎ ልክ ነህ» አለኝ።

«ታዲያ ቅርብ የሆነ ዘመድህን ስም ብትሰጠን ደግ አይመስልህም?» አልኩት። አሁንም በድጋሚ «አዎ» አለና መለሰልኝ። የሰውዬው ሁኔታ እየተለወጠና እየቀዘቀዘ መጣ። ምክንያቱም ካደረግነው አጭር ውይይት ቅጹን የሚሞላው ለራሱ ጥቅም እንደሆነ ስለተረዳ ነው። በነገሩ ተስማምቶ ሲሰናበተኝ ይህ ጉልማሳ የተጠየቀውን መረጃ መስጠት ብቻ ሳይሆን በኔ ሀሳብ አቅራቢነት በእናቱ ስም የቁጠባ ሂሳብም ከፈተ። ስለእናቱም ብዙ አጫወተኝ።

ከዚያ ወዲህ ስጀምር ሰዎች ነገሬን በአዎንታ እንዲቀበሉኝ ካደረግሁ ሁሉን ነገር ትተው በትክክለኛ መንገድ ያቀረብኩትን ሃሳብ ያለማወላወል እንደሚቀበሉኝ ተረዳሁ።

ሶቅራጥስ የተባለው የግሪክ ፈላስፋ በታሪክ ውስጥ እፍኝ ለማይሞሉ ሰዎች ብቻ የሚቻል ነገር አደረገ። ያነጋገሩትን ሰዎች ሁሉ በውይይት ማሳመን ይችል ነበር።

በምን ዘዴ ነበር የሚጠቀመው? ሰዎቹን ተሳስታችኋል ይላቸው ነበር? ይህ የሶቅራጥስ ሥራ አይደለም። በጣም ቅን ነበርና እንዲህ ማለት አይችልም። ዛሬ «የሶቅራጥስ መንገድ» ተብሎ የሚታወቀውን በአዎንታ መልሶች ንግግር የመጀመርን ዘዴ ይጠቀም ነበር። ማለትም ተከራካሪው ያምንበታል ብሎ የሚያስበውን ጥያቄ ይጠይቃል። ነገር በአዎ ይጀመራል። በአዎ ይፈጸማል። አንተም ሀሳብህ ተቀባይነት እንዲያገኝ በምትሻበት ጊዜ ሶቅራጥስ ትዝ ይበልህ። የማያስቆጣ

t.me/BooksandYou.



ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጀምር። ቻይናውያን «ቀስ ብሎ የሚራመድ ሩቅ ይሄዳል» ይላሉ።

ስለዚህ፤

**ሰዎች ሀሳብህን እንዲቀበሉህ ስትፈልግ ከዚህ በታች ያለውን መመሪያ አስታውስ።**

**የተቃዋሚህን ሀሳብ አስቀድመህ ተረዳና የእምንታ መልስ በሚያስገኙልህ ነጥቦች ብቻ ንግግርህን ጀምር።**

pdf by @shuktuss ሹክቱስ

# ምዕራፍ 15

## ሰዎች እንዲተባበሩን ስለማድረግ፣

ሰዎች ከሚሰጡህ ወርቃማ ሀሳብ ይልቅ ራስህ ተመራምረህ የደረስክበትን ሀሳብ ይበልጥ ታምንበታለህ። እንዲያ ከሆነ የኔን ሀሳብ ተቀበሉኝ ብሎ ሰዎችን ማስጨነቅ መጥፎ ነገር አይመስልህምን? ዝም ብሎ ሀሳብ ማቅረብ እና ሌላው ሰው የራሱን ፍርድ እንዲሰጥ ነገሩን ለሰውዬው መተው አዋቂነት አይመስልህምን?

ነገሩን በምሳሌ ለማስረዳት፣

የአንድ መኪና መሸጫ ድርጅት ባለቤት የሆነ ሰው ገበያው እየቀዘቀዘበት ስለሄደ በስራቸው ደከም ያሉ ሠራተኞቹን ለማበረታታት ስብሰባ ጠራ። ሥራው መቀዝቀዙን ሁሉም እንደሚያውቁት ገልጾ ምክንያቱን እሱ ሊያውቀው ስላልቻለ እነሱ እንዲያስረዱት ጠየቃቸው። እያንዳንዱ ሠራተኛ ሀሳብ ሰጠ። የተሰጡትንም ሀሳቦች ጥቁር ሠሌዳ ላይ ጻፈ። በመጨረሻም በሱ በኩል ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ነገሮች ጠየቃቸው። ሠራተኞቹም ነገሩት። እሱ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ናቸው ተብለው በሠራተኞቹ የተጠቆሙትን ሀሳቦችም እጥቁር ሠሌዳው ላይ ጻፈ። ከዚህ በኋላ ከኔ የሚፈለጉትን ነገሮች ሁሉ እፈጽማለሁ። እናንተ ደግሞ ልትፈጽሙ የሚገባችሁን ነገሮች ንገሩኝ ሲላቸው፣ ታማኝነት፣ ሀቀኝነት፣ እስበ መስራት፣ ተባብሮ መስራት፣ ስምንቱን ሰዓት በሙሉ ልብ እሥራ ላይ ማዋል የሚሉ መልሶች እየተሸጎደጎዱ መጡለት። እንዲያውም አንዱ ሠራተኛ በቀን አስራ አራት ሰዓት ለመሥራት ፈቃደኛ እንደሚሆን ገለጸ። ስብሰባው አዲስና ጠንካራ መንፈስ በሠራተኞቹ ላይ በማሳደር ተፈጸመ። «ከዚያ ጊዜ ጀምሮ» ይላል የድርጅቱ ባለቤት «የገባሁላቸውን ቃል እስካከበርኩ ድረስ እነሱ

ቃላቸውን ሳያጥፉ ሥራቸውን ቀጠሉ። የሠራተኞቹን ፍላጐትና ምኞት መጠየቁ ራሱ ሞራላቸውን ለመጠበቅ የሚረዳ ፍቱን መድኃኒት ሆኖ ነው ያገኘሁት።»

ማንም ሰው አንድ ነገር ሸጥኩልህ ሲሉት ወይም ይህን ነገር አድርግ ሲሉት አይወድም። ሁላችንም አንድ ነገር ገዛን ወይም ይህን ነገር አስበን ሠራን ማለትን እንመርጣለን። ስለምንፈልገውና ስለምንመኘው ነገር እንዲሁም ባንድ ጉዳይ ላይ ስላለን አስተያየት ስንጠየቅ ደስ ይለናል።

አቶ ዌሰን የተባለ የልብስ ዲዛይን ነዳፊ 150 ጊዜ በተደጋጋሚ ዲዛይኖቹን ለአንድ የልብስ ስፌት ድርጅት ለመሸጥ ጥሮ ሳይሳካለት ይቀራል። በዚህ ጊዜ ዌሰን ጉድለቱ ከራሱ መሆኑን ይገነዘባል። ሰዎችን የሚያግባባበትን ዘዴ ይፈልጋል። በሳምንት አንድ ቀን እኤም ዘንድ እየመጣ ምክሮችን ይቀበል ነበር። ከዚያም የልብስ ስፌት ድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ ከዚህ በፊት ባልሞከረው መንገድ ሊቀርበው ይወስናል። አንድ ቀን ስድስት ያህል ያላለቁ ዲዛይኖችን ይዞ ሄደና ባለቤቱን ፈቃደኛ ከሆንክ አንድ ነገር ላስቸግርህ አለ። «እነዚህ የምታያቸው ያላለቀላቸው ንድፎች ናቸው። በምን ሁኔታ ቢያልቁ ነው ቆንጆ የሚሆኑት?»

የድርጅቱ ባለቤትም ንድፎቹን በዝምታ ለጥቂት ጊዜ ከተመለካከተ በኋላ «እስኪ እዚህ ተዋቸውና ሂድ ነገ ስትመለስ አስተያየቴን እነግርሃለሁ» አለው። ዌሰን ከሦስት ቀን በኋላ ሲመለስ ባለቤቱ ስለንድፎቹ ያለውን አስተያየት ሰጠው። ከዚያም ንድፎቹን ስቱዲዮው ወሰደ። በተሰጠው ሀሳብ መሠረት ጨረሰ። ውጤቱ ምን የሆነ ይመስልሃል? የልብስ ስፌት ድርጅቱ ባለቤት ሁሉንም ገዛቸው።

ዌሰን ይህን አሠራር ደጋገመው:: ከድርጅቱ ጋርም የጠበቀ ደንበኝነት መሠረተ:: ያለፈውን ጊዜ አስታውሶ ሲናገር ዌሰን፣

«ያኔ ለምን እንዳልተሳካልኝ አሁን ገብቶኛል:: የድርጅቱን ባለቤት ንድፎቹን እንዲገዛኝ ነበር የምገፋፋው:: አሁን ግን በመጀመሪያ ሀሳብ እንዲሰጠኝ እጠይቀዋለሁ:: በሰጠኝ ሀሳብ መሠረት ንድፎቹን እሠራቸዋለሁ:: እንዲህም ሳደርግ ንድፎቹን እኔ ሳልሆን ራሱ የፈጠራቸው እንዲመስለው አደርገዋለሁ:: ዛሬ ንድፎቹን እኔ አልሸጥለትም:: እሱ ነው የሚገዛኝ::»

አንድ የሕክምና መሳሪያዎች አምራች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ለአንድ የታወቁ ሀኪም እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጻፈ::

«የተከበሩ ዶክተር፣ ፋብሪካችን አዲስ ዓይነት የኤክስሬይ መሳሪያ ሠርቶ አውጥቶ ነበር:: ሆኖም መጀመሪያ የተመረቱትን ስንመለከታቸው ጥቃቅን ጉድለቶች አይተንባቸዋል:: ጉድለቶቹን ለማረም አስበናል:: ከዚያ በፊት ግን መጥተው አይተውልን እኛ ያላየናቸውን ጉድለቶች እንዲጠቁሙን እንፈልጋለን:: ይህን ስንጠይቅ ደግሞ ማስቸገራችን ይሰማናል:: የሚመችዎትን ሰዓት ቢነግሩኝ መኪናዬን ለመላክ ዝግጁ ነኝ::»

«እንዲህ ዓይነት ደብዳቤ ሲደርሰኝ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበርና በጣም አስደነቀኝ:: የመንፈስ ኩራትም ተሰማኝ:: ይህ ደብዳቤ በደረሰኝ ሳምንት በሥራ ተወጥሬ ነበር:: ሌሎች ቀጠሮዎችም ነበሩብኝ:: ስለዚህ አንዱን የምሳ ግብዣ ሠርዤ መሳሪያውን ለመመልከት ሄድኩ:: የኤክስሬዩን አሠራር እያጠናሁት በሄድኩ ቁጥር እየወደድኩት ሄድኩ:: በዚያም ላይ ማንም ሰው ይህን መሳሪያ እንድገዛ ያግባባኝ አልነበረም:: ስለወደድኩት ብቻ የምሠራበት ሆስፒታል መሣሪያውን መግዛት

እንዳለበት ወሰንኩ:: የመሣሪያው ጥራት አሸነፈኝ:: እናም ለሆስፒታል እንዲላክ ትዕዛዝ ሰጠሁ::»

ከዛሬ 2500 ዓመት በፊት በቻይና የኖረው ላኦ ትዜ ለሁላችንም የሚጠቅም አባባል ብሎ አልፏል::

«ወንዞችና ባህሮች ከተራራ ላይ የሚፈልቁ ምንጮችን ሁሉ የሚቀበሉበት ምክንያት ከምንጮች በታች ስለሆኑ ነው:: ስለዚህ ምንጮቹን ለማስገበር ይችላሉ:: አዋቂ ሰውም ከሰዎች በላይ ለመሆን ራሱን ዝቅ ያደርጋል:: ሊመራቸው ሲፈልግም ምሩኝ ይላቸዋል:: ስለዚህም ምንም እንኳ ከሰዎች ቢበልጥ ትልቅነቱ አይሰማቸውም:: ከፍተኛ ቦታ ቢሰጡትም እንደተዋረዱ አይቆጥሩትም::»

ስለዚህ!

**ሰዎች እንዲተባበሩሀና የፈለግኸውን እንዲፈጽሙልህ ብትፈልግ፣**

**እንዲተባበርህ የፈለግኸው ሰው ሀሳቡን ራሱ ያፈለቀው እንዲመስለው አድርግ!**

# ምዕራፍ 16

## ጥላቻን የሚያስከትል ትችት ስለመሰንዘር

ቻርለስ ሽዋብ አንድ ቀን በስሩ የሚተዳደሩ ሠራተኞች «ማጨስ ክልክል ነው» በሚል ማስታወቂያ ስር ተቀምጠው ሲጋራ ሲያጨሱ ይደርሳል:: ሠራተኞቹ እንዳዩት ሲጋራቸውን አጥፍተው ይደብቃሉ:: ሽዋብ ምን ያላቸው ይመስልሃል? አይቻችኋለሁ አትደበቁ አላለም:: አጠገባቸው እንደ ደረሰ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ሲጋራ አደላቸውና «ወጣ ብላችሁ ብታጨሱ ደስ ይለኛል» አላቸው:: እንዳወቀባቸው ገባቸው፤ አደነቁት:: ምክንያቱም መቆጣት ሲችል ስላከበራቸውና ስጦታም ስለጨመረላቸው ነበር:: እንዲህ ዓይነቱን ሰው መጥላት ይቻላል?

አንድ ትልቅ የገበያ አዳራሽ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰውም ተመሳሳይ ነገር ፈጽሟል:: አንድ ቀን ወደ ገበያ አዳራሹ ሲገባ አንድ ዕቃ ልትገዛ የመጣች ሴት ሂሳብ ለመክፈል ስትጠባበቅ አየ:: ሠራተኞቹ ግን አንድ አካባቢ ተሰብስበው ያወኩ ነበር:: ሥራ አስኪያጁ ሠራተኞቹን ምንም ሳይናገር የገንዘብ ተቀባዩን ቦታ በመተካት ሴትዩዋን ማስተናገድ ጀመረ:: ይህንን ያዩት ሠራተኞች ተደናግጠው ወደየሥራቸው ተሰማሩ:: ሥራ አስኪያጁ የሴትዩዋን ሂሳብ ካጠናቀቀ በኋላ ምንም ሳይናገር ወደ ቢሮው ተመለሰ::

አንድ ሰው የሬዲዮ ትያትር ይጽፍና ለሚስቱ ያነብላታል:: ትያትሩ ትያትር ሊባል የሚችል አልነበረም:: ሚስትየዋ ስለትያትር ታውቅ ነበር:: ሆኖም ይህ ትያትር አይደለም፤ ቢተላለፍ አድማጭ አያገኝም ለማለት ስትችል እሷ ግን ጥሩ የፍልስፍና ማስተማሪያ

ይሆናል አለችው። እንዲህ ስትል ምን ማለቷ እንደሆነ ለባሏ ገባው። ሆኖም ጽሑቶን ባንድ ወገን ስታኮሰሰው በሌላ በኩል ሰላደነቀችው ቅር አልተሰኘም። በሬዲዮ እንዲተላለፍ የማድረግ ሃሳቡን ግን ሰረዘው።

**ሰዎች ሳይቀየሙ ወይም ቅሬታ ሳያድርባቸው ሁሳባቸውን እንዲለውጡ ለማድረግ የሚከተለውን መመሪያ ተጠቀም። ስህተታቸውን በተዘዋዋሪ መንገድ ንገራቸው!**

# ምዕራፍ 17

## ስህተትህን እመን

ፈርዲናድ ዎረን የተባለ የንግድ ስዕል ሰዓሊ እንዲህ ብሎ አጫውቶኛል::

«... ስህተት ፈልጎ ማግኘት የሚወድ ስዕሎችን የሚገዛ አንድ ሰው አውቃለሁ:: ስዕል ለመሸጥ በሄድኩ ቁጥር በጣም ቅር ብሎኝ ነበር የምመለሰው:: እንደዚህ የሚሰማኝ ትችቱን የሚሰነዝረው ሰውን ለማስቀየም ብሎ ስለነበር ነው:: በቅርቡ አንድ ስዕል ሠርቼ ለጥቼው እንደተመለስኩ ወደቢሮዬ በፍጥነት ድረስ ብሎ ስልክ ደወለልኝ:: እንደደረስኩም የፈራሁት ነገር አጋጠመኝ:: በጥላቻ መልክ የትችት ናዳ አወረደብኝ:: ለምን እንዲህ አደረግህ? ያን ለምን እንደዚህ አደረግህ? እያለ በጥያቄ ያጣድፈኝ ጀመር:: በዚህ ጊዜ መከላከሌን ትቼ የራሴን ስህተት ማጋነን ጀመርኩ:: 'የምትለው ሁሉ እውነት ከሆነ ፈጽሞ ምህረት ሊደረግልኝ የሚገባኝ ሰው አይደለሁም:: ለእናንተ እንኳ ስዕሎች ሳቀርብ ይኸውና ብዙ ዓመቴ ነው:: እና ይህን ሁሉ ሠርቼ እንዲህ ዓይነት ስህተት ከፈጸምኩ በጣም ላፍር ይገባኛል::' ሰለው ወዲያው ሀሳቡን ቀየረና ለኔ መከላከል ጀመረ:: 'ልክ ነህ ነገር ግን ይህን ያህል የጐላ ስህተት እኮ የለም እንዲያው ትንሽ' ሲል አቋረጥኩትና፣ 'እባክህ ተወኝ ትንሽም ስህተት ቢሆን እናንተን ያከስራችኋል:: ብቻ ነገሩ በጠቅላላው ያበሳጫል' አልኩት:: ሊያቋርጠኝ ሞከረ፣ ግን አልቻለም:: እኔ ለራሴ በሁኔታው እየተደሰትኩ ነበር:: በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሴን እየወቀስኩ ነበርና ደስ አለኝ::

'የለም የለም በጣም መጠንቀቅ ነበረብኝ' አልኩና ቀጠልኩ::

'ብዙዎቻችን ስዕሉቹን የምትገዙን እናንተ ናችሁ:: ስለዚህ ደግሞ በደንብ ልሠራላችሁ ይገባል:: ስለዚህ ስዕሉን መልስልኝና እንደገና እሠራዋለሁ':: እንዲህ ስለው በጣም አዝኖ፣ 'የለም እንደሉ አይደለም እንዴ ምኑን አመጣህብኝ? ይህን ሁሉ ችግር ልጭንብህ አልፈቅድም' አለና ተከራከረኝ:: ስዕሉን ማድነቅ ጀመረ:: ያሉብት ስህተቶችም በጣም ጥቃቅን እንደሆኑ ማንም ኪሣራ እንደማያደርስበት ፍጹም ልጨነቅ እንደማይገባኝ አረጋገጠልኝ::

ራሴን ስህተተኛ ለማድረግ የነበረኝ ጉጉት ሊያነሳው ያሰበውም እምባ ጓሮ ድራሹን አጠፋው:: እንዲያውም ምሳ ጋበዘኝና ልንለያይ ስንል ሌላ ስዕል እንድሠራለት በቅድሚያ ገንዘብ ሰጠኝ::»

ሞኝ ስህተቱን ለመሸፈን ይጥራል:: ነገር ግን ስህተትን ማመን ከፍተኛ ደስታ ይሰጣል::

አልበርት ሂዮባርድ የተባለ ደራሲ አንድ ጽሑፍ በጻፈ ቁጥር ብዙ ሰዎችን ያስቆጣ ነበር:: ሆኖም የሚጠሉትን ሰዎች ካወቃቸው ወዳጅ የሚያደርግበት ዘዴ ነበረው:: ሂዮባርድ አንድ ጽሑፍ ቢጋዜጣ ላይ ቢያወጣና አንድ የተቆጣ አንባቢ ከሱ ጋር እንደማይስማማ ገልጾ ሰድብ መልስ ቢጽፍ ሂዮባርድ ለሰውዬው እንዲህ የሚል ደብዳቤ ይጽፍለት ነበር::

«...ሳስብበት እኔም በነገሩ ሙሉ በሙሉ አልተስማማሁበትም:: ትናንት የጻፍኩት ነገር ዛሬ አያስደስተኝም:: በዚህ ጉዳይ ላይ ያለህን አስተያየት ስረዳ ደስታ ተሰማኝ:: እንደአጋጣሚ ወደምኖርበት ብቅ ካልክ ነገሩን አንስተን እናበጥረዋለን:: ለጊዜው ግን በሩቅ እንጨባበጥ::»

ምንጊዜም ያንተው

አልበርት ሂዮባርድ

እንግዲህ እንዲህ ያለውን ሰው ምን ትሉታላችሁ? ለወደፊቱ ትክክል ስንሆን አስተሳሰባችንን እንዲረዱልን በትዕግስት እናስረዳቸው:: ስንሳሳት ደግሞ ስህተታችንን ያለ ቅሬታ እንመንላቸው:: ይህን የቆየ አባባል አስታውስ::

«በመጣላት የምንፈለገውን ያህል አናገኝም

እውቀን በመተው ግን ያልጠበቅነውን ያህል እናገኛለን::»

ስለዚህም ከሰዎች ጋር ተስማምተህ ለመኖር ይህንን መመሪያ አስታውስ::

መሳሳትህን ካወቅህ ሳታወላውልና ቅር ሳትሰኝ ስህተትህን እመን::

# ምዕራፍ 18

## የማስታወስ ችሎታን ስለማሻሻል

«አብዛኛው ሰው በተፈጥሮው ከወረሰው የማስታወስ ችሎታው አስር ከመቶ በላይ አይጠቀምም። የማስታወስን ተፈጥሯዊ ሕጎች በመጣስ ከችሎታው ዘጠና በመቶውን ያበላሸዋል» አሉ። የታወቀው ሳይኮሎጂስት ፕሮፌሰር ካርል ሲሾ፣ አንተስ ከአብዛኛው ሰው መካከል ነህን? ከሆንክ በማህበራዊ ኑሮና በሥራህ አኳያ ከፍተኛ መሰናክል አለብህ ማለት ነው። ስለሆነም ይህን ምዕራፍ ደግመህ ደጋግመህ ብታነበው ደስታም ጥቅምም ታገኝበታለህ። ይህ ምዕራፍ የማስታወስን ተፈጥሯዊ ሕጎች እንዲሁም በሥራህና በማኅበረሰቡም ውስጥ ከሰዎች ጋር የምትግባባበትን መንገድ የሚያወሳና በአደባባይም ንግግር ለማድረግ የሚረዳ ነው።

እነኝህ የማስታወስ የተፈጥሮ ህጎች የሚባሉት በጣም ቀላል ናቸው። በቁጥርም ሶስት ብቻ ናቸው። የማስታወስ ስልት የሚባለው የተመሰረተውም በእነኝህ በሶስቱ ላይ ነው። ባጭሩ የማስታወስ ተፈጥሯዊ ህጎች የሚባሉት፣

1. ነገሩን በአእምሮ መቅረጽ
2. ነገሩን ደጋግሞ ማሰብ
3. ነገሩን ከሌሎች ነገሮች ጋር ማገናዘብ ናቸው።

1. <u>ነገሩን በአእምሮ መቅረጽ</u>

የመጀመሪያ ተፈጥሯዊ የማስታወስ ህግ ልታስታውስ የምትፈልገውን ነገር ግልጽ እስኪሆንልህ ድረስ ጠለቅ ብለህ እኘናው። ይህንንም ለማድረግ ነገሩን በተመስጦ መመልከት አለብህ።

ዴል ካርኔጊ

አንድን ነገር ዓመት ሙሉ ላይ ላዩን ከመመልከት ለአምስት ደቂቃ አእምሮን ሰብስቦ በጥሞና ማጥናቱ የበለጠ ውጤት ያመጣል። ሄንሪ ወርድ ቢቸር ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር «አንድ የጥሞና ሰዓት ከአንድ ዓመት እንጉል ህልም ይሻላል» ይላል።

ቶማስ ኤድሰን በአምፖል ፋብሪካው ውስጥ የሚሠሩት ሠራተኞች ዘወትር በአንዲት ቀጭን መንገድ እንደሚያልፉ አይቶ ነበር። በዚህም ቀጭን መንገድ ዳር ላይ አንዲት የወይራ ዛፍ ነበረች። ሠራተኞቹ አንድ ቀን ዛፏን አይተዋት እንደሆነ ቢጠይቃቸው ሁሉም ልብ እንዳላሏት ገለጹለት። ከዚህም በመነሳት ቶማስ ኤድሰን እንዲህ ይላል። «የአብዛኛው ሰው አእምሮ አይኑ ከሚያየው ነገር መካከል አንዱን እንኳ አያጤንም ወይም ልብ አይልም። ልብ የማድረግ ችሎታችን ምን ያህል ደካማ እንደሆነ ለማመን ያዳግታል።»

እስኪ ጓደኛህን ከሁለት ወይም ሶስት ሌሎች ጓደኞችህ ጋር አስተዋውቀውና ከሁለት ደቂቃ በኋላ ስማቸውን ጠይቀው። ምናልባት ያንዳቸውንም ስም አያስታውስም ይሆናል። ለምን ይመስልሃል? ምክንያቱም ስማቸውን በደንብ ካለመስማቱም ሌላ ሰዎቹንም በሚገባ አላስተዋላቸውም ነበርና ነው። ምናልባት ለምን ረሳህ? ብትለው የማስታወስ ችሎታዬ ደካማ ነው ይልህ ይሆናል። ይህ ግን ስህተት ነው። ደካማ የማስታወስ ችሎታ ሳይሆን ደካማ የመመልከት ችሎታ ነው ያለው። ካሜራ በጉም ውስጥ ደህና ፎቶግራፍ እያነሳም ብለን መጥፎ ነው እንለውም። ይህም ሰው በትክክልና በጨረፍታ የሰማውንና ያየውን ሰላልመዘገበ ማስታወስ አልቻለም ብሎ አእምሮውን ሊወቅስ አይገባውም።

የአንድን ሰው ስም ለማስታወስ ብትፈልግ የሰውየውን ስም ጠ

ንቅቀህ ስማ። እንዲደግምልህም ጠይቀው። ይህን ስታደርግ ደግሞ የወደድከው ስለሚመስለው ይቀርብሃል። አንተም ስሙን ትይዛለህ። ሰውዬውም በደንብ እንዲያውቅህ ታደርገዋለህ። አብርሃም ሊንከን ሁሉን ነገር ጮክ ብሎ ማንበብ ይወድ ነበር። አንድ ቀን ሊንከን ጮክ ብሎ ጋዜጣ ሲያነብ በዚህ ልምዱ ይበሳጭ የነበረ የሥራ ባልደረባው ለምንድነው እንደዚህ የምታነበው? ብሎ ቢጠይቀው ሊንከን «ጮክ ብዬ ሳነብ ማለት የስሜት ህዋሳቴ ነገሩ እንዲደርሰኝ ያደርጋሉ። በመጀመሪያ የማነበውን በአይኔ አየዋለሁ፤ ደግሞ በጆሮዬ እሰማዋለሁ። ስለዚህም ድምጽ ሳላሰማ ከማነበው የበለጠ ነገሩ ይገባኛል» አለው።

«አእምሮዬ» ይላል አብርሃም ሊንከን «እንደ ብረት ሰሌዳ ነው። በቀላሉ ልትጭረው አትችልም። ከጫርክበት በኋላም ለማጥፋት እጅግ አስቸጋሪ ነው።» ለማስታወስ አንድን ነገር ማየት በጣም አስፈላጊ ነው። በአይን ሀሊና ወይም በአይን ሥጋ ያየነው ነገር በቀላሉ አይጠፋም። ምንጊዜም ቢሆን አንድን ሰው ካየነው በኋላ ገጽታውን አንረሳውም። ስሙ ግን ሊጠፋ ይችላል። ከአይኖቻችን ወደ አንጐላችን መልዕክት የሚወስዱ ነርቮች ብዛት ከጆሮዎቻችን ወደ አንጐላችን መልዕክት የሚወስዱትን ሃያ እምስት ጊዜ ያህል ይሆናሉ። ስለዚህም ከሰማነው ይልቅ ያየነውን እናስታውሳለን። «አንድ ጊዜ ማየት ሺህ ጊዜ የመስማትን ያህል ነው» ይላሉ ቻይናውያን ሲተርቱ።

2. <u>ነገሩን ደጋግሞ ማሰብ</u>

ሁለተኛው የማስታወስ ተፈጥሯዊ ህግ ነገሩን ደጋግሞ ማሰብ ነው። አንድን ነገር ደጋግሞ በማለት ወይም በማሰብ ሁለት መሰፈርት የሌለውን ነገር ማስታወስ እንድትችል ያደርግሃል። ልታስታውሰው

የፈለግኸውን ነገር ደጋግመህ አስበው፣ ወይም በለው:: በሥራ ላይ አውለው:: ልታስታውሰው የፈለግኸው አዲስ ቃል ከሆነ በንግግርህ ውስጥ ተጠቀምበት:: በአደባባይ ንግግር የምታደርግ ከሆነ የያዝካቸውን ነጥቦች ከሌሎች ጋር ተወያይባቸው:: በተግባር የዋሉት ዕውቀት ከአእምሮ አይጠፋም::

ሆኖም ነገሩን ጠለቅ ብሎ ሳይረዱ በጭፍን ቢደጋግሙት ዋጋ የለውም:: ማድረግ ያለብን ነገሩን ጠለቅ ብሎ መረዳትና የያዝናቸውን ነጥቦች ከነመረጃቸው ማጥናት ያስፈልጋል:: ሚስጥራቸውን ሳንረዳ በመደጋገም ልንጠቀምባቸው የምንፈልጋቸውን ነገሮች ሚስጥራቸውን ተረድተን ከምናጠናቸው ነገሮች የበለጠ ጊዜ ይፈጃል:: ሚስጢራቸውን ተረድተን ያጠናናቸው ነገሮች ይበልጥ ለረጅም ጊዜ በአእምሮአችን ውስጥ ይቆያሉ::

3. ነገሩን ከሌሎች ነገሮች ጋር ማገናዘብ

የታወቀው ፈላስፋ ዊሊያም ጀምስ እንደሚለው አእምሯችን ነገሮችን የሚያገናዝብ መኪና ነው:: ለምሳሌ አእምሯችንን በደፈናው አስታውስ፣ ትዝ ይበልህ ብንለው ምንም መልስ አይሰጠንም:: ምን እንደሚያስታውስ፣ ምን ትዝ ሊለው እንደሚገባ መጠቆም ይኖርብናል:: ለምሳሌ የተወለድክበትን ቀን አስታውስ፣ ወይም ፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ ዋናው ገጸ ባህርይ ትዝ ይበልህ ብንለው በቀላሉ ሊያስታውስ ይችላል:: ምክንያቱም አእምሯችን የተወለድኩበትን ቀን የሚለውን ጠቋሚ ሐረግና በውስጡ የተቀመጠውን ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት ያዛምዳል:: እንዲሁም በፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ ያለውን ዋና ገጸ ባህርይ የሚለው ሐረግ በአእምሯችን ውስጥ ካለው የገጸ ባህርዩ ስም ጋር ይገናዘባል:: በአጠቃላይ የማገናዘብ ህግ ተከታትለው የሚመጡትን

ሀሳቦች ሁሉ ካለፈ ልምዳችን ጋር የምናያይዝበት ህግ ነው:: የዳበረ የማስታወስ ችሎታ በተቃና የማገናዘብ ዘዴ ላይ የተመረከዘ ነው:: የማገናዘቡ ተራትም በሁለት ነገሮች ይወሰናል:: አንደኛው ያለማቋረጥ ማገናዘብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በአጠራቀምነውና ልናገናኝበው በምንችለው እውቀት መጠን ነው::

ስለዚህም በደንብ የማስታወስ ትልቁ ሚስጢር ነገሩን ከተለያዩ ነገሮች ጋር በየአቅጣጫው ማገናዘብ ነው::

ባጭሩ ተመሳሳይ የኑሮ ልምድ ካላቸው ሁለት ሰዎች መካከል የተሻለ የማስታወስ ችሎታ የሚኖረው የኑሮ ልምድን ወደኋላ መለስ ብሎ ደጋግሞ የሚያስብበት ሰው ነው::

ይህስ ሆነ፤ ነገሮችን እርስ በርስ የምናዛምዳቸው እንዴት አድርገን ነው? መልሱ ቀላል ነው:: ትርጉማቸውን መረዳት:: በሁኔታው ማሰብ:: ለምሳሌ ስለአንድ ነገር የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቀህ መልሳቸውን ብትሰጥ ነገሮችን ለማዛመድ ይረዳሃል::

ሀ/ ይህ ለምን ሆነ?

ለ/ እንዴት ሆነ?

ሐ/ መቼ ሆነ?

መ/ የት ነው የሆነው?

ሠ/ ሆን ያለው ማነው?

## ማጠቃለያ

1. የማስታወስ ችሎታህን ለማሻሻል ከፈለግህ ተፈጥሮ በለገሰችህ የማስታወስ ችሎታ ሙሉ በሙሉ ተጠቀምበት:: ይህንንም

ለማድረግ፣

2. ስስቱን ተፈጥሯዊ የማስታወስ ህጉች በሥራ ላይ አውል። እነሱም፣

ሀ/ ነገሩን በአእምሮ መቅረጽ

ለ/ ነገሩን ደጋግሞ ማሰብ

ሐ/ ነገሩን ከሌሎች ነገሮች ጋር ማገናዘብ ናቸው።

3. ሊታስታውሰው ስለምትፈልገው ነገር ግልጽና ጥልቀት ያለው ዕውቀት መስርት። ይህንንም ለማድረግ፣

ሀ/ ነገሩን በተመሰጠ መመልከት

ለ/ ነገሩን ቀረብ ብሎ ማጥናት

ሐ/ በተቻለ መጠን በሁሉም የስሜት ህዋሳት ለመጠቀም መሞከር

መ/ ከማንኛውም ነገር ይበልጥ በአይን አይቶ ለመረዳት መሞከር

4. ትርጉሙን ሳይረዱ ለመሸምደድ አለመሞከርና፣ ስለአንድ ነገር የያዝነውን ማስታወሻ ደጋግመን ማየት፣

5. አዲስ ነገር ሲያጋጥምህ ከዚህ በፊት ከምታውቃቸው ነገሮች ጋር ለማዛመድ መሞከር። ይህን ለማድረግ፣

ሀ/ ከተለያዩ ነገሮች ጋር በየአቅጣጫው ለማዛመድ መሞከር

ለ/ አዳዲስ ቁጥሮች ሲያጋጥሙህ በፊት ከምታውቃቸው ቁጥሮች ጋር ማዛመድ

ለምሳሌ የጓደኛህ የፖስታ ሣጥን ቁጥር 1888 ቢሆን ከአድዋ ጦርነት ጋር አዛምደህ አስበው።

t.me/BooksandYou



፮. ንግግር ማድረግ ጀምረህ የምትለው ቢጠፋብህ በመጨረሻ የተናገርከውን አረፍተ ነገር እንደመነሻ አድርገህ ሳትሸበር ንግግርህን ለመቀጠል ሞክር።

ተፈጸመ

pdf by @shuktuss ሹክቱስ